# የዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) (ምዕራፍ 2)

# የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ዘላቂታማነት ማዕቀፍ

SRMI Sustainable Renewables Risk Mitigation Initiative

*የSRMI ተቋም የE&S ዘለቄታማነት ማዕቀፍ አረዳድ ላይ ማናቸውም ዓይነት ጥርጣሬ ቢፈጠር የእንግሊዝኛው ዕትም በማናቸውም ሌሎች የተተረጐሙ ዕትሞች ላይ የበላይነት ይኖረዋል።*

## ማውጫ


**1. መግቢያ ........................................................ 4**

**2. ተቋሙ አሁን ያለበት ዓውዳዊ ዕይታ ........................................................ 5**

2.1 አስፈላጊነቱ ........................................................ 5

2.2 የተቋሙ ዓላማዎች ........................................................ 6

2.3 የተቋሙ አጠቃላይ ዕይታ ........................................................ 7

2.4 የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋት ቁጥጥር የአፈጻጸም ዘዴ........................................................ 8

**3. በተቋሙ ሥር የሚከናወን የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋት መቆጣጠሪያ ዘዴ ........................................................ 10**

3.1 ሊያጋጥሙ የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ........................................................ 10

3.2 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) መስፈርቶች ........................................................ 10

3.3 በፕሮጀክቶች ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች እና መፍትሔ እርምጃዎች........................................................ 13

3.3.1 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1)........................................................ 14

3.3.2 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2)........................................................ 14

3.3.3 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 3 (ESS3)........................................................ 15

3.3.4 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 4 (ESS4)........................................................ 15

3.3.5 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS5)........................................................ 16

3.3.6 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 6 (ESS6)........................................................ 16

3.3.7 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7)........................................................ 16

3.3.8 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 8 (ESS8)........................................................ 16

3.3.9 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 9 (ESS9)........................................................ 17

3.3.10 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS10)........................................................ 17

**4. በፕሮጀክት ዝግጅት እና ትግበራ ወቅት አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋት ቁጥጥር ........................................................ 18**

4.1 የፕሮጀክት ዝግጅት........................................................ 18

4.2 የፕሮጀክት ትግበራ ..... 19

**5. የመረጃ ይፋ አወጣጥ፣ የባለ ድርሻ አካላት እና የቅሬታ አፈታት ዘዴ ..... 21**

5.1 የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ እና መረጃን ይፋ ማውጣት ..... 21

5.2 የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) የቅሬታ አፈታት ዘዴዎች ..... 22

**ዓባሪ 1፡- የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ግዴታ ዕቅድ ጠቋሚ ዝግጁ አብነት (ቴምፕሌት) ..... 24**

**ዓባሪ 2፡- የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ ማረጋገጫ ዝርዝር ..... 36**

**ዓባሪ 3፡- የባለድርሻ አካል ተሳትፎ ዕቅድ ጠቋሚ ዝግጁ አብነት (template) ..... 40**

**ዓባሪ 4፡- የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘና (ESIA) እና የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ጠቋሚ ቢጋሮች ..... 48**

**ዓባሪ 5፡- የዳግም ሰፈራ ፖሊሲ ማዕቀፍ ጠቋሚ ..... 55**

**ዓባሪ 6፡- ለዳግም ማቋቋሚያ ዕቅድ የድርጊት መርሐ ግብር ጠቋሚ ቢጋር ..... 64**

**ዓባሪ 7፡- የአካባቢ ተወላጆች ዕቅድ አዘጋጀት ማዕቀፍ ጠቋሚ ..... 68**

**ዓባሪ 8፡- የአካባቢ ተወላጆች ዕቅድ ጠቋሚ ቢጋር ..... 76**

**ዓባሪ 9፡- የሠራተኛ አስተዳደር አሠራር ሥርዓቶች ጠቋሚ ..... 79**

**ዓባሪ 10፡- ሥርዓተ ጾታ ..... 84**

# 1. መግቢያ

ይህ ሰነድ በ*ዘላቂነት ያላቸው ታዳሾች የስጋት መቆጣጠሪያ የሥራ ውጥን (ምዕራፍ 2)/ Sustainable Renewables Risk Mitigation Initiative (SRMI) Facility (Phase 2)* ክትትል የሚደረግበትን የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ዘላቂታማነት ማዕቀፍን /Environmental and Social Sustainability Framework (ESSF)/ ምንነት ያብራራል። የተቋሙን የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተጠቃሚነት (E&S) ማረጋገጫ ክትትልና ቁጥጥር ማድረጊያ ዘዴ እንደ መንደርደሪያ ሆነው የሚያገለግሉትን መመዘኛ መስፈርቶች፣ የክንውን ሂደቶች እና መርጃ መሣሪያዎችን ያብራራል።

በዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ሥር እንደ ሐሳብ ለቀረቡ ፕሮጀክቶች አስፈላጊ ሊሆን የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ፋይዳ ያላቸውን ሰነዶች ዝግጁ አብነቶችን እና የሥራ ውጥን ቢጋሮችን በተጨማሪ ያካተተ ሰነድ ነው።

ESSF በተጨማሪ በዓለም ባንክ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) ላይ በተገለጸው መሠረት ተበዳሪዎች ከፕሮጀክቶች ጋር ቁርኝት ያላቸውን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ችግሮች በዓለም ባንክን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶችን (ESSs) በማሟላት መቆጣጠር እንዲችሉ መውሰድ ያለባቸውን ዋንኛ እርምጃዎችን ያብራራል።

እንደ SRMI ተቋም አንድ አካልነቱ፣ ይህ አሁን የቀረበው ESSF በተቋሙ ውስጥ በተካተቱ በሁሉም ፕሮጀክቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። ፕሮጀክቶቹ በኢትዮጵያ፣ በጊኒ ቢሳዎ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ኪርጊዝስታን፣ ሞንጎሊያ፣ ሲሼልስ፣ ሶማሊያ፣ ታጂኪስታን፣ ቱኒዚያ እና ቬትናም ውስጥ ይገኛሉ።

## 2. ተቋሙ አሁን ያለበት ዓውዳዊ ዕይታ

### 2.1 አስፈላጊነቱ

የታዳሽ ኃይል (RE) ምርት በየዓመቱ እየጨመረ የመሄዱን ያክል፣ ከዓለም አቀፉ የኤሌክትሪክ ኃይል ምርት ድምር አንፃር ሲታይ አሁንም ድረሻው ዝቅተኛ ከመሆኑ ባሻገር የፓሪስ ስምምነትን ዓላማዎች ከማሳካት አኳያ ሲታይ ገና ብዙ ይቀረዋል። በንፋስ፣ በፀሐይ – አንድ ላይ ተለዋዋጭ ታዳሽ ኃይል /Variable Renewable Energy (VRE)/ በመባል የሚታወቁት፣ ባዮጋዝ እና ቆሻሻን ወደ ኤሌክትሪክ ኃይል መለወጥ፣ የባሕር እና አነስተኛ ሃይድሮ ኃይል አቅርቦት የሚገኘው ኤሌክትሪክ ኃይል መጠን በዓለም ዙሪያ በ 2010 ከነበረበት 6 በመቶ በ2018 ወደ 12.9 በመቶ አድጓል። ኃይልን ለማግኘት፣ ኢነርጂ ደኅንነትን ለመጠበቅ እና በፓሪሱ ስምምነት ከተቀመጠው የአካባቢ አየር ለውጥን በ 2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ የማቆም ግምት በታች ለመቆየት መጠነ ሰፋፊ የሆኑ የፀሐይ እና የንፋስ ኃይል ማመንጫዎች ያስፈልጋሉ። በዓለም አቀፉ ኢነርጂ ኤጀንሲ የዘላቂ ልማት መላ ምት (World Energy Outlook 2018) መሠረት በታዳጊ አገሮች ውስጥ በ 2025 ከፀሐይ ኃይል የሚገኝ ኢሌክትሪክ (PV) 950 ጊጋዋት እና ከነፍስ የሚገኝ ኤሌክትሪክ 580 ጊጋዋት ያላቸው ኃይል ማመንጫዎችን ማግኘት ያስፈልጋል። አሁን ካለንበት አቅም አንፃር ሲታይ ተጨማሪ 690 ጊጋዋት ከፀሐይ ብርሃን የሚገኝ ኃይል እና 330 ጊጋዋት ከንፋስ የሚገኝን ኃይል ማግኘት እንደሚያስፈልግ ያመላክታል።

በታዳጊ አገሮች ውስጥ ያለው ውስን አቅም ያለው ወጪ ቆጣቢ ከፀሐይ ብርሃን እና ከንፋስ የሚገኝ የኤሌክትሪክ ኃይል በጉልህ የሚታዩ የቁጥጥር፣ መዋቅራዊ እና የቴክኒክ ችግሮች እንዳሉ ያሳያል። እስካሁን ተለይተው የታወቁት ችግሮች እነዚህ ናቸው፡- (i) ውስን የሆነ የኃይል ማመንጨት እና ማስተላለፍ ዕቅድ አወጣጥ አቅም፤ (ii) ዘላዊነት ያላቸው የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ኢንቨስትመንቶችን አስተባብሮ ወደ ሥራ ማስገባትን የሚገዳደር በቂ ያልሆነ የቁጥጥር ማዕቀፍ፤ (iii) የግል የኃይል አምራቾችን /Independent Power Producers (IPPs)/ ለመምረጥ የሚያስችል ውስን የሆነ የአገልግሎት ግዢ አሠራር ሥርዓት አቅም፤ (iv) ሥራውን ለመሥራት ከመንግሥት ኃላፊነት የሚወስዱ ድርጅቶች ውስን የገንዘብ አቅም፤ እና (v) በተለይ ከሳሀራ በታች ያለው የአፍሪካ ክፍለ አህጉር ውስጥ ባሉት የኃይል ማስተላለፊያ ግሪዶች ምክንያት የተለዋዋጭ ታዳሽ ኃይል (VRE) ግሪድን ከዋናው የኤሌትሪክ መሥመር ጋር ለማጣመር ያሉ ተግዳሮቶች።

ዓለም ባንክ በኢነርጂው ዘርፍ አስተዳደር የድጋፍ ፕሮግራሙ /Energy Sector Management Assistance Program (ESMAP)/ በኩል ለእነዚህ ተግዳሮቶች መፍትሔ ለመስጠት እና ለአገራት ሁሉን አቀፍ የሆነ የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ ለመስጠት የዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራምን /SRMI/ አዘጋጅቷል። ከፈረንሳይ የልማት ድርጅት /Agence Française de Développement (AFD)/፣ ከ ዓለም አቀፉ የታዳሽ ኃይል ኤጀንሲ /International Renewable Energy Agency (IRENA)/ እና ከዓለም አቀፍ የፀሐይ ብርሃን ጥምረት /International Solar Alliance (ISA)/ ትብብር በዓለም ባንክ ለተሳታፊ ወገኖች ኮንፈረስ 2 /COP 24/ በ2018 የተዘጋጀው ከዚህ ቀደም የፀሐይ ብርሃን ስጋትን መፍትሔ መስጫ ፕሮግራም እየተባለ ይታወቅ የነበረው የዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም /SRMI/ የግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚችሉ ዘላቂ የታዳሽ ኃይል ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት እና ተፈጻሚ በማድረግ አገራት ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸው ከፍ ማድረጋቸው እንደተጠበቀ ሆኖ (ከሴቶችን ማብቃት ዕይታ አንጻር ጨምሮ) በሕዝብ የገንዘብ ምንጮች ላይ የመመርኮዛቸውን ሁኔታ ለመቀነስ እንዲችሉ አገራትን የማገዝ ዓላማ አለው።

አሁን ባለው የኮቪድ-19 ወረርሺን የቀውስ ዓውድ ውስጥ የዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም /SRMI/ ልዩ፣ የተቀናጀ እና ሊባዛ የሚችል ዘዴ የግሉን ዘርፍ ኢንቨስትመንቶች በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፉ በማድረግ ዒላማ በተደረጉ ሕዝባዊ ኢንቨስትመንቶች በኩል የአረንጓዴ ኢኮኖሚያዊ ልማትን ማፋጠን እንዲችሉ አገራትን ሊደግፋቸው ይችላል። የዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም (SRMI) ለሚከተሉት የልማት እና የአየር ንብረት ገንዘብ ድጋፍ የማድረግ ዓላማ አለው፡- (i) አገራት በማስረጃ ላይ የተመረኮዙ የተለዋዋጭ ታዳሽ ኃይል (VRE) ዒላማዎችን እንዲያዘጋጁ፣ ዘላቂነት ያለው የታዳሽ ኃይል ፕሮግራምን

ተፈጻሚ እንዲያደርጉ እና በግብይት አማካሪዎች እየታገዙ ጠንካራ የሆኑ የግዢ ሥርዓቶች እንዲኖራቸው ለማድረግ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤ (ii) critical public investments to enable integration of የተለዋዋጭ ታዳሽ ኃይል (VRE) ከዋናው ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር ለማዋሃድ ወሳኝነት ያላቸውው ሕዝባዊ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን መሥራት፣ የፀሐይ ብርሃን/የንፋስ ኃይል ማመንጫ ቦታዎችን መሠረተ ልማቶች በገንዘብ መደገፍ እና የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን መጠን መጨመር፤ እና (iii) በግል ባለሀብቶች የሚፈጠሩ የአደገኛ ተረፈ ምርቶችን ስጋት ለመቀነስ የስጋት እርምጃት እርምጃ መውሰጃ ዘዴዎችን ማቅረብ። ይህ ለታዳሽ ኃይል ልማት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ በመንግስት ከሚሰጥ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ የሥራ አባል፣ ለዜጎች በቀጥታ የሚተላለፉ ጥሬ ገንዘቦች፣ ወይም ለአነስተኛ እና መካከለኛ ደረጃ ኢንተርፐራይዞች የኪሣራ ማካካሻ ድጋፍ ጎን ለጎን ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አሁን ባለንበት ሁኔታ አስፈላጊ ነው።

የዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) በተለይ ለዐሥር አገራት የቴክኒክ እና የፋይናንስ ድጋፍ የማድረግ ዓላማ አለው፤ እነዚህ አገሮችም ኢትዮጵያ፣ ጊኒ ቢሳዎ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ኪርጊስታን፣ ሞንጎሊያ፣ ሲሼልስ፣ ሶማሊያ፣ ታጂኪስታን፣ ቱኒዚያ እና ቬትናም ናቸው። በ 2017 እነዚህ አገሮች ከዓለም የግሪንሃውስ ጋዝ (GHG) ልቀት አጠቃላይ ድምር፣ እንደተለመደው /business as usual (BAU)/ ካለው የቢሆንስ መላ ምት ሲታይ 5 በመቶውን የሚሸፍኑ ሲሆኑ ከ2017 እስከ 2030 ባለው ጊዜ በአማካይ ሁሉም ልቀታቸውን በሦስት እጥፍ ያሳጋሉ ተብሎ ይገመታል። ከዓለም አቀፍ ድጋፍ ጋር፣ ዐሥሩ አገሮች በተለይ የልቀታቸው ዋንኛ ምክንያት በሆነው በኢነርጂው ዘርፍ ላይ የግሪንሃውስ ጋዝ (GHG) ልቀቶችን ለመቀነስ ቁርጠኛ አቋም አላቸው። ሆኖም ግን፣ አሁን ባለው የኮቪድ-19 ቀውስ ምክንያት ይህንን በቁጥጥር ሥር በማዋል አጣዳፊ የአስችኳይ ጊዜ ሁኔታው ውስጥ ተጠምደው ለዚህ ቅድሚያ ሰጥተዋል። ኢኮኖሚያዊ ማገገሙ እንዴት እንደሚዘጋጅ የሚነሣው ጥያቄ ለልቀቶች ቁጥጥር የረዥም ጊዜ አፈጻጸም መርሐግብር ዝግጅት እና ብሔራዊ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መቀነሻ ዕቅድ /Nationally Determined Contributions (NDC)/ ዒላማዎች ሊሳኩ መቻላቸውን ለማወቅ ወሳኝነት አለው። ከፊት ለፊት እየመጣ ያለውን የኢኮኖሚ ቀውስ ለመመከት መንግሥታት የዝቅተኛ ካርቦን ልቀት የልማት ስትራቴጂዎችን እና ፖሊሲዎችን ካላወጡ፣ የጋዝ ልቀቶች ሊያንሠራሩ እና እስከ 2030 የሚኖረው ዝቅተኛ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዳለ ሆኖ በ2030 ልቀቱ ከዚህ ቀደም ይጨምራል ተብሎ ከታሰበው በላይ በከፍተኛ ደረጃ ሊያድግ ይችላል።

ከዚህ የተነሣ በሚገባ ታስቦበት ለአየር ንብረት ጥበቃ የገንዘብ እና ሌላ ድጋፎችን መስጠት ከሚያስችል የመካከለኛ ጊዜ ስትራቴጂ ጋር አረንጓዴ ልማት አራቂ እርምጃዎችን መውሰድ የሚያስችሉ ዘዴዎችን እንዲያዘጋጁ ለፖሊሲ አውጪዎች ድጋፍ መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው።

## 2.2 የተቋሙ ዓላማዎች

የዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

(i) ዝቅተኛ ልቀት ያላቸውን የልማት ጎዳናዎችን ለመከተል እንዲችሉ በታዳጊ አገሮች ውስጥ ያለውን በተቀባዩ የተከናወኑ ፕሮጀክቶች (RE projects) ዘላቂነት ያለው እና የገንዘብ ፍሰቱ ወጥነትና አዋጪነት ያለው መሆን ያለመቻልን ችግር መፍታት፤

(ii) በድኅረ ኮቪድ-19 በሚኖረው የኢኮኖሚ ማገገሚያ እንቅስቃሴ ላይ ቁልፍ የሆነ ድጋፍን ለመስጠት ዒላማ ለተደረጉት አገራት እንደ የአረንጓዴ ልማት ፓኬጅ አንድ አካል ታዳሽ ኃይልን ማጎልበት።

የዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) በተቀባዩ የሚከናወኑ ፕሮግራሞች (RE Programs) በታዳጊ አገሮች ውስጥ የነበሩ ብሔራዊ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ፖሊሲዎች እና የግል ኃይል አማራቾች (IPP) የመረጣ ሂደት ላይ ከነበሩ ስኬቶች እና ውድቀቶች ላይ በመነሣት ትምህርቶችን ይወስዳሉ።

## 2.3 የተቋሙ አጠቃላይ ዕይታ

የግሉን ዘርፍ ኢንቨስትመንት ለማበረታታት እንዲቻል መፍትሔ እንዲሰጣቸው ያስፈልጋሉ ተብለው የታወቁ ዋንኛ መሰናኮች በሁለት ትላልቅ ምድቦች ሊመደቡ ይችላሉ፦ (i) ከግንባታ እና ከክወና በፊት በዝግጅት ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች፣ እና (ii) ፕሮጀክቱ ሥራውን ከጀመረ በኋላ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች። ሁለቱም ዓይነት ስጋቶች በየግል ኃይል ማመንጫ ገንቢዎች (IPPዎች) እና የአበዳሪዎች የካፒታል ወጪ ላይ የተካተቱ ናቸው። እነዚህ ስጋቶች አሁን ባለው ቀውስ ምክንያት ወደ ከፋ ደረጃ ደርሰዋል፣ እና የግል ኢንቨስትመንትን ሚዛን ለመጠበቅ ሁሉን አቀፍ የሆነ ስጋትን መቋቋሚያ ድጋፍን ማቅረብ ያስፈልጋል።

እነዚህን ስጋቶች ለመቋቋም፣ የዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) በሦስት ዋንኛ ክፍለ አካላት ሥር ያሉ እንቅስቃሴዎችን ይደግፋል፣ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፦

a. **ክፍለ አካል 1፦ የቴክኒክ ድጋፍ** – ከተለዋዋጭ ታዳሽ ኃይል (VRE) ውህደት ትንታኔ፣ ከሕጋዊ፣ ከፋይናንሳዊ እና በግብይት ላይ በውድድር ላይ በተመረኮዘ የጨረታ ሥርዓት የግል የኃይል አምራቾች (IPP) ምርጫ በማድረግ ሂደት ላይ የግብይት የምክር አገልግሎት ድጋፍ ጋር የግዢ ድጋፍ መስጠት እና የፀሐይ እና የንፋስ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫዎችን ለወደፊት ለሚኖሩ ተጫራጮች የቴክኒክ እና የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ድጋፍ ጋር በማጣመር ዝቅተኛ ወጪ ያላቸው የኃይል ማመንጨት ዕቅዶችን ለማዘጋጀት በሁሉን አቀፍ እና የተቀናጀ ዕቅድ አወጣጥ ላይ ያተኩራል።

b. **ክፍለ አካል 2፦ የመንግሥት ኢንቨስትመንት** – በፀሐይ እና ንፋስ ኃይል ማመንጫዎች የተለመዱ ዓይነት መሠረተ ልማቶች ላይ መንግስታዊ ኢንቨስትመንቶችን ማከናወን፣ የተለዋዋጭ ታዳሽ ኃይል (VRE) ከዋናው ኤሌክትሪክ ኃይል ግሪድ ጋር ማገናኘት ሥራ ላይ ማሻሻያዎችን ማድረግ (መንግስዊ የሆኑ የባትሪ ማከማቻዎችን ጨምሮ)፣ በአየር ንብረት ለውጥ እና የኤሌክትሪክ ኃይል ስርጭት ላይ በሚኖር መዋዠቅ ወቅት ግሪድ ያለውን የመቋቋም አቅም በማጎልበት የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር አብሮ የሚመጣ ፍላጎትን መቋቋም ላይ ያተኩራል፤ እና

c. **ክፍለ አካል 3፦ ስጋትን መቆጣጠር የሚያስችሉ ዘዴዎች** – ለግል ባለሀብቶች በግሪድ ለተገናኙ እና ከግሪድ ውጭ ላሉ የታዳሽ ኃይል/ማከማቻ መፍትሔዎች የስጋትን መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ማቅረብ ላይ ያተኩራል።

የቴክኒክ ድጋፍ ክፍለ አካሉ የዕቅድ አዘጋጀት ስጋቶችን ለመቀነስ ዘላቂነት ያላቸው የታዳሽ ኃይል (RE) ዒላማዎችን ለማዘጋጀት በአገሪቱ/ማክሮ ደረጃ ያሉ ስጋቶች ላይ ያተኩራል እንዲሁም ዝቅተኛ ልቀት እንዲኖር በሚያስችሉ መንገዶች ላይ በማስረጃ ላይ የተመረኮዙ ዒላማዎችን በማቅረብ፣ የግል የኃይል አምራቾችን (IPP) ጠንካራ እና ግልጽነት በተሞላ ምርጫ በመመረጥ የግዢ ስጋቶችን በመቀነስ እና የመንግሥትን ውስጣዊ አቅም በመጨመር እና በፀሐይ/ንፋስ ኃይል ማመንጫ ግንባታ ውጥኖች ላይ መሬት እና ፈቃዶችን በመስጠት ለግል የኃይል አምራቾች (IPP) የማልማት ስጋቶችን መቀነስ ላይ ያተኩራል። የሕዝብ ኢንቨስትመንት ክፍለ አካሉ በከፍተኛ የተለዋዋጭ ታዳሽ ኃይል (VRE) ከፍተኛ ስርፀት ምክንያት በግሪድ መረጋጋት ላይ ያለ እክል እና ስጋትን መቀነስ የሚቻልባቸውን መንገዶች፣ በአየር ንብረት ለውጥ ወቅት ግሪዱ ያለውን የመቋቋም አቅም በማጎልበት፣ የግል የኃይል አምራቾች (IPP) የሚያስፈልጋቸውን ሕዝባዊ መሠረተ ልማት በገንዘብ መደጎም እና ኤሌክትሪክ የማግኘት ችግር ላለባቸው ሕዝቦች የኤሌክትሪክ መዳረሻ እንዲያገኙ ማድረግ ላይ በማተኮር በግሪዱ እና በመሠረተ ልማት ደረጃ ባሉ ስጋቶች ላይ ያተኩራል። ስጋትን መቆጣጠር የሚያስችሉ ዘዴዎች ክፍለ አካል ወደ ግሪዱ እንዲቀላቀሉ በተደረጉ እና ከግሪድ ውጭ ባሉ የታዳሽ ኃይል በተቀባዩ የተከናወኑ ፕሮጀክቶች (RE projects) ላይ የግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንት ሚዛኑን በዘላቂነት መጠበቅ መቻሉን ለማረጋገጥ በግል ባለሃብቶች ላይ የተጋረጡት የተረፈ ምርት ስጋቶች ላይ ያተኩራል።

በዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም (SRMI Facility) ሥር የሚጠበቁት ዋንኛ ውጤቶች እነዚህ ናቸው፦

a. በግሪድ ውስጥ በገቡ እና ከግሪድ ውጭ በሆኑ ፕሮጀክቶች እና ንቁ ተሳትፎ ያለው የተለዋዋጭ ታዳሽ ኃይል (VRE) ወደ ዋናው ኤሌክትሪክ መሥመር በማስገባት ላይ የግል ኢንቨስትመንትን በመጠቀም ተለዋዋጭ ታዳሽ ኃይል (VRE) አቅምን በሚያሳጉ ኢንቨስትመንቶች የግሪንሃውስ ጋዝ (GHG) ልቀቶችን መቀነስ፣
b. በመንግሥት የገንዘብ አቅም ላይ ያለውን ጫና የሚቀንሱ የግል ኢንቨስትመንቶችን ሚዛንን መጠበቅ፣
c. የግሪድ መቋቋም ችሎታን እንዲሁም በፕሮጀክቶች አካባቢ ያሉ ማኅበረሰቦችን የመቋቋም ችሎታዎች ማሻሻል፣ እና
d. የተቋማዊ እና የቁጥጥር አቅምን ማጠናከር።

የተቋሙ ዋንኛ ዓላማ አገራት ወደ ዝቅተኛ ልቀት መንገዶች እንዲቀየሩ መደገፍ እና ዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ፣ አስተማማኝ፣ ዘላቂነት ያለው እና ዘመናዊ ኢነርጂ ለሕዝባቸው ማቅረብ መቻላቸውን ማረጋገጥ ነው።

## 2.4 የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋት ቁጥጥር የአፈጻጸም ዘዴ

የዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ዘላቂታማነት ማዕቀፍ የስጋት ቁጥጥር የአፈጻጸም ዘዴ ዓላማ የሚከተሉት ናቸው፡-

- የእያንዳንዱን እንደ ሐሳብ የቀረበ ፕሮጀክት አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶችን እና ሊፈጥሩ የሚችሏቸውን ተፅዕኖች መመዘን፤
- እነዚህን ስጋቶች እና የሚያስከትሏቸውን ተፅኖዎች ለማስቀረት፣ ለመቀነስ እና/ወይም ለመቋቋም ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች እንደ ሐሳብ ማቅረብ፤
- በክወናው የትግበራ ደረጃ ላይ የእነዚህን እርምጃዎች አፈጻጸም መከታተል፤
- በፕሮጀክቱ የሕይወት ዑደት ወቅት በሙሉ ቀጣይነት ያለው የባለድርሻ አካል ተሳትፎን ማስቀጠል፤
- ያልታሰቡ ክስተቶች ሲያጋጥሙ በቁጥጥር ሥር ሊውሉ የሚችሉበትን ዘዴ ማመላከት እና፤
- የፕሮጀክቶችን እና ተመሳሳይ ሥራ የሚሠሩ ወገኖችን የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ አፈጻጸምን ጥራት ደረጃ ማሻሻል።

በየዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ሥር ያሉ የሁሉም ፕሮጀክቶች አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋቶች እና ተፅዕኖች በዓለም ባንክ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) መሠረት እየተመዘኑ እንዲተዳደሩ ይደረጋሉ። በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) መሠረት፣ ባንኩ በየዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ሥር ከተበዳሪው ጋር በተወሰነ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ላይ ይስማማል። የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) ለፕሮጀክቱ መዘጋጀት ያለባቸውን የተወሰኑ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ዕቅዶችን እና ሌሎች መሣሪያዎችን ጨምሮ ፕሮጀክቱ በአንድ የተወሰነ ክፍለ ጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶችን (ESSs) ለማሟላት እንዲችል የሚያደርጉ አስፈላጊ የሆኑ ተጨባጭ እርምጃዎች እና ውሳኔዎችን ያስቀምጣል። ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት የሚዘጋጀው ሕጋዊ የስምምነት ውል የሥራ ተቋራጮቹን እና የንኡስ ሥራ ተቋራጮቹን ግዴታዎች በግዢ ጨረታው ሰነዶች እና ውሎች ላይ ማንፀባረቅን ጨምሮ በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) የተጠቀሱትን እርምጃዎች እና ውሳኔዎች ተፈጻሚ ለማድረግ የተበዳሪውን ግዴታዎች የሚያካትት ይሆናል።

በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) ላይ ተለይተው የታወቁትን እርምጃዎች እና ውሳኔዎች ተበዳሪው በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ላይ በተቀመጡት የጊዜ ማዕቀፎች ውስጥ ተፈጻሚ ማድረግ እንዲችል የፕሮጀክት አፈጻጸም ድጋፍ ባንኩ የሚያደርግለት ሲሆን እንደ የፕሮጀክት አፈጻጸም ክትትል እና ሪፖርት አቀራረብ አንድ አካል የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱን (ESCP) አፈጻጸም ሁኔታ የሚገመግም ይሆናል። የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ረቂቁ በተቻለ መጠን ቶሎ ይፋ የሚደረግ ሲሆን ይህም የሚከናወነው እያንዳንዱ ፕሮጀክት ከመመዘኑ በፊት ይሆናል።

የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) እንደ ሐሳብ የሚቀርቡ የፕሮጀክት ማሻሻያዎችን ካለው ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለማስተዳደር ወይም ያልታሰቡ ክስተቶች ሲያጋጥሙ በቁጥጥር ሥር ለማዋል የሚያስችል ሂደትን በውስጡ የሚያካትት ይሆናል። የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) እንዲህ ያሉት ለውጦች ወይም ክስተቶች እንዴት በቁጥጥር ሥር እንደሚውሉ እና ሪፖርት እንደሚደረጉ፣ እንዲሁም እንዴት አስፈላጊ የሆኑት ለውጦች በየአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ እና እንዴት በተበዳሪው የቁጥጥር ዘዴዎቹ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ የሚጠቅስ ይሆናል።

በተመሳሳይ መልኩ፣ ተበዳሪው እንደ ፕሮጀክቱ አንድ አካል የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) እንዲያዘጋጅ ይገደዳል።

## 3. በተቋሙ ሥር የሚከናወን የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋት መቆጣጠሪያ ዘዴ

### 3.1 ሊያጋጥሙ የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች

ከዓለም ባንክ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) ጎን ለጎን፣ በዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ሥር ተገቢ የሆነውን ጥንቃቄ ለማድረግ ከግምት መግባት ያለባቸው ሊያጋጥሙ የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች እንደ የፕሮጀክቱ ተለይተው የሚዘጋጁ ሆነው የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

a. አካባቢያዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፡- (i) በዓለም ባንክ ቡድን አካባቢያዊ፣ ጤና ነክ እና የደኅንነት መመሪያ ደንቦች (EHSGs) ተለይተው የታወቁ፤ (ii) ከማኅበረሰብ ደኅንነት ጋር የተገናኙ፤ (iii) ከአየር ንብረት ለውጥ እና ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወይም ዓለም አቀፍ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ጋር የተገናኙ፤ (iv) በተፈጥሮ ሀብቶች እና እንስሳት እንዲሁም ብዝኃነት ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና ወደ ነበረበት መመለስ ጥረት ላይ ማናቸውንም ተጨባጭ ስጋት የሚያስከትሉ፤ እና (v) የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶች እና እንደ ዓሣ ማስገሪያ ቦታዎች እና የደን ሀብቶች በመሳሰሉ ሕያው የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ጋር የተገናኙ፤ እና

b. ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖች፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፡- (i) የግል፣ የግራ ወይም የአገር ውስጥ ግጭት፣ ወንጀል ወይም ዐመፅ በኩል በሰው ልጅ ደኅንነት ላይ የሚፈጠሩ ስጋቶች፤ (ii) ባላቸው የተለዩ ሁኔታዎች ምክንያት ሊበደሉ ወይም ተጠቃሚ ላይሆኑ የሚችሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ተመጣጥኝ ባልሆነ ደረጃ ፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ሊያሳርፍባቸው እንደሚችል የሚገመቱ ስጋቶች፤ (iii) በተለይ ሊበደሉ ወይም ተጠቃሚ ላይሆኑ እንደሚችሉ ወገኖች ላይ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች የልማት ግብዓቶች እና የፕሮጀክት ጥቅሞችን ማግኘት እንዳይችሉ የሚያግዱ ማናቸውም የተዛቡ አመለካከቶች ወይም መድሎዎች፤ (iv) ከፈቃደኝነት ውጭ መሬት ከመውሰድ ወይም መሬት አጠቃቀም ላይ ገደብ ከመጣል ጋር በተገናኘ የሚፈጠሩ አሉታዊ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎች፤ (v) በአካባቢ የመሬት አጠቃቀም ልማዶች እና የመሬት ይዞታ ሥርዓቶች፣ የመሬት ተደራሽነት እና ተገኝነት፣ የምግብ ዋስትና እና የመሬት ዋጋዎች፣ እና በመሬት እና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ከሚነሱ ግጭቶች ወይም ሽሚያዎች ጋር በተነሣ የሚፈጠሩ ተዛማጅነት ያላቸው ስጋቶችን ጨምሮ (እንደ ተገቢነታቸው) ከመሬት እና ተፈጥሮ ሀብት ይዞታ እና አጠቃቀም ጋር የተገናኙ ስጋቶች ወይም ተፅዕኖዎች፤ (vi) በሠራተኞች እና ከፕሮጀክቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ማኅበረሰቦች ጤና፣ ደኅንነት እና ሰላማዊ ኑሮ ላይ የሚፈጠሩ ተፅዕኖዎች፤ እና (vii) በባህላዊ ቅርስ ላይ የሚኖሩ ስጋቶች።

### 3.2 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) መስፈርቶች

ይህ ክፍል በመቀጠል አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋት ቁጥጥር የሚቀርብለትን የፖሊሲ ማዕቀፍን የሚያብራራ ይሆናል። ይህ የፖሊሲዎች ስብስብ ተዛማጅነት ያላቸውን ሕጎች እና ፖሊሲዎች እንዲሁም የዓለም ባንክን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) የሚሰጡትን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ያካትታል። ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) አንፃር ሲታዩ ብሔራዊ ሕጎች እና ፖሊሲዎች ክፍተት ኖሯቸው በሚገኙበት ጊዜ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) የበላይነት ይኖረዋል።

በዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ሥር በኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ገንዘብ አቅርቦት በኩል በባንኩ በሚደገፉ ፕሮጀክቶች ላይ ያሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎችን ለይቶ ከማወቅ እና ከመመዘን ጋር የተገናኙ መስፈርቶችን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ያስቀምጣሉ። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶችን ለይቶ በማወቅ እና በመቆጣጠር ላይ በማተኮር የእነዚህ መመዘኛ መስፈርቶች አፈጻጸም ለአካባቢው እና ለዜጎቹ ዘላቂነት ባለው መንገድ ተበዳሪዎች ድህነትን ለመቀነስ እና ብልፅግናን ለመጨመር ያስቀመጡትን ግብ እንዲሙቱ ድጋፍ ለማድረግ ትኩረት

ይሰጣል። መስፈርቶቹ፦ (ሀ) ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ዘላቂነት ጋር በተገናኘ ጥሩ ዓለም አቀፍ አሠራር እንዲከተሉ ተበዳሪዎችን መደገፍ፤ (ለ) ተበዳሪዎች ያሉባቸውን ብሔራዊ እና ዓለም አቀፍ የአካባቢ እና ማኅበራዊ ግዴታዎች እንዲወጡ ማገዝ፤ (ሐ) መድልዎ አለማድረግን፣ ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትን እና መልካም አስተዳደርን ማሻሻል፤ እና (መ) ቀጣይነት ባለው የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ አማካይነት የፕሮጀክቶችን ዘላቂ የልማት ውጤቶች ማሻሻል። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) በሁለቱም ቁሳዊ ኢንቨስትመንት እና የቴክኒክ ድጋፍ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

ዐሥሩ የአካባቢ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች በዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ሥር በፕሮጀክቱ የሕይወት ዘመን ዑደት ላይ በሙሉ ለታሰቡ ፕሮጀክቶች የሚከተሉትን ተገቢነት ያላቸው መመዘኛ መስፈርቶችን ያስቀምጣሉ፦

a. **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1)፦ የአካባቢ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ምዘና እና ቁጥጥር።** በኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ገንዘብ አቅርቦት በኩል በባንኩ በሚደገፉ ፕሮጀክቶች ላይ ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ጋር በሚጣጣም መልኩ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ውጤቶችን ለማግኘት በእያንዳንዱ የፕሮጀክቱ ደረጃ ላይ ግንኙነት ያላቸውን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች በተመለከተ ተበዳሪው ያለበትን የመመዘን፣ የመቆጣጠር እና የመከታተል ግዴታዎችን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1) ያስቀምጣል።

b. **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2)፦ ሠራተኛ እና የሥራ ቦታ ሁኔታ።** አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2) ድህነትን ለመቀነስ እና ሁሉን አካታች የሆነ ኢኮኖሚያ ዕድገት እንዲገኝ የሥራ ፈጣራ ዕድል እና ገቢ መፍጠር ያላቸውን አስፈላጊነት ዕውቅና ይሰጣል። ተበዳሪዎች ጥሩ የሆነ የሠራተኛ እና የአስተዳደር ግንኙነትን ማበረታታት ይቻላሉ እንዲሁም በፕሮጀክቱ ውስጥ ያሉትን ሠራተኞች በፍትሐዊ መንገድ በመያዝ እና ለደኅንነት አስተማማኝ እና ጤናማ የሥራ ቦታ ሁኔታዎችን በመፍጠር የፕሮጀክቱን የልማት ጥቅማ ጥቅሞች ከፍ ወዳለ ደረጃ ማሸጋገር ይችላሉ።

c. **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 3 (ESS3)፦ የግብዓት ውጤታማ አጠቃቀም እና የብክለት መከላከል እና ቁጥጥር ሥራ።** አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 3 (ESS3) ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እና ከተሜነት ብዙውን ጊዜ የአየር፣ የውሃ እና የመሬት ብክለትን ሊፈጥሩ እንደሚችሉ እና የሰዎችን ሕይወት፣ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎቶችን እና አካባቢን በአካባቢ፣ በክፍለ አህጉር እና በዓለም አቀፍ ደረጃዎች ስጋት ላይ ሊከት በሚችል ደረጃ ግብዓቶችን እንዲጠቀሙ ዕውቅና ይሰጣል። አሁን ላይ ያለው እና ወደፊት ይኖራል ተብሎ የሚገመተው የግሪንሃውስ ጋዝ (GHG) በአየር ድባብ ላይ ያለው ክምችት አሁን ያለውን እና ወደፊት የሚመጠውን ትውልድ ደኅንነትን ስጋት ውስጥ የሚከቱ ናቸው። በተመሳሳይ ጊዜ፣ ይበልጥ ውጤታማ እና ጠንቃቃ የግብዓት አጠቃቀም፣ ብክለትን መከላከል እና የግሪንሃውስ ጋዝ (GHG) ከመልቀቅ መቆጠብ፣ እና ማስተካከያ ቴክኖሎጂዎች እና አሠራር ልማዶች ይበልጥ ተደራሽ እና ሊሳኩ የሚችሉ እየሆኑ በመሄድ ላይ ናቸው።

d. **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 4 (ESS4)፦ የማኅበረሰብ ጤና እና ደኅንነት።** አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 4 (ESS4) የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች፣ መሣሪያዎችና ማሽኖች እና መሠረተ ልማቶች ማኅበረሰብ ለስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ያለውን ተጋላጭነት ሊጨምሩ እንደሚችሉ ዕውቅና ይሰጣል። ከዚህ በተጨማሪ፣ በአየር ንብረት ለውጦች ምክንያት በሚፈጠሩ ተፅዕኖዎች ተጎጂ የሆኑ ማኅበረሰቦች በፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ምክንያት ተፅዕኖዎቹ በበለጠ ፍጥነት ሊባባሱባቸው ወይም ሊከፉባቸው ይችሉ ይሆናል።

e. **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS5)፦ መሬትን ማግኘት፣ በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦች እና በፈቃደኝነት ላይ ያልተመሠረተ ሰፈራ።** አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS5) ከፕሮጀክት ጋር በተገናኘ የሚኖር የመሬት ማግኘት እና በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦች በማኅበረሰቦች እና በግለሰቦች ላይ መጥፎ ተፅዕኖ ሊያሳርፉ እንደሚችሉ ዕውቅና ይሰጣል። ከፕሮጀክት ጋር በተገናኘ

የሚኖር የመሬት ማግኘት እና በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦች አካላዊ መፈናቀል (ወደ ሌላ ቦታ መዛወር፣ መኖሪያ ቦታን ማጣት ወይም መጠለያን ማጣት)፣ ኢኮኖሚያዊ መፈናቀል (የመሬት፣ የእሴት ወይም ወደ እሴቶች መዳረሻ መነጠቅ፣ በዚህም የገቢ ምንጮችን ወይም ሌሎች ኑሮን ማሸነፊያ ዘዴዎችን ማጣት)፣ ወይም ሁለቱንም ሊያስከትሉ ይችላሉ። "በፈቃደኝነት ላይ ያልተመሠረተ ሰፈራ" የሚለው ቃል እነዚህን ተፅዕኖዎች ይመለከታል። አንድ ሰፈራ በፈቃደኝነት ላይ ያልተመሠረተ እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠረው በመፈናቀል ምክንያት ተፅዕኖ ያረፈባቸው ግለሰቦች ወይም ማኅበረሰቦች የመሬት መወሰዱን ወይም በመሬት አጠቃቀም ላይ የተጣሉትን ገደቦች ለመቃወም ሳይችሉ የሚቀሩበት ሁኔታ ሲኖር ነው።

f. **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 6 (ESS6)፡- የብዝኃ ሕይወት ጥበቃ እና የሕያው የተፈጥሮ ሀብቶች ዘላቂነት ያለው አስተዳደር።** አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 6 (ESS6) ለብዝኃነ ሕይወት ጥበቃ ማድረግ እና ጠብቆ ማቆየት እንዲሁም ሕያው የተፈጥሮ ሀብቶችን ማስተዳደር ለዘላቂ ልማት መሠረታዊ አስፈላጊ ነገሮች እንደሆኑ ዕውቅና ይሰጣል። ብዝኃ ሕይወት በኢንተር አሊያ፣ በየመሬት፣ በየባሕር እና ሌላ በየውሃ ሥርዓተ ምህዳሮች እንዲሁም እነዚህ አንድ አካል የሆኑባቸው በሥርዓተ ምህዳራዊ ውስብስባዊ ደረጃዎች፣ ይህም በዝርያዎች ብዝኃ ሕይወት፣ በዝርዎች እና በሥርዓተ ምህዳሮች መካከል ያለውን ውስብስብት ደረጃ የሚያካትት ሆኖ ከሁሉም ሕይወት ያላቸው ምንጮች የተገኙ ሕያው ኦርጋኒዝሞች ላይ ያለው ልዩነት እንደሆነ ተደርጎ ይተረጎማል። ብዝኃ ሕይወት ብዙውን ጊዜ በሰዎች ልጆች ዋጋ የሚሰጣቸውን ሥርዓተ ምህዳራዊ አገልግሎቶችን አስፈላጊ መሠረት ይጥላል። በብዝኃ ሕይወት ላይ የሚያርፉ ተፅዕኖች በዚህ ምክንያት በአብዛኛው የሥርዓተ ምህዳር የሚያቀርባቸው አገልግሎቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ።

g. **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7)፡- የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ በአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች።** አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7) በአንድ ተለይቶ የታወቀ የተወሰነ ልዩ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ቡድን ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። እንዲህ ላሉት ቡድኖች ጥቅም ላይ የሚውለው ቃል ከአገር ወደ አገር ይለያያል፣ አብዛኛውን ጊዜ በብሔራዊ ደረጃ ከግምት ውስጥ የሚገቡ ነገሮችን ያንፀባርቃል። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7) ተለይተው የታወቁ ቡድኖች በተለያዩ አገሮች በተለያዩ ስያሜዎች ሊታወቁ እንደሚችሉ ከግምት በማስገባት "የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ በአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች" የሚለውን መጠሪያ ስም ይጠቀማል። እንዲህ ያሉት መጠሪያ ስሞች "ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ በአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች"፣ "የአካባቢው ተወላጅ ጎዳጣኖች"፣ "ጥንታዊ ሰዎች/ አቦርጂኖች"፣ "በኮረብታ ላይ የሚኖሩ ነገዶች"፣ "ለጥቃት የተጋለጡ እና የተገለሉ ቡድኖች"፣ "ጎዳጣን ዜጎች"፣ "ተለይተው የተያዙ ነገዶች"፣ "የመጀመሪያዎች የአገሬው ሰዎች" ወይም "የጎሣ ቡድኖች" የሚሉ ስያሜዎችን ያካትታሉ። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7) በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7) የተቀመጡትን መስፈርቶች እስካሟሉ ድረስ እንዲህ በመሳሰሉት በሁሉም ቡድኖች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል። ለዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ዓላማዎች፣ "የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ በአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች" የሚለው አባባል እንዲህ ያሉትን ሁሉንም አማራጭ ቃላት ያካትታል።

h. **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 8 (ESS8)፡- ባህላዊ ቅርስ።** አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 8 (ESS8) ባህላዊ ቅርስ ባለፈው፣ አሁን ባለው እና ወደፊት በሚኖረው መካከል ተጨባጭ እና ተጨባጭ ባልሆኑ መንገዶች የሕይወት ቀጣይነት እንደሚያረጋግጥ ዕውቅና ይሰጣል። ሰዎች ባህላዊ ቅርስን በቀጣይነት እያደጉ የሚሄዱ እሴቶቻቸውን፣ እምነቶቻቸውን፣ ዕውቀታቸውን እና ወግና ልማዳቸውን እንደሚያንፀባርቅላቸው እና እንደሚገለጽላቸው ያምናሉ። ከበርካታ መገለጫ መንገዶቹ ጋር ባህላዊ ቅርስ እንደ ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው ሳይንሳዊ እና ታሪካዊ መረጃ፣ እንደ ለልማት ጠቃሚ የሆነ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ እሴት እና እንደ የሰዎች ባህላዊ ማንነት እና የአኗኗር ዘይቤና ሥርዓት አንድ ቁልፍ አካል እንደ መሆኑ መጠን አስፈላጊ ነው። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ

መስፈርት 8 (ESS8) በፕሮጀክቱ የሕይወት ዑደት ወቅት በሙሉ ባህላዊ ቅርሶችን ለመጠበቅ የሚያስችሉ እርምጃዎችን በግልጽ ያስቀምጣል።

i. **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 9 (ESS9)፡- የፋይናንስ ድርጅቶች።** አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 9 (ESS9) ጠንካራ የአገር ውስጥ ካፒታል እና ገንዘብ ነክ ገበያዎች እና ለፋይናንስ የሚኖር ተደራሽነት ለኢኮኖሚ ልማት፣ ዕድገት እና ለድህነት ቅነሳ አስፈላጊ እንደሆኑ ዕውቅና ይሰጣል። ባንኩ ዘላቂነት ያለውን የፋይናንሱ ዘርፍ ልማት ለመደገፍ እና የአገር ውስጥ ካፒታል እና ገንዘብ ነክ ገበያዎች ያላቸውን ሚና ማላቅ ላይ ድጋፍ ለመስጠት ቁርጠኛ አቋም አለው። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 9 (ESS9) በዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ሥር ላሉ ፕሮጀክቶች ተዛማጅነት ይኖረዋል ተብሎ አይጠበቅም።

j. **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS10)፡- የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ እና መረጃን ይፋ ማውጣት።** አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS10) እንደ ጥሩ ዓለም አቀፍ አሠራር አንድ አስፈላጊ አካል በተበዳሪ እና በፕሮጀክት ባለድርሻ አካላት መካከል ክፍት እና ግልጽ የሆነ ግንኙነት መኖሩ አስፈላጊ እንደሆነ ዕውቅና ይሰጣል። ውጤታማ የሆነ የባለድርሻ አካል ተሳትፎ የፕሮጀክቶችን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ዘላቂነት ሊያሻሻል፣ የፕሮጀክት ተቀባይነትን ከፍ ሊያደርግ፣ እና በፕሮጀክት ዲዛይን እና አፈጻጸም ላይ ጉልህ አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል።

አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1) የሚከተሉትን አስፈላጊነት ይደነግጋል፡- (ሀ) የፕሮጀክቱን ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች መፍትሔ በመስጠት ረገድ ተበዳሪው አሁን ያለው የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ፤ (ለ) የአንድ ፕሮጀክት ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ለይቶ ለማወቅ የተቀናጀ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ሁኔታ ምዘና፤ (ሐ) ከፕሮጀክት ጋር የተገናኘ መረጃ ይፋ በማድረግ፣ በምክክር እና ውጤታማ የግብረ መልስ አቀባበል በኩል ውጤታማ የማኅበረሰብ ተሳትፎ መኖር፤ እና (መ) በፕሮጀክቱ የሕይወት ዑደት ላይ በሙሉ በተበዳሪው የሚከናወን የአካባቢ እና የማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ቁጥጥርና ክትትል። ባንኩ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1) መሠረት እንደ ተከናወኑ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናዎች አንድ አካል ሁሉም የፕሮጀክቱ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች መፍትሔ እንዲሰጣቸው ይፈልጋል።

ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 እስከ 10 (ESS2–10) ያሉት ተበዳሪው የተለየ ትኩረት ማግኘት ሊያስፈልጋቸው የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎች ለይቶ በማወቅ እና መፍትሔ በመስጠት ላይ ያሉበትን ግዴታዎች ያስቀምጣሉ። እነዚህ መስፈርቶች ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎችን ለማስቀረት፣ ለመቀነስ፣ እና መፍትሔ ለመስጠት እንዲሁም ቀሪ በጉልህ የሚታዩ ተፅዕኖዎች ሲኖሩ ደግሞ ለእነዚህ ተፅዕኖዎች ማካካሻ ወይም መፍትሔ ለመስጠት ያለሙ ዓላማዎችን እና ግዴታዎችን ያስቀምጣሉ።

## 3.3 በፕሮጀክቶች ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች እና መፍትሔ እርምጃዎች

ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ዓይን ሲታይ ከግምት የሚገቡት ዋንኛ ገጽታዎች እንደሚከተለው በአጭሩ ቀርበዋል። ሆኖም ግን፣ በዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ሥር ያለ እያዳንዱ ፕሮጀክት በፕሮጀክቱ ዝግጅት ወቅት የሚሟላ የራሱ የሆነ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ምዘና ይኖረዋል። ከእነዚህ ፕሮጀክቶች መካከል ጥቂቶቹ ብቻ ከተለዋዋጭ ታዳሽ ኃይል (VRE) የሚገኘውን ጊጋዋት በዋናው የኤሌክትሪክ መሥመር ላይ አስገብቶ ለመጠቀም እስከ 500 ኪሎቮልት ለሚሆኑት መሥመሮች ብቻ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ የሚያልሙ እንደ መሆናቸው፣ እነዚህ ፕሮጀክቶች እንደ ተቋሙ /Facility/ አካልነታቸው ምድብ ሀ /Category A/ ደረጃ በዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ተቋም (GCF) ምደባ መሠረት

ይሰጣቸዋል እና በዓለም ባንክ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) ምደባ መሠረት ደግሞ ከፍ ያለ ወይም ጉልህ ቦታ ያለው ደረጃ ሊያገኙ ይችላሉ።

### 3.3.1 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1)

ፕሮጀክቶቹ ታዳሽ ኃይልን ጥቅም ላይ የማዋል ሁኔታን በመጨመር ከፍተኛ ዋጋ ያለው የአካባቢ ተጠቃሚነትን ያስገኛሉ ተብለው ይገመታሉ። በኤሌክትሪክ ቅይጥ ማመንጫዎች ውስጥ ወደ ታዳሽ ኃይል በከፍተኛ መቶኛ ድርሻ ላይ ለመድረስ የሚደረገው ሽግግር ግሪንሃውስ ጋዝ (GHG) ልቀቶችን፣ የአየር እና የውሃ ብክለት እንዲሁም የውሃ ሀብቶች አጠቃቀም በተመለከተ ለአገራት የሚሰጠው ጥቅም አለው። ፕሮጀክቶቹ የግንባታ ሥራ ዕድሎችን ጨምሮ ከፍተኛ የሥራ ዕድልን ሊያስገኙ እንደሚችሉ ይገመታል፤ ይህ የሥራ ዕድል ሁኔታ ከክዋኔ እና ጥገና (O&M) እንቅስቃሴዎች ጋር በተገናኘ መጠኑ አነስተኛ የሆኑ ለረዥም ጊዜ የሥራ ዕድልን ሊፈጥሩም ይችላሉ። እነዚህ ዕድሎች በሥልጠና እና በድጎማዎች አማካይነት ለሴቶች የሚሰጡ (ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ) የሥራ ዕድሎችን ለማበረታታት የሚያስችሉ ትላልቅ ዕድሎች ናቸው።

በአግባቡ ካልተያዘ፣ የፀሐይ/ንፋስ ኃይል መመንጫዎች መሠረተ ልማት ተዋረዳዊ ልማት እንዲሁም የታዳሽ ኃይል (RE) ማመንጫዎች ግንባታ እና ሥርዓተ ክወና የመሬት ልወጣን (እና የመሬት ጥራት ደረጃ ማሽቆልቆልን)፣ የዕፅዋት እና እንስሳት ከቦታው መጥፋትን፣ በተለይ በቆላማ አካባቢዎች ከፍተኛ የውሃ አጠቃቀምን፣ በፎቶቮልታይክ ሶላር ሴሎች እና የንፋስ ተርባይኖች ማመምረቻ ቦታዎች ላይ አደገኛ የሆነ ቆሻሻ አወጋገድን፣ እና የፀሐይ ብርሃን ባትሪ ድንጋዮችን መጣልን፣ እና በሠራተኛ እና በማኅበረሰብ ጤና እና ደኅንነት ላይ አደጋን ማስከተልን ሊያመጡ ይችላሉ። ሆኖም ግን፣ እነዚህ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተፅዕኖዎች ካላቸው ስርጭት ደረጃ/ጉልህነት አኳያ ሲታዩ ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ደረጃ የሚመደቡ ናቸው፣ ብሎም ሊቀለበሱ እና ከአካባቢው ጋር በቀላሉ እንዲጣጣሙ ሊደረጉ የሚችሉ ናቸው፤ ይህም በመሆኑ በቀላሉ መከላከል ይችላል፣ ለምሳሌ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) መስፈርቶች መሠረት የማመንጫ ቦታ መረጣን ማከናወን እና መፍትሔ አሰጣጥ ለምሳሌ በሥርዓተ ክወና ወቅት ተቀባይነት ያላቸውን የአሠራር ልማዶችን ተግባራዊ በማድረግ።

### 3.3.2 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2)

የፕሮጀክት ሠራተኞች በሁሉም በእነዚህ ፕሮጀክቶች ላይ እንዲንቀሳቀሱ ይደረጋሉ ተብሎ ይጠበቃል። ተበዳሪው ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት በሚዘጋጁት በየሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) ላይ በተጠቀሰው የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2) ተገዢ መሆን አለበት። የሥራ አካባቢ ደኅንነት እና ጤንነት (OHS) ዕቅዶች በዓለም ባንክ ቡድን የአካባቢ ጤና እና ደኅንነት (EHS) መመሪያዎች መሠረት መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

ሥራና ሠራተኛን የሚመለከተው ችግር ዓይነት የሥራ ቦታ ሁኔታዎችን፣ ጤናን፣ ደኅንነትን፣ ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ጥቃትን (GBV)፣ ግጭትን ወዘተ ጨምሮ በፕሮጀክት ሠራተኞች ላይ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው ማኅበረሰቦች ላይ ጭምር ከባድ ተፅዕኖዎችን ሊፈጥር ይችላል። እነዚህ ስጋቶች በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ምዘና አንድ አካል ሆነው ሊፈተሹ እና በሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) እና ሌሎች አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነዶች አማካይነት ሊመሩና ሊተዳደሩ ይገባል። ሁሉም ተዛማጅነት ያላቸው እርምጃዎች በጨረታ እና በውል ሰነዶች ላይ የሚንፀባረቁ ይሆናሉ።

ለፕሮጀክት ሠራተኞች የተዘጋጀ የቅሬታ አፈታት ዘዴ በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ሥር መዘጋጀት ይኖርበታል። ይህ ዘዴ ከአጠቃላዩ የፕሮጀክት የቅሬታ አፈታት ዘዴ የተነጠለ ነው።

### 3.3.3 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 3 (ESS3)

እንደ ሐሳብ የቀረበው ተቋም /Facility/ ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 3 (ESS3) ጋር በከፍተኛ ደረጃ ተዛማጅነት ያለው ነው። በመሆኑም የኢነርጂ ውጤታማ ቴክኖሎጂዎች እና ሥራ ሂደቶች፣ ኢነርጂን ማቀቢያ ኢንቨስትመንት፣ የታዳሽ ኃይል (RE) ምርጥ የአሠራር ልማዶች፣ እና ግሪንሃውስ ጋዝ (GHG) ቅነሳ ጥቅማ ጥቅሞች በፕሮጀክቱ ዲዛይን እና በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) መሣሪያ ዘዴዎች ላይ ይንፀባረቃሉ።

ከውሃ እጥረት (በተለያየ ወቅት የሚገኝ ውሃን እና በውሃ ፍላጎት መብዛት ምክንያት የሚፈጠሩ ማናቸውም ድምር ተፅዕኖዎች ጨምሮ)፣ ከበካይ ነገሮች ልቀት፣ ቆሻሻን ማመንጨት፣ እንደ ቆሻሻ የተጣሉ ማቴሪያሎች እና አደገኛ ቆሻሻ አጠቃቀም፣ በማኅበረሰቦች ላይ ከሚደርሱ ተፅዕኖዎች እና የግብዓት ወይም የአህበት አጠቃቀም ውጤታማነት ጋር የተገናኙ ተዋረዳዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ውስጥ እየተፈተሹ ይመዘናሉ። ሆኖም ግን እነዚህ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አብዛኛዎቹ ተፅዕኖዎች ካላቸው ስርጭት ደረጃ/ጉልህነት አኳያ ሲታዩ ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ደረጃ የሚመደቡ ናቸው፣ ብሎም ሊቀለበሱ እና ከአካባቢው ጋር በቀላሉ እንዲጣጣሙ ሊደረጉ የሚችሉ ናቸው፤ እና በመሆኑም በቀላሉ መፍትሔ ሊያገኙ ይችላሉ።

የፀሐይ እና የንፋስ ኃይል ማመንጫዎችን በመገንባት ሥራ ወቅት፣ አንዳንድ ሊያጋጡ የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎች ሊኖሩ ይችላሉ፤ እነዚህ ተፅዕኖዎችም በግንባታ እንቅስቃሴዎች ወቅት የሚፈጠር አቧራ እና የታመቀ የተቃጠለ አየር ልቀት ምክንያት የአየር ጥራት ደረጃ ማሽቆልቆልን ያካትታሉ። እነዚህ ተፅዕኖዎች ተገቢነት ያላቸው ፍተሻና ምዘናዎችን ማድረግ እና በቁጥጥር ሥር ለማዋል አስተዳደራዊ እርምጃዎችን መውሰድ ይጠይቃሉ። በኮንስትራክሽን እና በሥርዓተ ክወና ወቅት ተፈጻሚ የሚሆኑ የቆሻሻ እና የብክለት ቁጥጥር ዕቅዶች ይህን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) መስፈርቶችን ለማሟላት እንዲችሉ ተደርገው ይዘጋጃሉ።

### 3.3.4 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 4 (ESS4)

አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 4 (ESS4) የሚያስቀምጣቸው መስፈርቶች በእያንዳንዱ ፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ላይ የሚኖራቸው ተፈጻሚነት ከግምት ውስጥ ይገባሉ። የፀሐይ ብርሃን/ንፋ ማመንጫዎች ኮንስትራክሽን እና ሥርዓተ ክወና ሁለቱንም በመደበኛ ሥርዓተ ክወና ወቅት የሚያጋጥሙ አደጋዎችን እና ድንገተኛ ያልተጠበቁ አደጋዎችን ጨምሮ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች አሉ፤ በሌሎች የኢነርጂ ማመንጫ ተቋሞች (ለምሳሌ ሃይድሮፓወር) ከሚያጋጥሙ አደጋዎች አንፃር ሲታይ በእነዚህ ላይ ያጋጠሙ ምንም አስከፊ አደጋዎች የሉም። በሚሠሩ የኮንስትራክሽን ማሽኖች እና ተዛማጅነት ያላቸው ትራንስፖርት እንቅስቃሴዎች የሚፈጠሩ የድምፅ ልቀቶች ምክንያት የሚፈጠር ማኅበረሰብን ሊያበሳጩ የሚችሉ ሁኔታዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ተፅዕኖዎችን በቁጥጥር ሥር ለማዋል ተገቢነት ያለውን ምዘና ማድረግ እና አስተዳደራዊ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል። ሥራ ተቋራጮች በፕሮጀክት ትግበራ እና በሥርዓተ ክወና ወቅት በተቻለ መጠን ዝቅተኛ ሁከት መኖሩን ለማረጋገጥ የትራፊክ አስተዳደር ዕቅዶችን የማዘጋጀት ኃላፊነትን ይወስዳሉ።

እነዚህ እና ሌሎች በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 4 (ESS4) መሠረት መፍትሔ ማግኘት ያላባቸው ሊያጋጥሙ የሚችሉ የማኅበረሰብ ጤና ተፅዕኖዎች በነጻነት በራስ በሚዘጋጁ ዕቅዶች ወይም በፕሮጀክቱ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ሥር ክትትል ሊደረግባቸው ይችላል።

### 3.3.5 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS5)

ለፀሐይ እና ንፋስ ኃይል ማመንጫዎች የመሬት ፍላጎቶች በጣም ከፍተኛ ናቸው። በተገቢነት ያለው ጥንቃቄ አደራረግ እና በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS5) መሠረት በተዘጋጁ ዕቅዶች ላይ በመመርኮዝ የመሬት ማግኛ ወጪዎችን ለማስቀረት፣ ለመቀነስ፣ መፍትሔ ለመስጠት እና ካሳ ለመክፈል እንዲቻል ማናቸውም ሊያጋጥሙ የሚችሉ የመሬት ማግኛ ወይም የመሬት አጠቃቀም ገደቦች ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS5) መስፈርቶች ጋር በሚጣጣም መልኩ ምዘና ተደርጎባቸው አስፈላጊው ክትትል ይደረግባቸዋል።

የሰፈራ ፖሊሲ ማዕቀፍ ጠቋሚ ቢጋር በዓባሪ 5 ላይ ተሰጥቷል። ለባንኩ አጥጋቢ እና ተጨባጭ በሆነ መልኩ ተበዳሪዎች ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS5) መስፈርቶች ጋር በሚጣጣም መልኩ እንደ የፕሮጀክቱ የተዘጋጀ የሰፈራ ፖሊሲ ማዕቀፎችን እና/ወይም የሰፈራ የድርጊት መርሐ ግብሮችን ማዘጋጀት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።

### 3.3.6 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 6 (ESS6)

በአግባቡ ካልተዘጋጁ እና ቦታ ካልተመረጠላቸው በቀር እንደ ሐሳብ የቀረቡት የፀሐይ/የንፋስ ኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች የዕፅዋት እና የእንስሳት ከቦታው መጥፋት፣ ማሽቆልቆል ወይም መበታተን እንዲሁም በብዝኃ ሕይወት እና ሕያው የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ሌሎች አስከፊ ተፅዕኖዎች ሊፈጥሩ ይችላሉ። እንዲህ ያሉት ፕሮጀክቶች በተፈጥሮ ሀብቶች፣ በመሬት እና በውሃ ሥርዓተ ምህዳር እና ዝርያዎች ላይ የሚያስከትሉት ተፅዕኖ በሚገባ መፈተሻቸውን፣ መመዘናቸውን እና በሚገባ በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊው ጥንቃቄ ይደረጋል። ሁሉም ፕሮጀክቶች በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 6 (ESS6) ተገዢነትን ለማረጋገጥ እንዲቻል የሚወሰዱ እርምጃዎችን ያካትታሉ።

### 3.3.7 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7)

በፕሮጀክቱ የሚገኝበት አካባቢ የአካባቢ ተወላጆች (IP) መኖር ወይም ከቦታው ጋር በጋራ ያላቸው ትስስር እና ቅርርብ ከብሔራዊ ባለሥልጣናት ጋር በመመካከር አስቀድሞ በባንኩ የሚታይ እና ችግር እንደሌለው የሚረጋገጥ ይሆናል። አንድ ጊዜ ማረጋገጫ ከተሰጠው በኋላ፣ ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7) ዓላማዎች እና መስፈርቶች ጋር በሚጣጣም መልኩ የአካባቢው ተወላጆች ልማት ዕቅድ ወይም ሌላ በአገሪቱ እና በፕሮጀክቱ ዓውድ ላይ በመመርኮዝ ሌላ ዓይነት ዕቅዶች፣ እንዲሁም በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7) ላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ውስጥ በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ ጨምሮ በፕሮጀክቱ ዲዛይን እና በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነዶች ላይ የሚካተት ይሆናል።

### 3.3.8 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 8 (ESS8)

ፕሮጀክቱ የፕሮጀክቱን አካባቢ ይቃኝ እና በሁለቱም የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች ላይ ፕሮጀክቱ ሊኖረው የሚችለው ተፅዕኖን ይመዝናል።

የእያንዳንዱ ፕሮጀክት ቦታ መረጣ የባህል ቅርሶችን እና የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 8 (ESS8) ተፈጻሚነትን ከግምት ስለማስገባቱ በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ውስጥ በተጨማሪ የሚፈተሽ እና የሚመዘን ይሆናል። በሲቪል ኮንስትራክሽን የሚሠራባቸው ቦታዎች ላይ ምንም ዓይነት በግልጽ የሚታይ ባህላዊ ቅርስ ከሌለ፣ የተገኘው ልዩ ዕድል የተጣራበት አሠራር ሂደት በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነዱ ላይ የሚካተት ይሆናል።

### 3.3.9 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 9 (ESS9)

ፕሮጀክቶቹ የፋይናንስ አቅራቢ ፕሮጀክቶች እንዲሆኑ አይጠበቅባቸውም።

### 3.3.10 አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS10)

ባለድርሻ አካላት በፕሮጀክት ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ማኅበረሰቦች ወይም ግለሰቦች እንዲሁም የእነርሱን መደበኛ እና ኢመደበኛ ተወካዮች፣ ብሔራዊ ወይም የአካባቢ የመንግሥት ባለሥልጣናትን፣ ፖለቲከኞችን፣ የሃይማኖት ወይም የማኅበረሰብ ድርጅቶችን እና ልዩ ፍላጎት፣ አካዳሚያዊ ማኅበረሰቦች እና ንግድ ድርጅቶች የያዙ የሲቪል ማኅበረሰብ ቡድኖችን ሊያካትቱ ይችላሉ። በፕሮጀክት ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ወገኖች (ግለሰቦች ወይም ቡድኖች) ለይቶ ማወቅ ሥራው በተጨማሪ ለምሳሌ በፕሮጀክቱ ተፅዕኖዎች ከሌሎች ይልቅ ይበልጥ ከፉኛ ሊጎዱ የሚችሉ እና/ወይም በፕሮጀክቱ ጥቅማ ጥቅሞች ተጠቃሚ ለመሆን ከሌሎች ይልቅ ውስን የሆነ አቅም ያላቸው የመሳሰሉ ባላቸው ሁኔታ ሊበደሉ ወይም ለጥቃት ሊጋለጡ የሚችሉትን ወገኖች የሚያካትት ይሆናል።

በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ካረፈባቸው እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር ግልጽነት እና ትርጉም ያለው ምክክር መኖሩን ለማረጋገጥ እንዲቻል የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ይዘጋጃል። የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና ምክክሮች በፕሮጀክቱ የሕይወት ዑደት ወቅት በሙሉ የሚከናወኑ ይሆናሉ። ይህ በፕሮጀክት ዲዛይን እና ተፅዕኖዎች እንዲሁም በዝግጅት ደረጃ ወቅት እንዚህ ጉዳዮች ላይ ከበርካታ ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደረጉ ውይይቶችን ያካትታል። የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ከሌሎች አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) መሣሪያዎች ጋር በአንድነት በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS10) ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት ሕዝባዊ ምክክር የማድረግን እና መረጃን ይፋ ማድረግን ያስገድዳሉ እንዲሁም በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት እንደ አስፈላጊነቱ በመደበኛነት እንደሚሻሻል ሕያው ሰነድ የሚታዩ ይሆናሉ።

## 4. በፕሮጀክት ዝግጅት እና ትግበራ ወቅት አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋት ቁጥጥር

በዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ሥር ያሉት ዐሥር አገሮች ፕሮጀክቶች ከልይታ እስከ ፅንሰ ሐሳብ ድረስ በተለያየ የፕሮጀክት ዝግጅት ደረጃ ላይ ላይ ያገኛሉ። ከዚህ በታች የቀረበው ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት መወሰድ የሚገባውን ዋንኛ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) የጥንቃቄ አደራረግ እርምጃዎች በባንኩ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ፖሊሲ እና እንዲሁም በኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፋይናንስ አደራረግ ላይ ባለው ፖሊሲ መሠረት ያቀርባል።

### 4.1 የፕሮጀክት ዝግጅት

ባንኩ በተቋሙ (Facility) ሥር በኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፋይናንስ በኩል በፖሊሲዎቹ እና በአሠራር ሥርዓቶቹ መሠረት ድጋፍ ለሚሰጣቸው ለሁሉም እንደ ሐሳብ የቀረቡ ፕሮጀክቶች አስፈላጊ የሆነውን የአካባቢ እና ማኅበራዊ ጥንቃቄን ያደርጋል። የአካባቢ እና ማኅበራዊ አስፈላጊ ጥንቃቄ ማድርግ ዓላማ ባንኩ ኣንደ ሐሳብ ለቀረበው ፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ የሚያስፈልገው ስለ መሆኑ ከውሳኔ ላይ ለመድረስ እና ድጋፉ እንዲሰጥ ከተወሰነ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች በምዘና፣ በማልማት እና በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት የሚስተናገዱበትን መንገድ ባንኩ ማወቅ እንዲችል ለማገዝ ነው።

የባንኩ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስፈላጊ ጥንቃቄ እንደ ፕሮጀክቱ ተፈጥሮ እና ደረጃ ተገቢነት ያለው ሆኖ በዚሁ ተመጣጣኝ የሆነ የአካባቢ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎችን በደረጃቸው ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤ በዚህም በመፍትሔ አሰጣጥ ተዋረድዊ ሰንሰለት ከግምት የሚገባ ይሆናል። ይህ ተገቢነት ያለው ጥንቃቄ አንድ ፕሮጀክት በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) መሠረት ለመዘጋጀት እና ለመተግበር አቅም ያለው መሆኑን ይመዝናል።

የባንኩ ተገቢነት ያለው ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነቶች እንደተገቢነቱ የሚከተሉትን የሚያካትት ይሆናል፡- (ሀ) ከፕሮጀክቱ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖች ጋር በተገናኘ በተበዳሪው የቀረበውን መረጃ መገምገም እና ባንኩ የሚፈልገውን ተገቢነት ያለው ጥንቃቄን ማድረግ ግዴታውን እንዳይወጣ የሚከላከሉ የመረጃ ክፍተቶችን ለማሟላት ተበዳሪውን ተጨማሪ መረጃ እንዲያቀርብ መጠየቅ፤ እና (ለ) ተበዳሪው በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) መሠረት ለአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች መፍትሔ ለመስጠት ከሚያስችሉ የመፍትሔ መስጫ ተዋረዳዊ ሰንሰለት ጋር በተጣጣመ መልኩ አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች ማዘጋጀት እንዲችል ተበዳሪውን ለማገዝ መመሪያ መስጠት። ባንኩ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) መሠረት ያለበትን የአካባቢ እና ማኅበራዊ ተገቢነት ያለው ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነቱን መወጣት እንዲችል ተበዳሪው ለባንኩ የተሰጡ መረጃዎች በሙሉ ተዛማጅነት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት።

በፅንሰ ሐሳብ ደረጃ ላይ እያለ ባንኩ የአካባቢ እና ማኅበራዊ ግምገማ ማጠቃለያ (ESRS) የሚያዘጋጅ እና በይፋ የሚገልጽ ሲሆን በዚህ ሰነድ አማካይነትም የፕሮጀክቱን ዓይነት እና ወሰን፣ ያሉትን ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች፣ የሚደረግለት የአካባቢ እና የማኅበራዊ ምዘና ዓይነት እና ምዘናው የሚደረግበት ጊዜያዊ የጊዜ ማዕቀፍ የተመለከተ መረጃን የሚሰጥ ይሆናል። ይህ የባለድርሻ አካላትን ማንነት ያልተጣራ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ እና ባለድርሻ አካላት የሚኖራቸው ተሳትፎ ምን ዓይነት እንደሆነ የሚያሳይ መረጃን ያካትታል። በፅንሰ ሐሳብ ደረጃ ላይ፣ ማለትም በአካባቢ እና ማህበራዊ ግምገማ ማጠቃለያ (ESRS)፣ ባንኩ ሁሉንም ፕሮጀክቶች ካሉት አራት የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) ምድቦች ወደ አንዱ ይመድባቸዋል፡-

- ከፍተኛ፣
- ግምት የሚሰጠው፣
- መካከለኛ እና
- ዝቅተኛ።

አግባብነት ያለውን የስጋት ምድብ በመወሰን ላይ፣ እንደ ዓይነት፣ መገኛ ቦታ፣ አደገኝነት፣ እና የፕሮጀክቱን ደረጃ፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበርዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ተፈጥሮዋዊ ባሕሪ እና መጠነ ስፋት፣ እና ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ጋር በሚጣጣም መልኩ የአካባቢ እና ማኅበራዊ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎችን ለመቆጣጠር (ሌላ ማናቸውም በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ላይ ኃላፊነት ያለው አካልን ጨምሮ) ተበዳሪው ያለው ቁርጠኝነት የመሳሰሉ ተዛማጅነት ያላቸውን ጉዳዮች ባንኩ ከግምት ያስገባል። እንደ አንድ የተወሰነ ዓይነት ፕሮጀክት እና ፕሮጀክቱ በሚለማበት ዓውድ ላይ የሚወሰን ሆኖ ሌሎች የስጋት አካባቢዎች ላይ ያሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መፍትሔ መስጫ እርምጃዎች እና ውጤቶች ተዛማጅነት ሊኖራቸው ይችል ይሆናል። እነዚህ ሕጋዊ እና ተቋማዊ ሁኔታዎችን ከግምት ማስገባት፣ የመፍትሔ አሰጣጡ ተፈጥሯዊ ባሕሪ እና እንደ ሐሳብ የቀረበው ቴክኖሎጂ ዓይነት፣ የአስተዳደር መዋቅሮች እና ሕግ አወጣጥ፤ እና ከመረጋጋት፣ ከግጭት ወይም ከፀጥታ ጋር ግንኙነት ያላቸው ከግምት የሚገቡ ሁኔታዎችን ያካትታሉ። ባንኩ ፕሮጀክቱ የተሰጠውን ምደባ እና ምደባው የተደረገበትን ምክንያት በባንኩ የድር ጣቢያ እና በፕሮጀክት ሰነዶች ውስጥ ይፋ ያደርጋል።

በትግበራ ወቅት ጨምሮ ባንኩ ለፕሮጀክቱ የተመደበውን የስጋት ደረጃ በመደበኛነት የሚገመግም ይሆናል እንዲሁም ፕሮጀክቱ ላሉበት ሊያጋጥሙ የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች አግባብነት ያለው ሆኖ መቀጠሉን ለማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የተደረገውን ምደባ ይለውጠዋል። በምደባው ላይ የሚደረጉ ማናቸውም ለውጦች በባንኩ የድርጣቢያ ላይ የሚታዩ ይሆናሉ።

ባንኩ በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ላይ የሚያከናውነውን ምዘና ከመጀመሩ በፊት እንዲህ ላለው ፕሮጀክት የአካባቢ እና ማኅበራዊ ግምገማ ማጠቃለያ (ESRS) የምዘና ደረጃ ያዘጋጃል እና ከዚህ ሰነድ ጋር አያይዞ ከፕሮጀክቱ የአካባቢ እና ማኅበራዊ ምዘና ጋር በተገናኘ ተበዳሪው ያቀረባቸውን ማናቸውንም ሰነዶች ይፋ ያደርጋል። ረቂቁ ሰነድ የፕሮጀክቱን ቁልፍ የሆኑትን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች በበቂ ዝርዝሮች ለይቶ ያሳያል እንዲሁም ተንትኖ ያቀርባል። የቁልፍ ግኝቶች እና እንደ ሐሳብ የቀረቡ የመፍትሔ እርምጃዎች አጭር ማጠቃለያ ጨምሮ እንዲህ ስላሉት ስጋቶች እና ተፅዕኖች በተመለከተ ትክክለኛ እና ተዛማጅነት ያለው መረጃ ይሰጣል። የረቂቅ ሰነዱ ክፍሎች በኋላ ላይ የሚዘጋጁ በሚሆኑበት ጊዜ፣ የሚከናወኑ ማናቸውንም ጥናቶች ወይም ምዘናዎች ጨምሮ ረቂቁ ሰነድ ምን ሊደረግ እንደታሰበ የሚያሳይ ቢጋር በውስጥ ይኖረዋል፣ ይህም በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ላይ የሚመዘገብ ይሆናል። ለግምገማና ምዘና፣ ተበዳሪው የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) እና የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ያዘጋጃል። የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) ከስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን እርምጃዎች እና ውሳኔዎች ለማጎልበት እና ለመተግበር ተበዳሪው ሊጠቀምባቸው የሚችሉ የተለያዩ የአስተዳደር መሣሪያዎችን (ዘዴዎችን) ያብራራል። እነዚህ የአስተዳደር ዘዴዎች ወይም መሣሪያዎች እንደ ተገቢነቱ የአካባቢ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶችን፣ የአካባቢ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ማዕቀፎችን፣ የሥራ ክንውን ፖሊሲዎች፣ የሥራ ክንውን የጽሑፍ መመሪያዎች (ማኑዋሎች)፣ የአስተዳደር ሥርዓቶች፣ አፈጻጸም ሥርዓቶች፣ የአሠራር ልማዶች እና ካፒታል ኢንቨስትመንቶችን የሚያካትቱ ይሆናሉ። በፕሮጀክቱ የሕይወት ዑደት ላይ እንዳለ በየአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) መሠረት አግባብነት ያላቸው ሕጎች እና ደንቦች እንዲሁም አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) የሚያስቀምጧቸውን መስፈርቶች ለማሟላት እንዲቻል ሁሉም የአስተዳደር መሣርያዎች የመፍትሔ አሰጣጥ ተዋረዳዊ ሰንሰለት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ እንዲሁም መፍትሔ እርምጃዎችን ያካትታሉ። ሁለቱም ዝግጁ አብነቶች (ቴምፕሌቶች) በዓባሪዎች ውስጥ ቀርበዋል። ሌላ ማናቸውም የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) መሣሪያ ከተዘጋጀ ከምዘናው በፊት ይፋ የሚሆን ይሆናል።

## 4.2 የፕሮጀክትትግበራ

የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱን (ESCP) ጨምሮ ባንኩ የፕሮጀክቱን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አፈጻጸም በሕጋዊ ስምምነቱ በተቀመጡ መስፈርቶች መሠረት ክትትል የሚያደርግበት ሲሆን በፕሮጀክት ዲዛይን ወይም በፕሮጀክት ተጨባጭ

ሁኔታዎች ላይ በሚያጋጥሙ ለውጦች ምክንያት የሚፈጠሩ ለውጦችን ጨምሮ ማናቸውንም የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱን (ESCP) ይገመግምዋል። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አፈጻጸም ረገድ ባንኩ የሚያደርገው ክትትል እና የክትትል ሁኔታ ሊያጋጥሙ ከሚችሉት የፕሮጀክቱ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል። በኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፋይናንስ አቀራረብ ላይ በባንኩ ፖሊሲ እና አፈጻጸም ሥርዓት ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች ላይ በመመርኮዝ ባንኩ ፕሮጀክቶችን በቀጣይነት ክትትል ያደርግባቸዋል። የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱን (ESCP) ጨምሮ በሕጋዊ ስምምነቶች ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት የተበዳሪውን የክትትል ሪፖርቶች መገምገም የሚያካትት የፕሮጀክቱን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አፈጻጸም በተመለከተ ባንኩ የአፈጻጸም ድጋፍን ይሰጣል።

## 5. የመረጃ ይፋ አወጣጥ፣ የባለ ድርሻ አካላት እና የቅሬታ አፈታት ዘዴ

### 5.1 የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ እና መረጃን ይፋ ማውጣት

በተለየ ወይም ርትዓዊ ባልሆነ መንገድ በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ቡድኖች የተለዩ ፍላጎቶች ወይም (እንደ አካል ጉዳት፣ መሃይምነት፣ ሥርዓተ ጾታ፣ የቋንቋ ወይም የተደራሽነት ልዩነቶች የመሳሰሉ) የተለየ የመረጃ ማግኘት ፍላጎት ያላቸውን ቡድኖች ከግምት በማስገባት ዒላማ ለተደረጉ ማኅበረሰቦች እና ለሰፊው ሕዝብ በሚገባው ቋንቋ እና ተደራሽ በሆነ ቅርጸት ተዘማጅነት ያለው መረጃ ይፋ ይሆናል። ባለድርሻ አካላት የፕሮጀክቱን ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች መረዳት እንዲችሉ፣ ተጋላጭ እና ተበዳይ የሆኑ ቡድኖችን ርትዓዊ ባልሆነ መንገድ ተፅዕኖ ሊያሳርፉባቸው የሚችሉ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎችን ትኩረት በመስጠት እና ተፅዕኖዎቹን ለማስቀረት እና ለመቀነስ ወይም መፍትሔ ለመስጠት ስለ የሚወሰዱ የተለያዩ እርምጃዎች በማብራራት የፕሮጀክት መረጃ ይፋ እንዲሆን ይደረጋል።

ባለድርሻ አካላት በፕሮጀክት ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ማኅበረሰቦች ወይም ግለሰቦች እንዲሁም የእነርሱን መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ተወካዮች፣ ብሔራዊ ወይም የአካባቢ የመንግሥት ባለሥልጣናትን፣ ፖለቲከኞችን፣ የሃይማኖት ወይም የማኅበረሰብ ድርጅቶችን እና ልዩ ፍላጎት፣ አካዳሚያዊ ማኅበረሰቦች እና ንግድ ድርጅቶች የያዙ የሲቪል ማኅበረሰብ ቡድኖችን ሊያካትቱ ይችላሉ። በፕሮጀክት ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ወገኖች (ግለሰቦች ወይም ቡድኖች) ለይቶ ማወቅ ሥራው በተጨማሪ ለምሳሌ በፕሮጀክቱ ተፅዕኖዎች ከሌሎች ይልቅ ይበልጥ ከፉኛ ሊጎዱ የሚችሉ እና/ወይም በፕሮጀክቱ ጥቅማ ጥቅሞች ተጠቃሚ ለመሆን ከሌሎች ይልቅ ውስን የሆነ አቅም ያላቸው የመሳሰሉ ባላቸው ሁኔታ ሊበደሉ ወይም ለጥቃት ሊጋለጡ የሚችሉትን ወገኖች የሚያካትት ይሆናል። እንዲህ ያለው ግለሰብ/ቡድን በምክክር ሂደቱ ላይ ሳይሳተፍ እንዲቀር ሊደረግ/ ወይም ሙሉ በሙሉ ተሳትፎ ላይኖረው ይችል ይሆናል፤ ይህ እንዳይሆን ለማድረግ የተወሰኑ እርምጃዎችን እና/ወይም ድጋፍ መስጠትን ያስፈልገው ይሆናል። ብዙውን ጊዜ በዒላማ የተደረገ አገሮች ውስጥ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ሴቶች እንዳይካተቱ ሊደረጉ ስለሚችሉ ለእነርሱ ልዩ ትኩረት በመስጠት ሰፊ እና ሁሉንም በፕሮጀክቱ አካባቢዎች ውስጥ ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ያቀፈ ተሳትፎ መኖሩን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። እንዲህ ያለው ተሳትፎ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7) ላይ በተጠቀሰው መሠረት በአካባቢው ተወላጆች ላይ መጥፎ ተፅዕኖ የሚፈጠርበት ክስተት ሲያጋጥም ለባህል ተገቢውን ግምት የሰጠ አቀራረብ በመጠቀም እና በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) አማካይነት የሚከናወን ይሆናል። ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖችን ካሉበት ቦታ ድረስ መቅረብ ዒላማ በማድረግ ማኅበረሰቦች የፕሮጀክቱን ጥቅሞች ማግኘት የሚችሉባቸው አማራጮች ይሰጧቸዋል።

ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት ሙሉ የባለ ድርሻ አካላት ትንታኔ ይከናወናል። ለባለድርሻ አካል ልየታ የሚሰጠው ትንታኔ ደረጃ ሊያጋጥሙ በሚችሉ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ባላቸው ደረጃ ልክ መረጃ የሚያገኝ ይሆናል። የባለድርሻ አካላት ትንታኔ በሁሉም የፕሮጀክቱ ክፍለ አካላት ላይ የሚከናወን ይሆናል።

ባልተጣራ በመጀመሪያ ደረጃ ምዘና ወቅት በሚገኝ መረጃ በዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም (SRMI) ፕሮጀክቶች ተፅዕኖ ያርፍባቸዋል ተብለው የሚጠበቁ የባለድርሻ አካል ቡድኖች የሚከተሉት ሲሆኑ ሰፋ ያለ የባለድርሻ አካላት ትርጓሜ ከዚህ በላይ ቀርቧል፦

a. ከፕሮጀክቱ በቀጥታ እና/ወይም በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ የሚሆኑ ሰዎች፣ ማኅበራዊ ቡድኖች፣ እና ድርጅቶች። እነዚህ ዒላማ የተደረጉ ተጠቃሚዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦ (i) ለግሪድ ግንኙነት እና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ፕሮጀክቶች አዳዲስ ደንበኞች ሊሆኑ የሚችሉ፣ (ii) የፕሮጀክቱ ሠራተኞች ሊሆኑ የሚችሉ።

b. በመጥፎ ሁኔታ ተፅዕኖ ሊደርስባቸው የሚችሉ ማኅበረሰቦች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡- (i) ተፅዕኖ ያረፈባቸው የመሬት ባለቤቶች/ማኅበረሰቦች (ii) የአካባቢ ተወላጅ ሰዎች ያሉባቸው ማኅበረሰቦች። በአካባቢው ካሉ ግለሰቦች እና ማኅበረሰቦች ጋር ባለድርሻ አካላትን ለማሳተፍ የሚደረገው ጥረት በዋንኛነት በማኅበረሰብ ተወካዮች (የመንደር አለቆች፣ የጎሣ መሪዎች፣ የማኅበረሰብ እና የሃይማኖት መሪዎች፣ የአካባቢ የመንግሥት ተወካዮች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ተወካዮች) ላይ የሚወሰን በሚሆንበት ጊዜ፣ እንዲህ ያሉት ግለሰቦች የእነዚያን ግለሰቦች ማኅበረሰቦች አመለካከቶችና አስተያየቶች በተጨባጭ የሚወክሉ መሆኑን ለማረጋገጥ እና የመልእክት ልውውጡን ተገቢነት ባለው መንገድ እያሳለጡ እንዳሉ ለማረጋገጥ ጥረቶች የሚደረጉ ይሆናል።

c. ጉዳዩ የሚመለከታቸው ቡድኖች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡- (i) የአካባቢው የመንግሥት ኤጀንሲዎች፣ (ii) መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/መያዶች፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች (CSOs) እና ሌሎች በተለዋዋጭ ታዳሽ ኃይል (VRE) ላይ የሚሠሩ የልማት ተቋማት፣ (iii) የአካባቢ ተወላጆችን የሚወክሉ ድርጅቶች፣ እና (iv) የግል ኩባንያዎች።

d. አስፈጻሚ ኤጀንሲዎች እና የአካባቢ እና ማኅበራዊ ስጋቶችን ለመቆጣጠር ሥልጣን ያላቸው ኤጀንሲዎች በንኡስ ፕሮጀክት ትግበራ ላይ ተፅዕኖ መፍጠር እና ውሳኔዎችን መወሰን የሚችሉ ተቋማትን እና ኤጀንሲዎችን ያካትታሉ። እነዚህ ቡድኖች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡- (i) የማዕከላዊ መንግሥት ኤጀንሲ፣ እና (ii) ንኡስ-ብሔራዊ መንግሥት። የተሳትፎዋቸው ደረጃ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች ቁጥጥር ላይ ባላቸው የየራሳቸው ሚና እና ሥልጣኖች ላይ የሚመረኮዝ ይሆናል።

## 5.2 የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) የቅሬታ አፈታት ዘዴዎች

በዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ሥር እንደ ሐሳብ የቀረበ ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት በተዘጋጀ የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP)) አንድ አካል፣ በፕሮጀክት ተፅዕኖ ያረፈባቸው ማኅበረሰቦችን እንዲሁም በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ሊያርፍባቸው የሚችሉ ወይም ከፕሮጀክቱ እንቅስቃሴዎች ጋር በተገናኘ ፕሮጀክቱ የሚመለከታቸው ሰፋ ያሉ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳስቧቸውን ነገሮች እና ቅሬታዎች ለመቀበል እና መፍትሔ አሰጣጥን ለማሳለጥ የቅሬታ አፈታት ዘዴ (GRM) ተዘጋጅቶ በእያንዳንዱ ፈጻሚ ኤጀንሲ አማካይነት ይተገበራል። የቅሬታ አፈታት ዘዴ (GRM) ዓላማ በአጠቃላይ አነጋገር የሚከተለው ነው፡- (ሀ) ለተጠቃሚዎች ያለውን ተጠያቂነት ማጠናከር፤ እና (ለ) ከፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ጋር በተገናኘ ግብረመልስ ለመስጠት እና/ወይም አቤቱታዎችን ማቅረብ። የቅሬታ አፈታት ዘዴ (GRM) ችግሮች ተለይተው እንዲታወቁ እና በተቀናጀ እና ሳይዘገይ በወቅቱ መፍትሔ መስጠት በሚያስችል መንገድ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ተደራሽ እና አስተማማኝ የሆነ ዘዴን ለማቅረብ የተዘጋጀ ነው እንዲሁም በሥራ ላይ ያሉ መደበኛ ወይም ኢ-መደበኛ የቅሬታ አቀራረብ ዘዴዎችን የሚጠቀም ይሆናል። ይህ ዘዴ ጥቅሙ አቤቱታዎችን ለመቀበል እና ለመመዝገብ ብቻ አይደለም ይልቁንስ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የአንድ አቤቱታ መፍትሔ ለመስጠት እና ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የደረሰበትን ደረጃ መልሶ መልእክቱን ማስተላለፍን ያካትታል።

የቅሬታ አፈታት ዘዴ (GRM) የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡-

a. ተጠቃሚዎች ቅሬታቸውን ማስገባት የሚችሉባቸው የተለያዩ መንገዶች፤ እነዚህም በአካል ተገኝቶ፣ በስልክ፣ በጽሑፍ መልእክት፣ በደብዳቤ፣ በኢሜይል ወይም በድር ጣቢያ ወዘተ ቅሬታን ማስገባት ሊያካትቱ ይችላሉ፤

b. ቅሬታዎች በጽሑፍ የሚመዘገቡበት መዝገብ እና እንደ የመረጃ ቋት (ዳታቤዝ) የሚቀመጡበት መዝገብ፤

c. ያቀረቡት አቤቱታ ለሚመለከተው አካል እንደደረሰ የሚያውቁበት፣ መልስ የሚያገኙበት እና ለቅሬታቸው መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉበት ጊዜ መቼ ሊሆን እንደሚችል የጊዜውን ርዝመት የሚጠቅሱ ለሕዝብ በማስታወቂያ ማስነገሪያ መንገዶች የተዋወቁ የአሠራር ሥርዓቶች፤

d. ስለ ቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት፣ በበላይነት የሚያስተዳድረው መዋቅር እና ውሳኔ ሰጪዎችን በተመለከተ ግልጽነት፤

e. የቅሬታው መፍትሔ እንደተጠበቀው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር አርኪ መልስ ያልተገኙባቸው ቅሬታዎች ይግባኝ የሚጠይቁበት የይግባኝ መጠየቂያ ሂደት ሊመላከት ይችላል።

f. ተጠቃሚዎች በቀረበው መፍትሔ ሐሳብ ሳይረኩ ሲቀሩ ድርድር እንደ መፍትሔ ሐሳብ ሆኖ ይቀርባል።

## 5.3 የዓለም ባንክ የቅሬታ አፈታት ዘዴ አገልግሎቶች

ዓለም ባንክ በሚደግፋቸው ፕሮጀክቶች (ማናቸውም በዘላቂ ታዳሽ ኃይል አደጋ ስጋት ቅነሳ ፕሮግራም ተቋም (SRMI Facility) ሥር ሊኖር የሚችል ዕጩ ፕሮጀክትን ጨምሮ) ክፉኛ ጉዳት ደርሰቦናል ብለው የሚያምኑ ማኅበረሰቦች እና ግለሰቦች አቤቱታቸውን አሁን ላይ ወዳለው በፕሮጀክት ደረጃ ያለ የቅሬታ አፈታት ዘዴዎች ወይም በዓለም ባንክ (WB) የቅሬታ አፈታት አገልግሎት (GRS) በኩል ማስገባት ይችላሉ። የቅሬታ አፈታት አገልግሎት (GRS) የመጡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ከፕሮጀክት ጋር ግንኙነት ያላቸው አሳሳቢ ሁኔታዎች መፍትሔ እንዲያገኙ በፍጥነት ግምገማ የተደረገባቸው መሆኑን ያረጋግጣል። በፕሮጀክት ተፅዕኖ ያረፈባቸው ማኅበረሰቦች እና ግለሰቦች አቤቱታቸውን ለዓለም ባንክ (WB) ገለልተኛ የምርመራ ፓናል ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን ይህም ፓናል በዓለም ባንክ (WB) ፖሊሲዎች እና አፈጻጸም ሥርዓቶች ላይ ጥሰት በመፈጸሙ ምክንያት ጉዳት መድረሱን ወይም ሊደርስ መቻሉን በማጣራት ውሳኔ ላይ ይደርሳል። አቤቱታዎች ዓለም ባንክ ትኩረቱን እንዲያገኝ በቀጥታ ከተደረገ እና የባንኩ አስተዳደር ምላሽ እንዲሰጥ ዕድሉ ከተሰጠው በኋላ በማናቸውም ጊዜ ለፓናሉ ሊቀርቡለት ይችላሉ። ለዓለም ባንክ ኮርፖሬት የቅሬታ አፈታት አገልግሎት (GRS) እንዴት አቤቱታን ማስገባት እንደሚቻል መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ይህን ይጎብኙ፦ http://www.worldbank.org/en/projects-operations/products-and-services/grievance-redress-service. ለዓለም ባንክ የምርመራ ፓናል እንዴት አቤቱታዎችን ለማስገባት እንደሚቻል መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ይህን ይጎብኙ፦ http://www.worldbank.org/en/projects-operations/products-and-services/grievance-redress-service.

## ዓባሪ 1፡- የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ግዴታ ዕቅድ ጠቋሚ ዝግጅ አብነት (ቴምፕሌት)

**[የተበዳሪው ስም/የፕሮጀክት አስፈጻሚ አካል]**

**[የፕሮጀክት አርዕስት እና ቍጥር]**

**[ረቂቅ/ድርድር የተደረገበት/የተሻሻለው]**

የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP)

**[ቀን]**

1. [*የተበዳሪው ስም*] የ [*ስም*] ፕሮጀክት (ከዚህ በመቀጠል **ፕሮጀክት** በመባል የተጠቀሰው) የሚከተሉትን ሚኒስቴር *መሥሪያ ቤቶች/ኤጀንሲዎች/አሃዶች ጋር* [*ይተገብራል*] [*በመተግበር ላይ ነው*]፡- [*ስም*] [*ሌሎች ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች/ኤጀንሲዎች/ተሳትፎ የሚያደርጉ ሌሎች አሃዶችን ይከትቱ*]። የ [*የዳግም ግንባታ እና ልማት ዓለም አቀፍ ባንክ/ዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር*] (*ከዚህ በመቀጠል* [*ባንኩ/ማኅበሩ በመባል የተጠቀሰው*) ለፕሮጀክቱ ፋይናንስ ለማቅረብ [*ተስማምቷል*] [*ሊያቀረብ ነው*]።

2. ፕሮጀክቱ በአካባቢያዊ እና *ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች* **(ESSs)** *መሠረት ተፈጻሚ እንዲሆን* [*የተበዳሪው ስም*] *ተጨባጭ እርምጃዎችን ይወስዳል። ይህ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴት ዕቅድ* **(ESCP)** *ተጨባጭ እርምጃዎችን፣ ማናቸውንም ተለይተው የተቀመጡ ሰነዶችን ወይም ዕቅዶችን፣ እንዲሁም የእነዚህን የእያንዳንዳቸውን ጊዜ መርሐ ግብር ያስቀምጣል።*

3. [*የተበዳሪ ስም*] በተጨማሪ በ አካባቢያዊ እና *ማኅበራዊ ማዕቀፍ* (ESF) *ሥር ያሉ እዚህ ላይ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ* (ESCP) *በሚሉ የተጠቀሱ እንደ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች* (ESMP)፣ *የዳግም ማቋቋም ዕቅዶች* (RAP)፣ *የአካባቢ ተወላጆች ዕቅዶች* (IPPs)፣ *የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ* (SEP) *የመሳሰሉ በሌሎች ማናቸውም የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ* (E&S) *አስፈላጊ ሰነዶች እና በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ* (E&S) *ሰነዶች ላይ የተጠቀሱ የጊዜ ገደቦች ላይ ተገዢ ይሆናል።*

4. [*የተበዳሪ ስም*] የተወሰኑ እርምጃዎች ትግበራ ከላይ በ 1 ላይ በተጠቀሰው ሚኒስቴር *መሥሪያ* ቤት፣ ኤጀንሲ ወይም *አሃድ የሚፈጸም እንኳ ቢሆን የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ* (ESCP) *ሁሉም መስፈርቶች ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለበት።*

5. በዚህ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ *ግዴታ ዕቅድ* (ESCP) *የተቀመጡ ተጨባጭ እርምጃዎች ትግበራ* ክትትል እየተደረገበት ለ [*ባንክ/ማኅበር*] በ [*ተበዳሪ ስም*] በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ *ግዴታ ዕቅድ* (ESCP) ላይ በተቀመጡት *መስፈርቶች* እና በሕጋዊ ስምምነቱ *ግዴታዎች መሠረት ሪፖርት ይደረጋል።* [*ባንክ/ማኅበር*] የተጨባጭ እርምጃዎቹን ግስጋሴ እና ተፈጻሚነት በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ሂደት ላይ በሙሉ ክትትል እያደረገ ይመዘናቸዋል።

6. በ [*ባንክ/ማኅበር*] እና [*ተበዳሪ ስም*] መካከል በተደረሰው ስምምነት *መሠረት፣* በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ወቅት የፕሮጀክቱን ለውጦች እና ያልተጠበቁ ክስተቶች ከፕሮጀክቱ *ጋር ተጣጥመው መመራታቸውን ለማንፀባረቅ ወይም* በራሱ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ *ግዴታ ዕቅድ* (ESCP) *ሥር* የሚከናወነውን የፕሮጀክት አፈጻጸም ምላሽ ለመስጠት *ሲባል ይህ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ* (ESCP) *ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊሻሻል ይችላል።* እንዲህ ባሉ *ሁኔታዎች*

ውስጥ፣ [*የተበዳሪ ስም/ ወይም ተወካይ(ዮች)*] ለውጦቹን ከ [*ባንክ/ማኅበር*] ጋር ሆኖ ለማድረግ የተስማማ ሲሆን እና እነዚህን ለውጦች እንደሚያንፀባርቁ አድርጎ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱን (ESCP) በወቅቱ ያሻሽለዋል። በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) ላይ የሚደረጉ ለውጦች ላይ የሚደረስ ስምምነት በ [ባንክ/ማኅበር] እና በ [*ተበዳሪ ስም/ ወይም ተወካይ(ዮች)*] መካከል በተፈረመባቸው የደብዳቤ ልውውጦች አማካይንት በሰነድነት የሚያዝ ይሆናል። [*የተበዳሪው ስም/ ወይም ተወካይ(ዮች)*] ወዲያውኑ የተሻሻለውን የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ይፋ ያደርጋሉ።

7. የፕሮጀክት ለውጦች፣ ቀደም ሲል ያልታሰቡ ያጋጠሙ ክስተቶች ወይም በፕሮክቱ ትግበራ ወቅት በስጋቶቹ እና በተፅዕኖዎቹ ላይ ለውጦችን ማድረግ የሚያስገድድ የፕሮጀክት አፈጻጸም ሲኖር፣ [*ተበዳሪ ስም*] አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እንዲህ ያሉትን ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች መፍትሔ ለመስጠት ተጨማሪ ገንዘብ ሊያቀርብ ይችላል፤ ይህም [*እንደ የአካባቢ፣ የጤና እና የደኅንነት ተፅዕኖዎች ፣ የሠራተኛ እና ሥራ ችግሮች፣ ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ጥቃት የመሳሰሉ ከፕሮጀክቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች በግልጽ ያስቀምጡ*] ሊያካትት ይችላል።

| ተጨባጭ እርምጃዎች እና ውሳኔዎች | | የጊዜ ማዕቀፍ | ኃላፊነቱን የሚወስደው ባለሥልጣን |
|---|---|---|---|
| **ክትትል እና ሪፖርት አደራረግ** | | | |
| ሀ | **መደበኛ ሪፖርት አደራረግ**<br>[አካባቢያዊ፣ ማኅበራዊ ፣ ጤና እና ደኅንነት (ESHS)) አፈጻጸም ክትትል ሊደረግበት እና ለዓለም ባንክ ሪፖርት ሊደረግ ይገባል። ይህ በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ላይ መንፀባረቅ ይኖርበታል፤ ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌ ይመልከቱ]<br><br>በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ላይ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ትግበራ፣ በየአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ሥር አስፈላጊ ናቸው በተባሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነዶች ላይ ያለውን ዝግጅት እና ትግበራ ወቅታዊ አቋም፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች፣ የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ(ዎች) ጨምሮ ሆኖም ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን አካባቢያዊ፣ ማኅበራዊ ፣ ጤና እና ደኅንነት (ESHS)) በተመለከተ መደበኛ የክትትል ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለ [ባንክ/ማኅበር] ማስገባት። | *[ሪፖርት የሚደረግበትን ድግምግሞሽ መጠን ይጠቁሙ፤ ለምሳሌ በፕሮጀክቱ ትግበራ ሂደት ወቅት በየሩብ ዓመቱ፣ በየስድስት ወሩ፣ በየዓመቱ]።* | |
| ለ | **ክስተቶች እና አደጋዎች**<br>[የአጋጣሚዎች እና አደጋዎችን ማሳወቅ ተግባር በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1) ሥር አስፈላጊ የሆነ መስፈርት ነው። ከዚህ በታች የተሰጠውን ምሳሌ ይመልከቱ]።<br><br>በአካባቢ፣ ተፅዕኖ በሚያርፍባቸው ማኅበረሰቦች፣ በሕዝቡ ወይም ሠራተኞች [ይህንን ጨምሮ] [ለክወናው ዓይነት ተገቢነት ባለው መልክ የአጋጣሚዎቹን እና አደጋዎቹን ምሳሌዎች ይጥቀሱ] ጉልህ የሆነ አሉታዊ ተፅዕኖ ያላቸውን ወይም ሊኖራቸው የሚችሉ ከፕሮጀክቱ ጋር ግንኙነት ያለውን ማናቸውንም አጋጣሚ ወይም አደጋ ለ [ባንኩ/ማኅበሩ] በአፋጣኝ ማሳወቅ። የተወሰዱ አፋጣኝ እርምጃዎችን ወይም ለችግሩ መፍትሔ ለመስጠት ሊወሰዱ የታቀዱ እርምጃዎችን በመጠቆም እና በማናቸውም ሥራ ተቋራጭ እና ሥራውን በበላይነት የሚመራው አካል እንደ ተገቢነቱ የቀረበ ማናቸውንም መረጃ በማካተት ስለ አጋጣሚው ወይም አደጋው በቂ የሆነ ዝርዝር መረጃን መስጠት። በመቀጠልም በ [ባንኩ/ማኅበሩ] ጥያቄ መሠረት፣ በአጋጣሚው ወይም አደጋው ላይ ሪፖርት ማዘጋጀት እና አጋጣሚው ወይም አደጋው መልሶ እንዳይፈጠር ለመከላከል ሊወሰዱ የሚገባቸውን ማናቸውንም እርምጃዎች ምክረ ሐሳብ ማቅረብ። | *[ለማሳወቅ የጊዜ ማዕቀፍን መጥቀስ፤ ለምሳሌ አጋጣሚው ወይም አደጋው መፈጠሩ እንደታወቀ ለባንኩ በ48 ሰዓታት ውስጥ ማሳወቅ] [በመቀጠል የሚቀርበው ሪፖርት የሚቀርብበት ጊዜ በባንኩ የሚጠቀስ ይሆናል፤ ለምሳሌ በባንኩ/ማኅበሩ ተቀባይነት ባለው ጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ሪፖርቱ ሲጠየቅ የሚቀርብ ይሆናል]* | |

| ተጨባጭ እርምጃዎች እና ውሳኔዎች | | የጊዜ ማዕቀፍ | ኃላፊነቱን የሚወስደው ባለሥልጣን |
|---|---|---|---|
| ሐ | **የሥራ ተቋራጮች ወርኃዊ ሪፖርቶች**<br>[የባንኩን መደበኛ የግዢ ሰነዶች በመጠቀም ለሚሠሩ ሥራዎች በሚዘጋጁ የሥራ ውሎች ላይ፣ ሥራ ተቋራርጮች ለፕሮጀክት ተግባሪው አሃድ ወርኃዊ የክትትል ሪፖርት ማቅረብ ያስፈልጋል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ ቡድኖች እንዲህ ያሉት ወርኃዊ ሪፖርቶች ለባንኩ በተበዳሪው ሲጠየቅ የሚቀርቡ መሆናቸውን በመጥቀስ የሚወሰድ እርምጃን ማካተት ይችላሉ] | | |
| **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS 1):- የአካባቢ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ምዘና እና ቁጥጥር** | | | |
| **1.1** | **ድርጅታዊ መዋቅር**<br>[ከዚህ በታች እንደተሰጠው ምሳሌ ተጨማሪ ሠራተኞች መመደብ/ ወይም በፕሮጀክቱ ላይ እንዲሠሩ መቀጠር እንዳለባቸው ይጥቀሱ]።<br><br>የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ስጋቶችን መቆጣጠርን ለመደገፍ [ይህንን ጨምሮ] [ተዛማጅነት ሲኖረው፣ የድርጅታዊ መዋቅር አንድ አካል የሆኑ ለአካባቢያዊ፣ ማኅበራዊ ፣ ጤና እና ደኅንነት (ESHS) አስተዳደር አስፈላጊ የሆኑ የሥራ መደቦችን ለይቶ መጥቀስ ለምሳሌ የብዝኃ ሕይወት ስፔሻሊስት እና የጤና እና የደኅንነት ስፔሻሊስት] የሙያ ብቃት ያላቸው ሠራተኞች እና ግብዓቶች ጋር ድርጅታዊ መዋቅርን ማዘጋጀት እና ይዞ መቆየት። | *[ድርጅታዊ መዋቅር/ ሠራተኞች መቼ በቦታው ላይ መገኘት እንዳለባቸው መጥቀስ ለምሳሌ ሁለት (2) ተጨማሪ ስፔሺያሊስቶችን የያዘ ድርጅታዊ መዋቅር ፕሮጀክቱ ተፈጻሚ መሆን በጀመረ በ30 ቀናት ውስጥ ይቋቋማል። ስፔሺያሊስቶችን ጨምሮ ድርጅታዊ መዋቅሩ በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ወቅት በሙሉ ተጠብቆ መቆየት አለበት]* | |
| **1.2** | **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘና**<br>[በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS 1) ዓባሪ 1 ንኡስ አንቀጽ 5 ላይ የተጠቀሱ የተለያዩ ዘዴዎችን እና ሰነድ አያያዞችን ሊያካትት የሚችል የአካባቢ እና ማኅበራዊ ግምገማ (ESA) ተበዳሪዎች እንዲያደርጉ ይገደዳሉ። 5. የአካባቢ እና ማህበራዊ ግምገማ (ESA) መሻሻል የሚያስፈልገው ረቂቅ በሚሆንበት ጊዜ ማሻሻያውን ለማድረግ ያለው ግዴታ በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ላይ መንፀባረቅ አለበት። በፕሮጀክት ምርመራ ወቅት ምንም ተጨማሪ ምዘና ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ፣ በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ላይ ምንም ተጨማሪ እርምጃ መውሰድ አያስፈልግም። የእርምጃ ምሳሌን ከዚህ በታች ይመልከቱ]።<br><br>ለፕሮጀክቱ የተዘጋጀውን የአካባቢ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘና በ [ባንኩ/ማኅበሩ] ተቀባይነ ብለው መንገድ ማሻሻል፣ ከሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣም ማድረግ እና መተግበር። | *[የአካባቢ እና ማህበራዊ ግምገማ (ESA) ለማዘጋጀት የሚያስፈልገውን የጊዜ መርሐ ግብር ይጠቁሙ ወይም ቀደም ብሎ የተዘጋጀ ከሆነ በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት በሙሉ በአካባቢ እና ማህበራዊ ግምገማ (ESA) ውስጥ የተካተቱን የትግበራ እና የማረቂያ እርምጃዎች አስፈላጊነት ይጠቁሙ]።* | |

| ተጨባጭእርምጃዎች እና ውሳኔዎች | | የጊዜ ማዕቀፍ | ኃላፊነቱን የሚወስደው ባለሥልጣን |
|---|---|---|---|
| **1.3** | *የአስተዳደር መሣሪያዎችእና ሰነዶች*<br>[እዚህ ላይ ማናቸውም ሌላ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነዶች እና/ወይም የተዘጋጁ ዕቅዶች ወይም እንደ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ማዕቀፍ (ESMF), የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMPs)ያሉ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS 1) ሥር የሚዘጋጁ ቅዕዶችን ይጥቀሱ። ከዚህ በታች የተሰጠውን ምሳሌ ይመልከቱ]።<br><br>ለፕሮጀክቱ በተዘጋጀው የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ማዕቀፍ (ESMF)) መሠረት ማናቸውንም እንደ ሐሳብ የቀረበ ንኡስ ፕሮጀክት መመርመር እና ከዚህ በኋላ በባንኩ/ማኅበሩ ተቀባይነት ባለው መንገድ የንኡስ ፕሮጀክቱን የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶችን (ESMP) ረቂቅ ማዘጋጀት፣ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ፣ እና መተግበር። | *[ለሰነዶች ዝግጅቶች የጊዜ መርሐግብርን ይጠቁሙ። አንድ ጊዜ ከተዘጋጁ በኋላ መሣሪያዎች እና ሰነዶች በጠቅላላው የፕሮጀክት ትግበራ ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነዶች እና/ወይም ዕቅዶች የባንኩን ቅድሚያ ግምገማ እና ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋቸው እንደሆነ መጠቆም፤ ለምሳሌ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMPs) ለእያንዳንዱ የሚመለከተው ንኡስ ፕሮጀክት የጨረታው ሂደት ከመጀመሩ በፊት ባንኩ/ማኅበሩ ፈቃድ እንዲሰጥበት እንዲገባ ይደረጋል። አንድ ጊዜ ከጸደቀ በኋላ፣ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMPs) በጠቅላላው የፕሮጀክት ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።* | |
| **1.4** | *የሥራ ተቋራጮችአስተዳደር*<br>[አንዳንድ የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ሥራ ተቋራጮች/ንኡስ ሥራ ተቋራጮች የጉልበት ሥራዎችን እንዲያከናውኑ ሊያደርጓቸው ይችሉ ይሆናል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) የጨረታው ሰነዶች ተዛማጅነት ያላቸውን የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱን (ESCP) ገጽታዎች ማንፀባረቅ አለበት። ከዚህ በታች የተሰጠውን ምሳሌ ይመልከቱ]።<br><br>ተዛማጅነት ያላቸው የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነዶች እና/ወይም ዕቅዶችን፣ እንዲሁም የሠራተኛ አስተዳደር አሠራር ሥርዓቶችን ለሥራ ተቋራጮች ወደ የተዘጋጀው አካባቢያዊ፣ ማኅበራዊ ፣ ጤና እና ደኅንነት (ESHS) ዝርዝር ግዴታዎች ላይ እንዲካተቱ ማድረግን ጨምሮ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱን (ESCP) ተዛማጅ ገጽታዎች እንዲካተቱ ማድረግ። ከዚህ በኋላ ሥራ ተቋራጮቹ በየራሳቸው የሥራ ውሎች ላይ ባሉት አካባቢያዊ፣ ማኅበራዊ ፣ ጤና እና ደኅንነት (ESHS) ዝርዝር ግዴታዎች ተገዢ መሆናቸውን ማረጋገጥ። | *[የጊዜ መርሐግብርን ይጠቁሙ፡-<br>ለምሳሌ የግዢ ሰነዶችን ከማዘጋጀት በፊት።<br>በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት በሙሉ ሥራ ተቋራጮችን መከታተል]።* | |
| **አካባቢያዊእና ማኅበራዊመመዘኛ መስፈርት 2 (ESS 2):- ሠራተኛእና የሥራ ቦታሁኔታ** | | | |

| ተጨባጭ እርምጃዎች እና ውሳኔዎች | | የጊዜ ማዕቀፍ | ኃላፊነቱን የሚወስደው ባለሥልጣን |
|---|---|---|---|
| **2.1** | **የሠራተኛ አስተዳደር አሠራር ሥርዓቶች**<br>[የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) አስቀድመው የተዘጋጁ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ በተበዳሪው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ይህ በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) ውስጥ መንፀባረቅ ይኖርበታል። ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌ ይመልከቱ]<br><br>ለፕሮጀክቱ የተዘጋጁትን የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) ማሻሻል፣ እንደ ሁኔታው ማጣጣም እና መተግበር። | *[ጊዜን ይጠቁሙ ለምሳሌ በጠቅላላ የፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት]* | |
| **2.2** | **ለፕሮጀክት ሠራተኞች የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ**<br>[በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS 2) ሥር የሚያስፈልገው የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ በየሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) ውስጥ መብራራት አለበት። ከዚህ በታች የተሰጠውን ምሳሌ ይመልከቱ]።<br><br>በየሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) በተገለጸው መሠረት ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS 2) ጋር ወጥነት ባለው መልኩ ለፕሮጀክቱ ሠራተኞች የቅሬታ አቀራረብ ዘዴን ማቋቋም፣ ማስተካከል እና ከዋኔ ውስጥ እንዲገባ ማድረግ። | *[የጊዜ መርሐ ግብሩን ይጠቁሙ – ለምሳሌ የፕሮጀክት ሠራተኞችን ቀጥሮ ከማሠራት በፊት የቅሬታ አቀራረብ ዘዴን ሥራ ላይ እንዲወል ማድረግ እና በፕሮጀክት ትግበራው ወቅት በጠቅላላ ይዞ ማቆየት]።* | |
| **2.3** | **የሥራ አካባቢ ደኅንነት እና ጤንነት (OHS) እርምጃዎች**<br>[የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት እና ምላሽ አሰጣጥ እርምጃዎችን ጨምሮ የሥራ አካባቢ ደኅንነት እና ጤንነት (OHS) እርምጃዎች ከዚህ በላይ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS 1) ክፍል ውስጥ አስቀድሞ በተጠቀሰው ራሱን በቻለ የተለየ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነድ ውስጥ (ለምሳሌ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP)) ሊዘጋጅ ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ግዴታው በዚያ ሰነድ ሊመላከት ይችላል። ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌ ይመልከቱ]።<br><br>በየአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ውስጥ የተዘረዘሩትን የሥራ አካባቢ ደኅንነት እና ጤንነት (OHS) እርምጃዎችን ማዘጋጀት፣ እንደ ሁኔታው እንዲጣጣሙ ማድረግ እና መተግበር። | *[የጊዜ መርሐ ግብሩን ይጠቁሙ ለምሳሌ ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) አፈጻጸም ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጊዜ ማዕቀፍ]።* | |

| ተጨባጭእርምጃዎች እናውሳኔዎች | | የጊዜ ማዕቀፍ | ኃላፊነቱን የሚወስደው ባለሥልጣን |
|---|---|---|---|
| **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 3 (ESS 3):- የሀብት ውጤታማ አጠቃቀም እና የብክለት መከላከል እና ቁጥጥር** [የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 3 (ESS 3) ተዛማጅነት በየአካባቢ እና ማህበራዊ ግምገማ (ESA) ሂደት ወቅት ይቋቋማል። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 3 (ESS 3) የኢነርጂ፣ የውሃ እና ጥሬ ዕቃዎች አጠቃቀምን ለመሸፈን፣ የአየር ብክለትን፣ አደገኛ እና አደገኛ ያልሆኑ ቆሻሻዎችን፣ ኬሚካል እና አደገኛ ማቴሪያዎችን እንዲሁም ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን በቁጥጥር ሥር ለማዋል የተወሰኑ ልዩ እርምጃዎችን እንደ ሁኔታው አጣጥሞ ማዘጋጀትን ሊጠይቅ ይችላል። በፕሮጀክቱ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ፣ እነዚህ እርምጃዎች በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነድ (ለምሳሌ ቀደም ብሎ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS 1) በተጠቀሱት የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ወይም ራሱን እንደቻለ የተለየ ሰነድ ወይም የተነጠለ እርምጃ ውስጥ ሊዘጋጁ ይችላሉ። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 3 (ESS 3) ጋር የተገናኙ እርምጃዎች አሁን ባለው ሰነድ ወይም ለብቻቸው ተነጥለው በተዘጋጁት እርምጃዎች ላይ ሽፋን የተሰጣቸው ስለ መሆኑ መጠቆም። ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌ ይመልከቱ]። | | | |
| **3.1** | ኤሌክትሮኒካዊ ቆሻሻ አወጋገድ ዕቅድ:- ኤሌክትሮኒካዊ ቆሻሻ አወጋገድ ዕቅድን ማዘጋጀት፣ እንደ ሁኔታው ማጣጣም እና መተግበር። | *[የጊዜ መርሐ ግብሩን ይጠቁሙ ለምሳሌ ከፕሮጀክት ውጤታማነት ከሦስት ወር በኋላ ይዘጋጃል ከዚያ በኋላ በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት በጠቅላላ ተፈጻሚ ይሆናል]።* | |
| **3.2** | የግብዓት ውጤታማ አጠቃቀም እና የብክለት መከላከል እና ቁጥጥር ሥራ:- የግብዓት ውጤታማ አጠቃቀም እና የብክለት መከላከል እና ቁጥጥር ሥራዎች በየአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ከዚህ በላይ ባለው ድርጊት መርሐ ግብር XX ላይ የሚዘጋጁ ይሆናል። | *[የጊዜ መርሐ ግብሩን ይጠቁሙ ለምሳሌ ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) አፈጻጸም ጋር ተመሳሳይ የሆነ የጊዜ ማዕቀፍ]።* | |
| **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 4 (ESS 4):- የማኅበረሰብ ጤና እና ደኅንነት** [የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 4 (ESS 4) ተዛማጅነት በየአካባቢ እና ማህበራዊ ግምገማ (ESA) ሂደት ወቅት ይቋቋማል። ልክ በበአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 3 (ESS 3) ላይ እንደተደረገው፣ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 4 (ESS 4) የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነድ (ለምሳሌ ቀደም ብሎ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS 1) በተጠቀሱት የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ወይም ራሱን እንደቻለ የተለየ ሰነድ ወይም የተነጠለ እርምጃ ውስጥ እንዲዘጋጅ ሊጠይቅ ይችላል። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 4 (ESS 4) ጋር የተገናኙ እርምጃዎች አሁን ባለው ሰነድ ወይም ለብቻቸው ተነጥለው በተዘጋጁት እርምጃዎች ላይ ሽፋን የተሰጣቸው ስለ መሆኑ መጠቆም። ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌ ይመልከቱ]። | | | |
| **4.1** | ትራፊክ እና የመንገድ ላይ ደኅንነት። ከዚህ በላይ በድርጊት መርሐ ግብር XX ላይ የሚዘጋጁት በየአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMPs) በሚጠይቁት መሠረት የትራፊክ እና የመንገድ ደኅንነት ስጋቶችን ለመመዘን እና ለመቆጣጠር እንደ አስፈላጊነቱ እርምጃዎችን ማጣጣም እና መተግበር። | *[የጊዜ መርሐግብርን ይጠቁሙ:- ለምሳሌ ለአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMPs) ዝግጅት እና ትግበራ በላይ ተመሳሳይ የጊዜ መርሐግብር]።* | |

| ተጨባጭ እርምጃዎች እና ውሳኔዎች | | የጊዜ ማዕቀፍ | ኃላፊነቱን የሚወስደው ባለሥልጣን |
|---|---|---|---|
| **4.2** | የማኅበረሰብ ጤና እና ደኅንነት፦ ከፕሮጀክቱ እንቅስቃሴዎች የተነሣ [፣ ከሌሎች ነገሮች መካከል፣ ይህን ጨምሮ] [አፅዕኖት ሊሰጣቸው የሚገባቸው የስጋት አካባቢዎችን ይጥቀሱ ለምሳሌ የፕሮጀክቱ ሠራተኞች ባሕሪ፣ የሠራተኞች በቦታው መስፈር ጋር ያሉ ስጋቶች፣ ለድንገተኛ አደጋ ሁኔታዎች ምላሽ አሰጣጥ] በማኅበረሰብ ላይ የሚመጡ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎችን ለመመዘን እና ለመቆጣጠር የሚወሰዱ እርምጃዎችን ማዘጋጀት፣ እንደ አስፈላጊነቱ ማጣጣም፣ እና መተግበር እንዲሁም እነዚህን እርምጃዎች በባንኩ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለማዘጋጀት በየአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ማዕቀፍ (ESMF) መሠረት በየአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMPs) ውስጥ እንዲካተቱ ማድረግ። | *[የጊዜ መርሐግብርን ይጠቀሙ፦ ለምሳሌ ለአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMPs) ዝግጅት እና ትግበራ በላይ ተመሳሳይ የጊዜ መርሐግብር]።* | |
| **4.3** | ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ጥቃት (GBV) እና ወሲባዊ ጭቆና እና ጥቃት (SEA) ስጋቶች፦ [ለመካከለኛ፣ ግምት የሚሰጣቸው ወይም ከፍተኛ ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ጥቃት (GBV) ስጋት ላለባቸው ፕሮጀክቶች]<br><br>ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ጥቃት (GBV) እና ወሲባዊ ጭቆና እና ጥቃት (SEA) ስጋቶችን ለመመዘን እና ለመቆጣጠር ራሱን የቻለ ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ጥቃት (GBV) መከለከያ የድርጊት መርሐ ግብር ማዘጋጀት፣ እንደ ሁኔታው ማጣጣም እና መተግበር። | *[የጊዜ መርሐግብሩን ይጠቀሙ ለምሳሌ ከግዢ ሰነዶቹ ዝግጅት በፊት የባንኩን ፈቃድ ለማግኘት ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ጥቃት (GBV) መከለከያ የድርጊት መርሐ ግብር ማስገባት። አንድ ጊዜ ከጸደቀ በኋላ ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ጥቃት (GBV) የድርጊት መርሐ ግብሩ በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት በጠቅላላ ተፈጻሚነት ይኖረዋል]።* | |
| **4.4** | በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት ሥርዓተ ጾታን ያማከለ ጥቃት (GBV) እና ወሲባዊ ጭቆና እና ጥቃት (SEA) ስጋቶች፦ [አስፈላጊ ከሆነ፣ በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ የሥርዓተ ጾታን ያማከለ ጥቃት (GBV) እና ወሲባዊ ጭቆና እና ጥቃት (SEA) ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎች መፍትሔ ለመስጠት እርምጃዎችን ለመውሰድ ሊገኙ የሚችሉ ተጨማሪ ገንዘብ ምንጮችን ይጥቀሱ።] | | |
| **4.4** | የፀጥታና ጥበቃ ሠራተኞች፦ በባንኩ ተቀባይነት ባለው መንገድ ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 4 (ESS 4) በሚጣጣም መልኩ ራሱን የቻለ የፀጥታና ጥበቃ ሠራተኞች አስተዳደር ዕቅድን ማዘጋጀት፣ እንደ አስፈላጊነቱ ማጣጣም እና መተግበር። | *[የጊዜ መርሐ ግብሩን ይጠቀሙ ለምሳሌ የፀጥታና ጥበቃ ሠራተኞችን ከመቅጠር በፊት እና ከዚያ በኋላ በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት በጠቅላላ ተፈጻሚ ይሆናል]።* | |
| **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS 5)፦ መሬትን ማግኘት፣ በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦች እና በፈቃደኝነት ላይ ያልተመረኮዘ ሰፈራ** [የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS 5) ተዛማጅነት በየአካባቢ እና ማህበራዊ ግምገማ (ESA) ሂደት ወቅት የሚቋቋም ይሆናል። በፕሮጀክት ዝግጅት ወቅት፣ ዳግም ሰፈራ ሰነዶች መዘጋጀት እንዳለባቸው ከታወቀ፣ ይህ በየአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) ላይ መንፀባረቅ ይኖርበታል። ከዚህ በታች ያሉትን ምሳሌዎች ይመልከቱ] | | | |

| ተጨባጭእርምጃዎች እናውሳኔዎች | | የጊዜ ማዕቀፍ | ኃላፊነቱን የሚወስደው ባለሥልጣን |
|---|---|---|---|
| **5.1** | *የዳግም ሰፈራ ዕቅዶች፡-* በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS 5) መሠረት እና ለፕሮጀክቱ ከተዘጋጀው በየዳግም ማቋቋም ፖሊሲ ማዕቀፍ (RPF) ጋር በሚጣጣም መልኩ የዳግም ማቋቋም ዕቅዶችን (RAPs) ማዘጋጀት፣ እንደ ሁኔታው ማጣጣም እና መተግበር እና ከዚህ በኋላ ተዛማጅነት ያላቸውን እንቅስቃሴዎችን ከማከናወን በፊት በ[ባንኩ/ማኅበሩ] ተቀባይነት ባለው መንገድ እያንዳንዱን የዳግም ማቋቋም ዕቅዶች (RAPs) ተፈጻሚ ማድረግ። | *[የጊዜ መርሐግብሩን ይጠቁሙ ለምሳሌ የዳግም ማቋቋም ዕቅዶች (RAPs) ባንኩ ዐይቶ ፈቃድ እንዲሰጥበት ይገባል፣ አንድ ጊዜ ፈቃድ ከተሰጠበት በኋላ መሬትን ማግኘት እና ዳግም ሰፈራን የሚያካትቱ የፕሮጀክቱን እንቅስቃሴዎች ከማከናወን በፊት መተግበር]።* | |
| **5.2** | *የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ*<br>*[ከዳግም መቋቋም ወይም ሰፈራ ጋር የተገናኑ ቅሬታዎችን መፍትሔ ለመስጠት የተዘጋጀው የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ (GM) በዳግም ማቋቋም ፖሊሲ ማዕቀፍ (RPF)፣ በዳግም ማቋቋም ዕቅዶች (RAPs) እና በየባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ውስጥ መብራራት አለበት። ሆኖም ግን ከአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS 5) ጋር የተገናኙ አቤቱትዎችን እንዴት መስተናገድ እንዳለባቸው የሚያመላክት የተለየ ባሕሪ ካለ፣ ይህ በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) ውስጥ ሊጠቀስ ይችላል]።* | *[የጊዜ መርሐግብሩን ይጠቁሙ ለምሳሌ የዳግም ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ከመጀመራቸው በፊት]* | |
| **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 6 (ESS 6):- ብዝኃ ሕይወት ጥበቃ እና ሕያው የተፈጥሮ ሀብቶች አስተዳደር** [የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 6 (ESS 6) ተዛማጅነት በየአካባቢ እና ማህበራዊ ግምገማ (ESA) ሂደት ወቅት ይቋቋማል። ልክ እንደ ሌሎቹ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ላይ እንደተደረገው፣ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 6 (ESS 6) የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነድ (ለምሳሌ ቀደም ብሎ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS 1) በተጠቀሱት የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ወይም ራሱን እንደቻለ የተለየ ሰነድ ወይም የተነጠለ እርምጃ ውስጥ እንዲዘጋጅ ሊጠይቅ ይችላል። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 6 (ESS 6) ጋር የተገናኙ እርምጃዎች አሁን ባለው ሰነድ ወይም ለብቻቸው ተነጥለው በተዘጋጁት እርምጃዎች ላይ ሽፋን የተሰጣቸው ስለ መሆኑ መጠቆም። ከዚህ በታች ያለውን <u>ምሳሌ</u> ይመልከቱ]። | | | |
| **6.1** | *የብዝኃ ሕይወት ስጋቶችእና ተፅዕኖዎች፡-* *[ከብዝኃ ሕይወት ጋር የተገናኙ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች እንደ የአካባቢያዊእና ማኅበራዊአስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) አንድ አካል ሆነው ሽፋን ማግኘት በማይችሉበት ጊዜ]*<br><br>ለፕሮጀክቱ በተዘጋጀውየአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘና (ESIA) መሠረት እና በባንኩ ተቀባይነት ባለው መንገድ ራሱን የቻለ ብቻውን ተነጥሎ የሚቀርብ የብዝኃ ሕይወት አስተዳደር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ እንደ ሁኔታው እንዲጣጣም ማድረግ እና መተግበር። | *[ከዚህ ጊዜ በፊት ከባንኩ ፈቃድ ለማግኘት ማስገባት፡- [ቀን][ፕሮጀክቱ ሥራ ከጀመረ ከሦስት ወራት በኋላ][ ብዝኃ ሕይወት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳርፍ የሚችለው [ስትራክቸር] ግንባታ በፊት]]።*<br><br>*[አንድ ጊዜ ከጸደቀ በኋላ፣ ዕቅዱ በጠቅላላው የፕሮጀክት ትግበራ ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።* | |
| **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS 7):- የአካባቢው ተወላጅ ሕዝቦች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ በቂ ትኩረት ያላገኙ ባህላዊ የአፍሪካ የአካባቢ ማኅበረሰቦች** [አካባቢያዊእና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS 7) ተዛማጅነት ያለው መሆኑ ከታወቀ ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎችን ምሳሌዎች ከዚህ በታች ይመልከቱ]። | | | |

| ተጨባጭእርምጃዎች እና ውሳኔዎች | | የጊዜ ማዕቀፍ | ኃላፊነቱን የሚወስደው ባለሥልጣን |
|---|---|---|---|
| 7.1 | **የአካባቢ ተወላጆች ዕቅድ፡-** ለፕሮጀክቱ እና አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS 7) በተዘጋጀው የአካባቢ ተወላጆች የዕቅድ አወጣጥ ማዕቀፍ (IPPF) መስፈርቶች መሠረት የአካባቢ ተወላጆች ዕቅዶችን (IPPs) በባንኩ ተቀባይነት ባለው መንገድ ማዘጋጀት፣ እንደ ሁኔታው እንዲጣጣሙ ማድረግ እና መተግበር። | *[የጊዜ መርሐግብርን ይጠቁሙ ለምሳሌ<br>የግል የኃይል አምራቾች (IPP) ሰነድን ዝግጅት የሚጠይቅ ማናቸውንም እንቅስቃሴ ከማድረግ በፊት የባንኩን ፈቃድ ለማግኘት ተዛማጅነት ያለውን የግል የኃይል አምራቾች (IPP) ሰነድ ማስገባት። አንድ ጊዜ ከተፈቀደ በኋላ በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት በሙሉ የግል የኃይል አምራቾችን (IPP) ተግባራዊ ማድረግ።]* | |
| 7.2 | **የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ፡-** በአካባቢ ተወላጆች የዕቅድ አወጣጥ ማዕቀፍ (IPPF) ሥር በሚጠየቀው እና እንዲህ ያሉት ዝግጅቶች በነፍስ ወከፍ የአካባቢ ተወላጆች ዕቅዶች (IPPs) በተጨማሪ በተዘረዘረው መሠረት ለአካባቢ ተወላጆች ቅሬታን ማቅረቢያ ዘዴ ማዘጋጀት፣ እንደሁኔታው እንዲጣጣም ማድረግ እና መተግበር (የቅሬታ አቀራረብ ዘዴው በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS 10) ሥር ካለው የተለየ ከሆነ)። | *[የጊዜ መርሐግብርን ይጠቁሙ]* | |
| **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 8 (ESS 8)፡- ባህላዊ ቅርሶች** [የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 6 (ESS 6) ተዛማጅነት በየአካባቢ እና ማኅበራዊ ግምገማ (ESA) ሂደት ወቅት ይቋቋማል። ልክ እንደ ሌሎቹ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ላይ እንደተደረገው፣ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 6 (ESS 6) የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) ሰነድ (ለምሳሌ ቀደም ብሎ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS 1) በተጠቀሱት የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ወይም ራሱን እንደቻለ የተለየ ሰነድ ወይም የተነጠለ እርምጃ ውስጥ እንዲዘጋጅ ሊጠይቅ ይችላል። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 8 (ESS 8) ጋር የተገናኙ እርምጃዎች አሁን ባለው ሰነድ ወይም ለብቻቸው ተነጥለው በተዘጋጁት እርምጃዎች ላይ ሽፋን የተሰጣቸው ስለ መሆኑ መጠቆም። ከዚህ በታች ያለውን ምሳሌ ይመልከቱ]። | | | |
| 8.1 | **ልዩ ዕድል ማግኛቶች፡-** ለፕሮጀቱ በተዘጋጁት የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ውስጥ የተዘረዘሩትን ልዩ ዕድል ማግኛቶች አፈጻጸም ሥርዓቶችን ማዘጋጀት፣ እንደ ሁኔታው እንዲጣጣሙ ማድረግ እና መተግበር። | *[ጊዜን ይጠቁሙ ለምሳሌ በጠቅላላ የፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት]* | |
| **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 9 (ESS 9)፡- የፋይናንስ ድርጅቶች** [ይህ መመዘኛ መስፈርት የፋይናንስ ድርጅቶችን (Fis) በሚያሳትፉ ፕሮጀክቶች ላይ ብቻ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። የፋይናንስ ድርጅቶች (Fis) ተሳትፎ በሚኖራቸው ወቅት ከግምት ሊገቡ ስለሚገባቸው እርምጃዎች የተሰጡትን አንድ፣ ሁለት ምሳሌዎች ከዚህ በታች ይመልከቱ።] | | | |
| 9.1 | **የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ሥርዓት (ESMS)፡-** የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ሥርዓት (ESMS) ማዘጋጀት፣ እንደ አስፈላጊነቱ ማጣጣም እና ይዞ ማቆየት። | *[የጊዜ መርሐግብርን ይጠቁሙ ለምሳሌ የማናቸውንም የፋይናንስ ድርጅቶች (FI) ንኡስ ፕሮጀክት ከመከናወኑ በፊት። አንድ ጊዜ ከተዘጋጀ በኋላ፣ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ሥርዓት (ESMS) በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት በሙሉ ተጠብቆ ይቆያል እንዲሁም ሥራ ላይ ይውላል]።* | |

| ተጨባጭ እርምጃዎች እና ውሳኔዎች | | የጊዜ ማዕቀፍ | ኃላፊነቱን የሚወስደው ባለሥልጣን |
|---|---|---|---|
| 9.2 | የፋይናንስ ድርጅቶች (FI) ድርጅታዊ አቅም፡- በግልጽ ከተቀመጡ ሚናዎች እና ኃላፊነቶች ጋር [ተገቢነት ሲኖረው ለአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ (E&S) አስተዳደር በድርጅታዊ መዋቅሩ አንድ አካል ለሆኑ የሥራ ኃላፊነቶች እና ግብዓቶች] የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ሥርዓትን (ESMS) ለመተግበር የሚያስችል ድርጅታዊ አቅም እና ብቃትን ማቋቋም እና ይዞ ማቆየት። | *[የጊዜ መርሐግብሩን ይጠቁሙ ለምሳሌ ድርጅታዊው አቅም መቼ ቦታውን መያዝ እንዳለበት የተወሰኑ የሥራ ማዕረጎችን/ግብዓቶችን ጨምሮ በ [ቀን] መጥቀስ]።* | |
| 9.3 | የከፍተኛ አስተዳደር አካል ተወካይ፡- ለፋይናንስ ድርጅቶች (FI) ንኡስ ፕሮጀክቶች የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አፈጻጸም አጠቃላይ ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ የከፍተኛ አመራር ተወካይን መመደብ። | *[የከፍተኛ አመራር ተወካዩ መቼ መመደብ እንዳለበት መጥቀስ]።* | |
| **አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS 10)፡- የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እና መረጃን ይፋ ማውጣት ሁኔታ** | | | |
| 10.1 | የባለድርሻ አካል ተሳትፎ ዕቅድ ዝግጅት እና ትግበራ<br>[የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ረቂቅ ተዘጋጅቶ ከምዘና በፊት ይፋ መሆን አለበት። የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ዕቅዱ ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ የነበረ ስለመሆኑ ወይም መሻሻል ያስፈልገው እንደሆነ እና ትግበራው እንደሚያስፈልግ መጠቆም አለበት። ከዚህ በታች የተሰጠውን ምሳሌ ይመልከቱ]።<br><br>የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድን (SEP) ማሻሻል፣ እንደ አስፈላጊነቱ ማጣጣም እና ተግባራዊ ማድረግ። | *[ጊዜውን ይጠቁሙ፡- ለምሳሌ ከ [ቀን ወይም በጣም አስፈላጊ ኹነት] በፊት]* | |
| 10.2 | የፕሮጀክት የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ፡- በየባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) በተገለጸው መሠረት የቅሬታ አቀራረብ ዘዴን ማዘጋጀት፣ እንደ አስፈላጊነቱ ማጣጣም እና መከወን። | *[የጊዜ መርሐግብርን ይጠቁሙ፡- ለምሳሌ ከዚህ በፊት<br><br>[ቀን ያስገቡ]]።* | |
| **የአቅም ግንባታ ድጋፍ (ሥልጠና)** | | | |
| CS1 | [የሚሠጠውን ሥልጣና እና ዒላማ ቡድኖችን ይጥቀሱ<br>ለምሳሌ፣ [ለምሳሌ የፕሮጀክት ትግበራ ክፍል (PIU) ሠራተኞች፣ ባለድርሻ አካላት፣ ማኅበረሰቦች፣ ፕሮጀክት ሠራተኞች] በሚከተሉት ላይ ሥልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡-<br>• የባለድርሻ አካላት ያሉበትን በታለይቶ ማወቅ እና ማሳተፍ<br>• የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘና ልዩ ገጽታዎች<br>• የድንገተኛ አደጋ ዝግጁነት እና ምላሽ አሰጣጥ<br>• **የማኅበረሰብ ጤና እና ደኅንነት፡-]** | | |

| ተጨባጭ እርምጃዎች እና ውሳኔዎች | | የጊዜ ማዕቀፍ | ኃላፊነቱን የሚወስደው ባለሥልጣን |
|---|---|---|---|
| CS2 | [የድንገተኛ አደጋን መከላከል እና ዝግጅቱን እና ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓቶችን ጨምሮ በሥራ ቦታ ጤና እና ደኅንነት ጉዳይ ዙሪያ ለፕሮጀክት ሠራተኞች የሚሰጠውን ሥልጠና መጥቀስ።] | | |

## ዓባሪ 2፡- የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ ማረጋገጫ ዝርዝር

ይህ ማረጋገጫ ዝርዝር የዓለም ባንክ የ2016ቱን የአካባቢ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ አንድ አካል የሆኑትን የአካባቢ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች ትግበራ በተመለከተ ለተበዳሪው መመሪያን ይሰጣል። ማረጋገጫ ዝርዝሮች ለአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መስፈርቶች ለማብራራት ያግዛሉ እንዲሁም የባንክ ፖሊሲ ያልሆኑ እንዲሁም አስገዳጅነት ባሕሪ የሌላቸውን የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) አንዳንድ መስፈርቶችን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ናሙና ዘዴዎችን እንደ ሐሳብ ያቀርባሉ። የፕሮጀክት ውሳኔዎችን በመወሰን ወቅት የራስን ሚዛናዊ የሕሊና ፍርድ አሰጣጥን መጠቀም የማስፈለግ ሁኔታን አይተኩም። በማረጋገጫ ዝርዝሮች እና በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) መካከል አለመጣጣም በሚፈጠርበት ጊዜ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ላይ የተቀመጡት ይዘቶች የበላይነት ይኖራቸዋል።

የፕሮጀክቱ የቅሬታ አፈታት ዘዴ (GRM) ተገቢነት ያለው የውስብስብነት ደረጃ በፕሮጀክቱ የስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ደረጃ እና በፕሮጀክቱ ዓውድ የሚመረኮዝ ይሆናል። የሚከተለው ማረጋገጫ ዝርዝር ለሁሉም ፕሮጀክቶች ምናልባት አስፈላጊ ሊሆን የማይችል መልካም የዓለም አቀፍ አሠራር ልምድን የሚያከብርን የቅሬታ አፈታት ዘዴ (GRM) ያብራራል። እንዲሁም ሆኖ ግን፣ ይህ የማረጋገጫ ዝርዝር የቅሬታ አፈታት ዘዴው መልካም ዓለም አቀፍ አሠራር ልማድ ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ያግዛል።

### ሀ. የሲስተም ችግሮች

1. ፕሮጀክቱ ግብረመልስን/ቅሬታዎችን ይቀበላል?

2. ድርጅቱ የቅሬታ አፈታት ፓሊሲ አለው?

   ሀ. ፖሊሲው ለሁሉም ሠራተኞች፣ ተጠቃሚዎች እና ወደፊት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ወገኖች ሊገኝ የሚችል ነው?

   ለ. ፖሊሲው በአካባቢው ቋንቋ(ዎች) የተጻፈ ነው?

3. የቅሬታ አቀራረብ ዘዴው የሚከተሉትን ባሕሪያት አሉት?

   ሀ. ሰዎች ግብረመልስ መስጠት እንዲችሉ እና/ወይም ቅሬታ ማሰማት እንዲችሉ የሚያደረግ በግልጽ መረዳት የሚቻል አሠራር።

   ለ. ግብረመልስን/ቅሬታን ተቀብሎ ለማስተናገድ ማን ኃላፊነት እንዳለበት የሚገልጽ ገላጭ ዐርፍተ ነገር።

   ሐ. እንደ ክብደታቸው እና ውስብስብነታቸው ቅሬታዎችን መፍትሔ ለመስጠት ወይም ምርመራ ለማድረግ የሚያስችሉ አሠራር ሥርዓቶች።

   መ. ስለ ወቅታዊ አቋም መረጃዎችን ለቅሬታ አቅራቢዎች ማድረስ የሚያስችል ሥርዓት።

   ሠ. ግብረመልስ/ቅሬታዎችን እና ውጤቶችን ለመመዝገብ የሚያስችል ሥርዓት።

   ረ. የቅሬታ አቅራቢዎችን ምስጢር ለመጠበቅ የሚያስችል አሠራር ሥርዓት።

### ለ. የሠራተኛ አስተዳደር

1. ለሠራተኞች የተዘጋጀ የአቤቱታ አቀራረብ መመሪያ ሰነድ አለ?

2. የአቤቱታ አቀራረብ ፖሊሲው እና/ወይም አሠራር ሥርዓቶች በሚከተሉት ላይ መመሪያዎችን ይሰጣሉ?

   ሀ. አቤቱታ/ግብረመልስ ምንድን ነው?

   ለ. ከአቤቱታ አቅራቢዎች ምን ዓይነት መረጃ ይሰበሰባል?

   ሐ. ለአቤቱታዎች መፍትሔ ለመስጠት ምን ዓይነት መፍትሔዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ ወይም ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው?

3. የአቤቱታ አቀራረብ ፖሊሲው እና የአሠራር ሥርዓቶቹ ለሁሉም ሠራተኞች እንዲደርሳቸው ተደርጓል?

4. የአቤቱታ አቀራረብ ዘዴው በውጤታማ መንገድ መሥራት እንዲችል በቂ የሆኑ ግብዓቶች ተዘጋጅተውለታል?

5. ድርጅቱ አቤቱታን ማስተናገድ በተመለከተ ለሠራተኞቹ ሥልጠናን ይሰጣል?

## ሐ. ከቅሬታ አፈታት ዘዴ ተጠቃሚዎች ጋር መልእክት መለዋወጥ

1. ተጠቃሚዎች እንዴት ቅሬታዎችን/ግብረመልስን ማስገባት እንደሚችሉ ተነግሯቸዋል?

   ሀ. ለተጠቃሚዎች በቅሬታ አፈታት ዘዴው ዙሪያ የተዘጋጀ መረጃ ሰጪ ብሮሹር ተዘጋጅቶላቸዋል?

   ለ. ግብረመልስ/ቅሬታ ቅፆችን ተጠቃሚዎች ማግኘት ይችላሉ?

   ሐ. የቅሬታ ማቅረቢያ ቅፆች ወይም ምልክቶች በግልጽ የሚታዩ እና በቀላሉ ተደራሽ ናቸው?

   መ. ግብረመልስ/ቅሬታ የሚቀበሉ ሠራተኞች መገኛ አድራሻዎች ታትመው ለሁሉም ሰው ሊታዩ በሚችሉባቸው ቦታዎች ላይ ተለጥፈዋል?

   ሠ. በቅሬታ አያያዝ ላይ የተዘጋጀ መረጃ በአካባቢው ቋንቋዎች ተዘጋጅቷል?

2. ተጠቃሚዎች ቅሬታዎችን/ግብረመልስን በሚከተለው መንገድ ማስገባት ይችላሉ፡-

   ሀ. በጽሑፍ

   ለ. በኢሜይል

   ሐ. በፋክስ

   መ. በስልክ

   ሠ. በአካል

3. አስፈላጊ ሲሆን ተጠቃሚዎች ግብረመልስ/ቅሬታ አቀራረብ ላይ ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል?

4. የቅሬታ አቀራረብ ዘዴው በነጻ ሊገኝ ይችላል?

5. ተጠቃሚዎች ጉዳያቸው በምስጢር እንደሚያዝላቸው ቃል ተገብቶላቸዋል?

6. ተጠቃሚዎች ስለ ይግባኝ አቀራረብ ሂደቱ መረጃ ተሰጥቷቸዋል?

**መ. ግብረመልስ/ቅሬታን መዝግቦ መያዝ**

1. ሁሉም ግብረመልሶች/ቅሬታዎች ተመዝግበው ተይዘዋል?

   ሀ. ቅሬታዎች/ግብረመልሶች ተመዝግበው በሰነድነት ተይዘዋል?

   ለ. ጥያቄዎች/ጥቆማ ሐሳቦች እና ጠቃሚ ምክሮች ተመዝግበው ተይዘዋል?

   ሐ. የሁሉም ቅሬታዎች/ግብረመልሶች ውጤቶች እና ምላሾች ተመዝግበው ተይዘዋል?

**ሠ. የሥራ መመዘኛ መስፈርቶች**

1. አቤቱታ/ግብረመልስ የሚስተናገዱበት በሥራ ላይ ያለ የአፈጻጸም ሂደት እና ጊዜ መርሐግብር የሥራ መመዘኛ መስፈርቶች አሉ?

   ሀ. የቀረበው አቤቱታ/ግብረመልስ ስለመድረሱ በተቀመጠው የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ ለላኪው እንዲያውቀው ይደረጋል?

   ለ. አቤቱታዎች በተቀመጠው የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ መፍትሔ እንዲያገኙ ታስቧል?

2. የሚከተሉትን ለማድረግ የአሠራር ጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት በቦታው ላይ አለ፡-

   ሀ. ሁሉም አቤቱታዎች እንደተስተናገዱ ወይም አስፈላጊው እርምጃ እንደተወሰደባቸው ማረጋገጥ።

   ለ. ሁሉም የአቤቱታ ገጽታዎች መፍትሔ እንደተሰጣቸው ማረጋገጥ።

   ሐ. አስፈላጊው የክትትል እርምጃ እንደተወሰደ ማረጋገጥ።

**ረ. ትንታኔ እና ግብረመልስ**

1. ከፍተኛ አመራሮች ስለ አቤቱታዎች/ግብረመልሶች በመደበኛነት ውስጣዊ ሪፖርቶች ኣንዲያገኙ ተደርገዋል?

2. የአቤቱታዎች/ግብረመልሶች ሪፖርቶች የሚከተሉትን መረጃዎች ይይዛሉ፡-

   የቀረቡ አቤቱታዎች/ግብረመልስ ብዛት።

   በሥራ አፈጻጸም መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ያለው ተገዢነት ሁኔታ።

   በአቤቱታዎች/ግብረምልስ ውስጥ የተነሡ ችግሮች።

   በጊዜ ሂደት የተስተዋሉ የአቤቱታ/ግብረመልስ አዝማሚያዎች።

የአቤቱታ/ግብረመልስ መንሥዔ ምክንያቶች።

መፍትሔ ሰጪ እርምጃ እንደሚወስድ ቃል ስለ መገባቱ።

ምን ዓይነት መፍትሔ በተጨባጭ እንደተሰጠ?

ወደፊት በተደጋጋሚ እንዳይፈጠር ለመከላከል ወይም ለማስቆም የሚረዱ ጠቃሚ ምክሮች/ስትራቴጂዎች።

3. ስለ አቤቱታዎች/ግብረመልሶች የተዘጋጁ ሪፖርቶች ለሕዝብ በተወሰነ ጊዜ ልዩነት ይፋ ይሆናሉ?

## ዓባሪ 3፡- የባለድርሻ አካል ተሳትፎ ዕቅድ ጠቋሚ ዝግጁ አብነት (template)

ይህ ዝግጁ አብነት የዓለም ባንክ የ2016ቱን የአካባቢ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ አንድ አካል የሆኑትን የአካባቢ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) የተወሰነ ዓይነት የትግበራ ገጽታዎች በተመለከተ ለተበዳሪው መመሪያን ይሰጣል። ዝግጁ አብነቶች የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ለማብራርት ያግዛሉ እንዲሁም እነዚህን መስፈርቶች ለማሟላት የሚያስችሉ ዘዴዎችን እንደ ሐሳብ ያቀርባሉ፤ የባንኩ ፖሊሲ አይደሉም እና ጠቃሚ እና በፈቃደኝነት ጥቅም ላይ የሚውሉ መሣሪያዎች እንዲሆኑ ብቻ የታለሙ ናቸው። በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ላይ ወጥነት ሳይኖር ቢቀር ወይም አለመግባባት ቢፈጠር የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) የበላይነት ይኖራቸዋል።

የዕቅዱ ወሰን እና የዝርዝር መረጃ ደረጃ ከፕሮጀክቱ ተፈጥሮ እና ደረጃ፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች እንዲሁም በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ሊያርፍባቸው በሚችሉ ወይም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሊኖራቸው የሚችሉ የሚያሳስቡ ነገሮች መጠን የተመጣጠና እና ተገቢነት ያለው መሆን መቻል አለበት። በፕሮጀክቱ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ደረጃ ላይ በመመርኮዝ፣ የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) አባለ ነገሮች እንደ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) እና በባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ላይ አንድ አካል ሆነው ሊካተቱ ይችሉ ይሆናል።

*የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ግልጽ እና አጥር ምጥን ያለ መሆን እንዲሁም ፕሮጀክቱን በመግለጽ እና ባለድርሻ አካላቱን ለይቶ ማወቅ ላይ ያተኮረ መሆን ይኖርበታል። የትኛው መረጃ በየትኛው የሕዝብ ጎራ፣ በምን ቋንቋ እንደሚቀርብ እና የት ቦታ እንደሚገኝ ለይቶ ማወቅ በጣም ወሳኝነት አለው። ለሕዝብ ምክክር ያሉትን ዕድሎች ማብራራት፣ አስተያየቶች የሚሰጡበትን ቀነ ገደብ ማስቀመጥ፣ እንዲሁም አዲስ መረጃ ሲኖር ወይም አስተያየት መስጠት የሚያስችሉ ዕድሎች ሲኖሩ ሰዎች እንዴት እንዲያውቁት እንደሚደረጉ ማብራራት አለበት። አስተያየቶች እንዴት እንደሚመዘኑ እና እንዴት ከግምት ውስጥ እንደሚገቡ ማብራራት አለበት። በተጨማሪ የፕሮጀክቱን የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ እና ይህን ዘዴ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ማብራራት አለበት። የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ለምክክር ያሉ ዕድሎችን እና ቅሬታዎች እንዴት መፍትሔ እንደሚሰጣቸው ጨምሮ በፕሮጀክቱ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አፈጻጸም ላይ በመደበኛነት መረጃ ለመልቀቅ ቁርጠኝነት ያለው መሆን አለበት።*

የሚከተለው መደበኛ የሆነውን የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ቢጋር ያቀርባል፡-

### 1. *መግቢያ/የፕሮጀክት ዝርዝር መግለጫ*

ፕሮጀክቱን፣ የፕሮጀክቱን ደረጃ፣ ዓላማውን እና የሕዝብ ተሳትፎ የሚያስፈልግባቸው ናቸው የተባሉ አሁን ላይ እየታዩ ያሉ ምን ዓይነት ውሳኔዎች እንዳሉ በአጭሩ ማብራራት።

*መገኛ ቦታን ማብራራት፣ የሚቻል ከሆነ የፕሮጀክቱን የሥራ ቦታ እና አካባቢውን የሚያሳይ ካርታ ማቅረብ፣ በዚህም ማኅበረሰቦችን እና አደጋ ሊፈጥሩ ከሚችሉ ቦታዎች ጋር ያላቸውን ቅርበት ማሳየት እና በአጥር የተከለሉ ቦታዎች ወይም ሌላ ባለድርሻ አካላት ላይ ተፅዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ጊዜያዊ እንቅስቃሴ የሚከናወንባቸው ቦታዎችን ጨምሮ ማናቸውንም የሠራተኞች መኖሪያዎች ማሳየት። የፕሮጀክቱን ሊያጋጥሙ የሚችሉ ማኅበራዊ እና አካባቢያዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች አገናኝ (ሊንክ) መስጠት ወይም ቴክኒካዊ ያልሆነ አጭር ማጠቃለያን ዓባሪ ማያያዝ።*

### 2. ከዚህ ቀደም የነበሩ የባለድርሻ አካል እንቅስቃሴዎች አጭር ማጠቃለያ

የመረጃ ይፋ ማውጣት እና ኢመደበኛ ወይም መደበኛ ስብሰባዎች/ወይም ምክክር ጨምሮ እስካሁን የተከናወኑ ምክክሮች ወይም የእንቅስቃሴዎች መረጃ ይፋ ማውጣት ሁኔታ ከነበረ፣ የእነዚያን እንቅስቃሴዎች፣ ይፋ የሆነው መረጃ፣ እና ስለ እነዚህ ከዚህ ቀደም የነበሩ እንቅስቃሴዎች ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ የት ሊገኝ እንደሚችል ጠቋሚ መረጃ (ለምሳሌ፡- አገናኝ (ሊንክ) ወይም ቦታ ወይም በጥያቄ ሊገኝ የሚችል) አጭር ማጠቃለያ መስጠት (ከግማሽ ገጽ በማይበልጥ)።

## 3. የባለድርሻአካል ልየታእናትንታኔ

ስለ ፕሮጀክቱ የሚከተሉትን ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን ወይም ማኅበረሰቦችን ጨምሮ መረጃ የሚሰጣቸውን እና አብሮ ምክክር የሚደረግባቸውን ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ለይቶ ማወቅ፡-

a. በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ያረፈባቸው ወይም ሊያርፍባቸው የሚችሉ (በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ያረፈባቸው ወገኖች)፤ እና
b. የፕሮጀክቱ ጉዳይ ሊመለከታቸው የሚችሉ (ሌላ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች)።

በፕሮጀክቱ ተፈጥሮ እና ወሰን እንዲሁም ሊኖሩት በሚችሉ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ላይ የሚመረኮዝ ሆኖ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሊሆኑ የሚችሉ ወገኖች ምሳሌዎች የመንግሥት ባለሥልጣናትን፣ የአካባቢ ድርጅቶችን፣ መያዶችን፣ እና ኩባንያዎችን እንዲሁም በአቅራቢያ ያሉ ማኅበረሰቦችን ሊያካትት ይችል ይሆናል። ባለድርሻ አካላት ፖለቲከኞችን፣ የሠራተኛ ማኅበራትን፣ ምሁራንን፣ የሃይማኖት ቡድኖችን፣ ብሔራዊ የማኅበራዊ እና አካባቢያዊ የሕዝብ ዘርፍ ኤጀንሲዎችን እና መገናኛ ብዙኃንን በተጨማሪ ሊያካትት ይችላል።

### 3.1. ተፅዕኖ ያረፈባቸው ወገኖች

በፕሮጀክቱ በአዎንታዊ ሆነ በአሉታዊ መንገድ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ ሊያርፍባቸው የሚችሉ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችን፣ የአካባቢ ማኅበረሰቦችን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ለይቶ ማወቅ። የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) በተለይ በእነዚያ በፕሮጀክቱ እንቅስቃሴዎች በቀጥታ እና በከባድ ሁኔታ ተፅዕኖ ያረፈባቸው ላይ ማተኮር አለበት። በአንድ ጂኦግራፊያዊ ክልል ውስጥ ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ማኅበረሰቦች በማስቀመጥ ተፅዕኖ ያረፈበትን አካባቢ በቀጠና ለይቶ ካርታ ማዘጋጀት ተፅዕኖ የሚያርፍባቸውን አካባቢዎች ለመግለጽ ወይም ለማጣራት ሊያግዝ ይችላል። የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ሌሎች ተፅዕኖ አርፎብናል ብለው ሊያስቡ የሚችሉ ወገኖችን እና የፕሮጀክቱን ተፅዕኖዎች ወሰን ለመረዳት ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የሚያስፈልጋቸውን ወገኖች ለይቶ ማወቅ አለበት።

### 3.2. ሌሎች ጉዳዩየሚመለከታቸው አካላት

በፕሮጀክቱ መገኛ ቦታ፣ ከተፈጥሮ ወይም ሌሎች ሀብቶች ካለው ቅርበት ወይም በፕሮጀክቱ ተሳትፎ ያላቸው ዘርፎች ወይም ወገኖች ምክንያት ጉዳዩ ሊመለከታቸው የሚችል ሰፋት ያላቸው ባለድረሻ አካላትን ለይቶ ማወቅ። እነዚህ የአካባቢው የመንግሥት ባለሥልጣናት፣ የማኅበረሰብ መሪዎች እና ሲቪል የማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ በተለይ ተፅዕኖ ካረፈባቸው ማኅበረሰቦች ጋር ሥራ የሚሠሩ ወይም በማኅበረሰቡ ውስጥ ሥራ የሚሠሩ አካላት ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ቡድኖች በቀጥታ በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ላይደርስባቸው ቢችልም፣ በፕሮጀክት ዝግጅቱ ላይ የራሳቸው ሚና ሊኖራቸው ይችላል (ለምሳሌ ፈቃድ የሚሰጠው መንግሥት) ወይም በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ያረፈበት ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙ እና ከራሳቸው ነፍስወከፍ ቤተሰብ ይልቅ ሰፋ ያለ አሳሳቢ ጉዳይ ሊኖራቸው ይችላል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ ሲቪል ማኅበረሰቦች እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስለ ፕሮጀክቱ አካባቢ እና በአቅራቢያው ስለሚገኙት ሕዝቦች አካባቢያዊ እና ማኅበረሰባዊ ጠባያት ጥልቀት ያለው ዕውቀት ሊኖራቸው ይችላል፤ በመሆኑም ስጋቶችን፣ ሊፈጠሩ የሚችሉ ተፅዕኖዎችን እና ተበዳሪው ከግምት ሊያስገባቸው እና በምዘናው ሂደት ወቅት ሊመለከታቸው የሚገቡ ዕድሎችን

በተመለከተ ለይቶ የማሳወቅ ሚና በመጫወት ሊያግዙ ይችላሉ። አንዳንድ ቡድኖች ፕሮጀክቱ ባለበት ዘርፍ ምክንያት ጉዳዩ ሊመለከታቸው ይችል ይሆናል (ለምሳሌ የማዕድን ማውጣት ሥራ ወይም የጤና እንክብካቤ ሥራ) እና ሌሎች ደግሞ የሕዝብ ገንዘብ ፕሮጀክቱን ለመደገፍ ስለሚውል ብቻ መረጃ ለማግኘት ሊፈልጉ ይችሉ ይሆናል። መረጃው በሕዝብ ጎራ ውስጥ ያለ ከሆነ፣ ለማንም ለማወቅ ፍላጎት ያለው ክፍት መሆን አለበት—ሰዎች ወይም ቡድኖች ለምን ስለ ፕሮጀክቱ መረጃ ማግኘት እንደሚፈልጉ መሠረታዊ ምክንያቱን ለይቶ ማወቅ አስፈላጊ አይደለም።

## 3.3. እኩል ተጠቃሚ መሆን ያልቻሉ / ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች

የፕሮጀክቱን ተፅዕኖዎች ብዙውን ጊዜ የሚያሳስባቸውን ነገር በይፋ ለመናገር በማይችሉ ወይም የፕሮጀክቱን ተፅዕኖዎች ምን እንደሆኑ መረዳት በማይችሉ እኩል ተጠቃሚ መሆን ባልቻሉ ወይም ለጥቃት ተጋላጭ በሆኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ተመጣጣኝ ባልሆነ መንገድ ይበልጥ ተፅዕኖ የሚሳርፍ ከሆነ የፕሮጀክቱን ተፅዕኖዎች መረዳት አስፈላጊ ነው። የሚከተለው የእነዚህን ቡድኖች ዕይታዎች ለመረዳት የሚያስችል የአቀራረብ ዘዴን ለማዘጋጀት ሊያግዝ ይችላል፦

a. እኩል ተጠቃሚ መሆን ያልቻሉ ወይም ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ግለሰቦችን ወይም ቡድኖችን እንዲሁም ተሳትፎ በማድረግ እና/ወይም የፕሮጀክቱን መረጃ በመረዳት ወይም በምክክር ሂደቱ ላይ በመሳተፍ ረገድ ሊኖርባቸው የሚችሉ ውስንነቶችን ለይቶ ማወቅ።

b. እነዚህን ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ምን በታቀደው ሂደት ውስጥ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ሊያግዳቸው ይችላል? (ለምሳሌ የቋንቋ ልዩነቶች፣ በዝግጅቶች ላይ ለመገኘት የትራንስፖርት እጥረት፣ ወደ ክዋኔ ቦታዎች ለመድረስ አለመቻል፣ የአካል ጉዳት፣ የምክክር ሂደቱ ግንዛቤ አለመኖር)።

c. በተለምዶ ስለ ማኅበረሰቡ፣ ፕሮጀክቶች፣ እንቅስቃሴዎች በተመለከተ መረጃ እንዴት ነው የሚያገኙት?

d. ለሕዝባዊ ምክክሩ በተመረጠው ሰዓት ወይም መገኛ አካባቢ በተመለከተ የራሳቸው ውስንነቶች አሉባቸው?

e. እነዚህ ሰዎች በምክክር ሂደቱ እንዲሳተፉ ለማድረግ ምን ተጨማሪ ድጋፍ ወይም ግብዓቶች ሊያስፈልጉ ይችላሉ? (የእዚህ ምሳሌዎች ወደ ሕዳጣኑ ቋንቋ የትርጉም አገልግሎት፣ የምልክት ቋንቋ፣ በትላልቅ ጽሑፎች የታተመ ሰነድ ወይም የብሬል መረጃ ማቅረብ፤ ለዝግጅቶች ተደራሽ የሆኑ ቦታዎችን መምረጥ፤ በቅርብ ቦታ ሊገኝ ወደ የሚችል የስብሰባ ቦታ በሩቅ ቦታዎች ለሚገኙ ሰዎች የትራንስፖርት አገልግሎት ማቅረብ፤ ተጋላጭ የሆኑት ባለድርሻ አካላት ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ወይም የሚያሳስባቸውን ነገር ለመግለጽ ይበልጥ እንዲመቻቸው ትናንሽ፣ የትኩረት ስብሰባዎችን ማድረግ ናቸው።)

f. እንደ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች ካሉ ለጥቃት ተጋላጭ ከሆኑ ቡድኖች ጋር በንቃት ሥር የሚሠሩ ድርጅቶች በፕሮጀክቱ አካባቢ የሌሉ ከሆነ፣ ስለ መድልዎና መገለል የሚደርስባቸው ቡድኖች ማንነት እና እንዴት ከእነርሱ ጋር በተሻለ መንገድ መልእክት መለዋወጥ እንደሚቻል የሚያውቁትን የሕክምን አገልግሎት አቅራቢዎችን ማነጋገር።

g. ከጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ባለድርሻ አክላት እና ተወካዮቻቸው ጋር ፕሮጀክቱ በቅርቡ ምን ዓይነት ግንኙነት ነበረው?

## 3.4. የፕሮጀክት ባለድርሻ አካል ፍላጎቶች አጭር ማጠቃለያ

ምሳሌ

| ማኅበረሰብ | የባለድርሻ አካል ቡድን | ቁልፍ መገለጫ ባሕሪያት | የቋንቋ ፍላጎቶች | ማስታወቂያን ማድረስ የሚቻልበት ተመራጭ መንገድ (ኢሜይል፣ | ልዩ ፍላጎቶች (የአካል ጉዳት ላላቸው ተደራሽነት፣ በትላልቅ ፊደላት የታተመ ጽሑፍ፣ |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| መንደር ሀ | ትናንሽ ሕፃናት ያሏቸው ወላጆች | በግምት 180 ቤተሰቦች ተፅዕኖ ደርሶባቸዋል፤ 300 ሕፃናት | ብሔራዊ ቋንቋ | በጽሑፍ የቀረበ መረጃ፣ ሬዲዮ | በስብሰባዎች ወቅት ለሕፃናት ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ - ከሰዓት |
| መንደር ሀ | ስደተኞች | 38 ዘመድ አዝማዶች፣ የድኅነት ደረጃ | የቋንቋ አማራጭ | ከአስተርጓሚ እና ከሲቪል ማኅበረሰብ ተወካይ ጋር ሆኖ ጉብኝት ማድረግ | ግራፊክስ፣ በመስጠት ላይ ያለ ትምህርት |

## 4. የባለድርሻ አካል ተሳትፎ ፕሮግራም

### 4.1. የባለድርሻ አካል ተሳትፎ ፕሮግራም ዓላማ እና ጊዜ መርሐግብር

የባለድርሻ አካል ተሳትፎ ፕሮግራሙን ዋንኛ ግቦች እንዲሁም ለተለያዩ የባለድርሻ አካል ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች ማለትም በፕሮጀክቱ ዕድሜ ወቅት በሙሉ በየትኛዎቹ ደረጃዎች ላይ ተሳትፎ ይኖራቸዋል፣ በምን ያክል ጊዜ ልዩነት እና የየትኛዎቹ ሰዎች አስተያየቶች እና የሚያሳስቧቸው ነገሮች ላይ ውሳኔ እንደሚሰጥ የታለመውን መርሐግብር በአጭሩ ማስቀመጥ። በሕዝብ ስብሰባዎች፣ የስብሰባ ቦታዎች እና የስብሰባ ሰዓት ላይ እስካሁን ከውሳኔ ላይ ካልተደረሰ፣ ሰዎች መረጃን ለመገምገም እና የራሳቸውን አስተያየት መስጠት እንዲችሉ ወደፊት ስለሚኖሩ ዕድሎች እንዴት እንዲያውቁ እንደሚደረጉ የተወሰነ መረጃን መስጠት። እንደዚህ መረጃ አንድ አካል የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድን (ESCP) ማካተት። ለአንዳንድ ፕሮጀክቶች ለብቻው የተነጠለ የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ማዘጋጀት አስፈላጊ ላይሆን ይችላል እና አባለ ነገሮቹ በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) ውስጥ ሊካተቱ ይችሉ ይሆናል።

### 4.2. መረጃን ይፋ ስለማድረግ እንደሐሳብ የቀረበ ስትራቴጂ

ምን ዓይነት መረጃ ይፋ እንደሚደረግ፣ በምን ዓይነት ቅርጸት እና ይህን መረጃ ለሁሉም ባለድርሻ አካል ቡድኖች በነፍስ ወከፍ ለማስተላለፍ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎችን ዓይነት በአጭሩ ማብራራት። ጥቅም ላይ የሚውሉ ዘዴዎች እንደ ዒላማ የተደረገ ታዳሚ ዓይነት ሊለያዩ ይችላሉ። ለእያንዳንዱ መገናኛ ብዙኃን የራሳቸውን ስሞች ለይቶ ማቅረብ (ለምሳሌ፣ The Daily News እና The Independent፣ Radio News 100.6፣ Channel 44 ቴሌቪዥን)። ለማሳወቅ እና መረጃ ለመስጠት ለሁለቱም—መረጃን ይፋ ማድረጊያ መንገድ ምርጫ—በፕሮጀክቱ አካባቢ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ ሰዎች በተለመዶ መረጃን እንዴት እንደሚያገኙ ላይ መመርኮዝ አለበት እንዲሁም ለብሔራዊ ጥቅም ሲባል ይበልጥ ማዕከላዊ የሆነ መረጃ ምንጭን ሊያካትት ይችል ይሆናል። አብዛኛዎቹን ባለድርሻ አካላት ለመድረስ የተለያዩ የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎች ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። ፕሮጀክቱ ይበልጥ ተገቢነት ያላቸውን መምረጥ አለበት እና ለምርጫው ግልጽ የሆነ ምክንያትም መቀመጥ አለበት። ዕቅዱ እንደ ሐሳብ በቀረበው የተሳትፎ ዕቅድ ላይ የሚሰጡ የእንኳን ደህና መጣችሁ አስተያየቶችን እና ለመሻሻል የሚቀርቡ ጥቆማ ሐሳቦችን ማካተት አለበት። በርቀት ላይ ለሚገኙ ባለድርሻ አካላት፣ ጋዜጣ ወይም የተለየ ስብስባ ወይም ተጨማሪ ሰነድ የሚያገኙበትን ለሕዝብ አመቺ የሆነ ተጨማሪ መንገድ ማቅረብ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። የሕዝብ መረጃ ማግኛ አማራጮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

a. ጋዜጣዎች፣ ፖስተሮች፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፤
b. የመረጃ ማዕከላት እና ዐውደ ርዕዮች ወይም ሌሎች በቀላሉ ሊታዩ የሚችሉ ማሳያ ዘዴዎች፤
c. ብሮሹሮች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ፖስተሮች፣ ቴክኒካዊ ያልሆኑ አጭር ማጠቃለያ የያዙ ሰነዶች እና ሪፖርቶች፤
d. ኦፊሴላዊ የደብዳቤ ልውውጦች፣ ስብሰባዎች፤
e. የድርጣቢያ፣ የማኅበራዊ ግንኙነት አውታር።

ስትራቴጂዎች ተጨማሪ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎች የሚያስከትሉ በፕሮጀክቱ ላይ የሚደረጉ ጉልህ ለውጦች ካሉ በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ካረፈባቸው ባለድርሻ አካላት ጋር መመካከር የሚያስችል ዘዴን ማካተት አለባቸው። እንዲህ ካለ ምክርር በኋላ የተሻሻለው የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ይፋ ይሆናል።

ምሳሌ

| በፕሮጀክት ደረጃ | ይፋ የሚሆን መረጃ ዝርዝር | እንደ ሐሳብ የቀረቡ ዘዴዎች | የጊዜ ሰሌዳ፡- መገኛ አካባቢዎች/ቀናት | ዒላማ የተደረጉ ባለድርሻ አካላት | የተደረሰው መቶኛ | ኃላፊነቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ግንባታ ሥራ | የትራፊክ አስተዳደር ዕቅድ | ማሳወቂያ የሬዲዮ ዜና<br><br>100.6 እና ቅጂ በመንደሩ አዳራሽ<br><br>በማኅበረሰብ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ | መረጃው ይፋ በሚሆንባቸው ሳምንታት በቀን ሁለት ጊዜ ሬዲዮ | መንደርተኞች፣ እግረኞችን እና መኪና ሾፌሮችን ጨምሮ | የሬዲኦ ዜና<br><br>100.6 ከመንደሩ 60% ላይ ደርሷል<br><br>በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ የተለጠፈው ፖስተር የሕዝቡን ሌላኛውን መቶኛ ይደርሳል | የማኅበረሰብ ጉዳይ አስፈጻሚ ኦፊሰር |

## 4.3. ለምክክር እንደ ሐሳብ የቀረበው ስትራቴጂ

ከእያንዳንዳቸው የባለድርሻ አካል ቡድኖች ጋር ለመመካከር ጥቅም ላይ የሚውሉ ዘዴዎችን በአጭሩ ማብራራት። ጥቅም ላይ የሚውሉ ዘዴዎች እንደ ዒላማ የተደረገ ታዳሚ ዓይነት ሊለያዩ ይችላሉ፣ ለምሳሌ፡-

a. ከባለድርሻ አካላት እና ተዛማጅ ድርጅት ጋር የሚደረጉ ቃለ መጠይቆች
b. የዳሰሳ ጥናቶች፣ የሐሳብ ድምፅ መስጫዎች እና መጠይቆች
c. ሕዝባዊ ስብሰባዎች፣ ዐውደ ጥናቶች፣ እና/ወይም በተወሰነ ጉዳይ ላይ ያሉ የትኩረት ቡድኖች
d. አሳታፊ ዘዴዎች
e. ለምክክር እና ለውሳኔ አሰጣጥ ሌሎች ባህላዊ ዘዴዎች።

ምሳሌ

| በፕሮጀክት ደረጃ | የምክክር ርዕሰ ጉዳይ | ጥቅም ላይ የሚውለው ዘዴ | የጊዜ ሰሌዳ፡- ቦታ እና ቀን | ዒላማ የተደረጉ ባለድርሻ አካላት | ኃላፊነቶች |
|---|---|---|---|---|---|
| ግንባታ ሥራ | የትራፊክ ደኅንነት | ከመንደሩ ትምህርት ቤቶች ጋር የሚደረግ ውይይት<br><br>ሕዝባዊ ስብሰባ | ኤቢሲ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሴፕቴምበር 4, 3:00 p.m.<br><br>መንደር ሀ የመንደሩ | በመንደሯ ውስጥ ያሉ ወላጆች እና ሕፃናት<br><br>ማኅበረሰብ | የማኅበረሰብ ግንኙነት ኦፊሰር (CLO)<br><br>የትራንስፖርት ኢንጂነር፣ ሥራ አስኪያጅ፣ የማኅበረሰብ |

### 4.4. ለጥቃት ተጋላጭየሆኑ ቡድኖችንዕይታ ለማካተት እንደ ሐሳብየቀረበስትራቴጂ

ለጥቃት ተጋላጭ ወይም እኩል ዕድል ያላገኙ ቡድኖች ዕይታዎች እንዴት በምክክር ሂደቱ ላይ ሊገኙ እንደሚችሉ ማብራራት። ተሳትፎ የሚያውኩ መሰናክሎችን ለማስወገድ ምን እርምጃዎች ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው? ይህ ለምክክር እና ቅሬታ አቀራረብ የተለዩ ዘዴዎችን፣ ለፕሮጀክት ጥቅማ ጥቅሞች መዳረሻዎችን ለማግኘት የሚያስችሉ ዘዴዎችን ማዘጋጀት እና የመሳሰሉትን ሊያካትት ይችላል።

### 4.5. የጊዜ ሰሌዳዎች

የፕሮጀክት ደረጃዎችን እና ቁልፍ ውሳኔዎችን በተመለከተ ስላለው ጊዜ ሰሌዳ መረጃን ማቅረብ። አስተያየቶች የሚሰጡበትን ቀነ ገደብ መስጠት።

### 4.6 የአስተያየቶች ግምገማ

አስተያየቶች (በጽሑፍ እና በቃል የተሰጡ አስተያየቶች) እንዴት እንደሚሰበሰቡ እና እንደሚገመገሙ ማብራራት እና የመጨረሻውን ውሳኔ በተመለከተ ለባለ ድርሻ አካላት መልሶ ሪፖርት ለማድረግ ቁርጠኝነትን ማሳየት እንዲሁም አስተያየቶች እንዴት ከግምት እንደገቡ የሚያሳይ አጭር ማጠቃለያን መስጠት።

### 4.7 የፕሮጀክቱየወደፊትደረጃዎች

በፕሮጀክቱ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አፈጻጸም ሪፖርት አደራረግ እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ ትግበራ እና የቅሬታ አቀራረብ ዘዴን ጨምሮ ፕሮጀክቱ እያደገ ሲሄድ ሰዎች መረጃ እያገኙ እንደሚሄዱ ማብራራት። ፕሮጀክቶች ለባለድርሻ አካላት ቢያንስ በየዓመቱ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው ሆኖም ግን ብዙውን ጊዜ በተለይ ይበልጥ እንቅስቃሴ በሚኖራቸው ክፍለ ጊዜዎች ላይ፣ ሕዝቡ ይበልጥ ተፅዕኖ ሲያርፍበት ወይም የፕሮጀክቱ ደረጃዎች ሲቀየሩ ይበልጥ በብዛት ሪፖርት ይደረጋል (ለምሳሌ፣ በኮንስትራክሽን ወቅት የሩብ ዓመት ሪፖርቶች፣ ከዚያም በትግበራ ወቅት ዓመታዊ ሪፖርቶች)።

## 5. ለባለድርሻ አካል ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች ግብዓቶች እና ኃላፊነቶች

### 5.1. ግብዓቶች

Iበተለይ የሚከተሉትን ጨምሮ ምን ዓይነቶች ግብዓቶች የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድን ለማስተዳደር እና ለመተግበር ጥቅም ላይ እንደሚውሉ መጠቆም፡-

a. በየባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ላይ ኃላፊነቱን ምን ዓይነት ሰዎች ይወስዳሉ
b. ለባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ በቂ የሆነ በጀት መመደቡን ማረጋገጥ
c. ሰዎች ስለ ፕሮጀክቱ ወይም ስለ ምክክር ሂደቱ አስተያየቶች ወይም ጥያቄዎች ካሉዋቸው የሚጠቀሙባቸውን አድራሻዎች መስጠት፤ እነዚህ አድራሻዎች ስልክ ቁጥር፣ የቢሮ አድራሻ፣ ኢሜይል አድራሻ፣ የኃላፊው ግለሰብ የሥራ ማዕረግ (የግለሰብ ስሞች ሊለወጡ ስለሚችሉ መጥቀሱ ብዙም አስፈላጊ አይደለም)።

### 5.2. የአስተዳደር ተግባራት እና ኃላፊነቶች

የባለ ድርሻ አካል ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች በፕሮጀክት አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ እንዴት ሊካተቱ እንደሚችሉ ማብራራት እና የባለድርሻ አካል ተሳትፎ ዕቅድ አስተዳደር እና ትግበራ ላይ ምን ዓይነት ሠራተኞች እንደሚመደቡ መጠቆም፡-

a. ለባለድርሻ አካል ተሳትፎ እያንዳንዱ እንቅስቃሴዎች ክወና ማን ኃላፊነቱን ይወስዳል እንዲሁም የእነዚህ ኃላፊነቱን የሚወስዱ አካላት የትምህርት ደረጃ እና የሥራ ልምድ ምንድን ነው?

b. በባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ላይ ከፍተኛው አመራር ምን ያክል ተሳትፎ ይኖረዋል?

c. ሂደቱ እንዴት በሰነድ ይያዛል፣ እንዴት ክትትል ይደረግበታል እንዲሁም እንዴት ይተዳደራል (ለምሳሌ፡- የባለድርሻ አካል የመረጃ ቋት፣ የኃላፊነትና ግዴታ መዝገብ፣ እና የመሳሰሉት)?

## 6. የቅሬታአቀራረብዘዴ

በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ያረፈባቸው ሰዎች አቤቱታዎቻቸውን እና የሚያሳስቧቸውን ነገሮች ለፕሮጀክት አስተዳደር ትኩረት እንዲሰጥባቸው ማምጣት የሚችሉበትን ሂደት እና አቤቱታቸው እንዴት ከግምት እንደሚገባ እና መፍትሔ እንደሚሰጠው ማብራራት፡-

a. ቀደም ብሎ የነበረ መደበኛ ወይም ኢመደበኛ የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ አለ እና ይህ ዘዴስ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS10) መስፈርቶችን የሚያሟላ ነው? ካለው ሁኔታ ጋር ሊጣጣም የሚችል ነው ወይስ አዲስ የሆነ ነገር መቋቋም ይኖርበታል?

b. የቅሬታ አቀራረብ ዘዴው በባህል ዓይን ሲታይ አግባብነት ያለው ነው፣ ይህም ማለት ማኅበረሰቡን የሚያሳስቡትን ነገሮች ለማስተናገድ በባህል ተቀባይነት ያላቸውን መንገዶች ከግምት ለማስገባት በሚያስችለው መልኩ የተዘጋጀ ነው? ለምሳሌ ወንዶች እና ሴቶች ለየብቻ ስብሰባ በሚያደርጉባቸው ባህሎች ውስጥ አንዲት ሴት በፕሮጀክቱ የቅሬታ አቀራረብ ሂደት ውስጥ ላለች ሌላ ሴት የሚያሳስባትን ነገር ማቅረብ ትችላለች?

c. ቅሬታዎችን እና የሚያሳስቡ ነገሮችን በሰነድ ለመያዝ ምን ዓይነት ሂደት ጥቅም ላይ ይውላል? የሕዝብ አቤቱታዎችን ማን ይቀበላል? አቤቱታዎቹ እንዴት ይመዘገባሉ እና እንዴት ክትትል ይደረግባቸዋል?

d. መቀበል እና ችግሮችን መፍትሔ ለመስጠት ምን ዓይነት የጊዜ ገደብ ቁርጠኝነት ለአቤቱታ አቅራቢዎች ቃል ይገባል? በሂደቱ ላይ በሙሉ ከአቤቱታ አቅራቢዎች ጋር ቀጣይ የሆነ የመልእክት ልውውጥ ይኖራል?

e. የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ እንዳለ ለሁሉም ባለድርሻ አካል ቡድኖች እንዴት መልእክቱ እንዲደርሳቸው ይደረጋል? ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ባለድርሻ አካላት የተለዩ ሂደቶችን መጠቀም ያስፈልጋል?

f. አቤቱታ ወይም ቅሬታ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግበት የማያስፈልገው ሆኖ ከታመነበት፣ ለምን ከዚያ በላይ መቀጠል እንደማይችል ለአቤቱታ አቅራቢው ማብራሪያ ይሰጠዋል?

g. አቤቱታ አቅራቢው በቀረበለት የመፍትሔ ሐሳብ ደስተኛ ካልሆነ ይግባኝ ሊጠየቅ የሚችልበት የአሠራር ሂደት አለ? ሁሉም ፕሮጀክቶች የይግባኝ ሰሚ ሂደት ይኖራቸዋል ማለት አይደለም ሆኖም ግን ይበልጥ ውስብስብ ለሆኑ ፕሮጀክቶች አንድ ይግባኝ ሰሚ አካል እንዲኖር ይመከራል። በሁሉም ጉዳዮች ላይ፣ አቤቱታ አቅራቢዎች በአገራቸው የሕግ ሥርዓት ሥር ሁሉም ሕጋዊ መብቶቻቸው የተጠበቁላቸው መሆናቸውን ማረጋገጫ ሊሰጣቸው ይገባል።

h. የቅሬታ አቅራቢዎችን ማንነት ጥበቃ ለማድረግ ማንነትን ለይቶ ሊያሳውቅ የሚችለው የመረጃ ክፍል ከተወገደ በኋላ የቅሬታ አቀራረብ ዘዴው አፈጻጸም አጭር ማጠቃለያ በመደበኛነት ለሕዝቡ መስጠት ይኖርበታል። ሂደቱ እየተፈጸመ ያለ ስለ መሆኑ ለማሳየት ሪፖርቶቹ ለሕዝብ በምን ያክል ጊዜ ብዛት ይፋ መሆን አለባቸው?

## 7. ክትትል እና ሪፖርት አደራረግ

### 7.1. በክትትል እንቅስቃሴዎች ላይ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ

አንዳንድ ፕሮጀክቶች ፕሮጀክት ላይ ወይም ከፕሮጀክቱ ጋር በተገናኙ ተፅዕኖች ላይ ክትትል በማድረግ ሥራ ላይ ሦስተኛ ወገኖችን ያሳትፋሉ። በፕሮጀክት እና በፕሮጀክት ተፅዕኖዎች እንዲሁም በማስታረቂያ ፕሮግራሞች ላይ ክትትሎችን ለማድረግ የፕሮጀክት ባለድረሻ አካላትን (ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ማኅበረሰቦች ጨምሮ) ወይም ሦስተኛ ወገን ለማሳተፍ ያሉ ማናቸውንም ዕቅዶች ማብራራት። የሦስተኛ ወገኖች መምረጫ መስፈርት ግልጽ መሆን አለበት። ለተጨማሪ መረጃ የዓለም ባንክን የሦስተኛ ወገን ክትትል አደራረግ የመልካም አሠራር ማስታወሻ ይመልከቱ።

## 7.2. ለባለድርሻ አካል ቡድኖች መልሶ ሪፖርት ማድረግ

የባለድርሻ አካል እንቅስቃሴዎችን ውጤቶች እንዴት፣ መቼ እና የት ተመልሰው ተፅዕኖ ላረፈባቸው ባለድርሻ አካላት እና መጠነ ሰፊ ይዘት ላላቸው የባለ ድርሻ አካላት ቡድኖች ሪፖርት እንደሚደረጉ ማብራራት። እነዚህ ሪፖርቶች ባለድርሻ አካላትን ለማሳወቅ ከዚህ ቀደም ጥቅም ላይ የዋሉትን የመልእክት ማስተላለፊ ተመሳሳይ ዘዴዎች በመጠቀም እንዲተላለፉ ይመከራል። ባለድርሻ አካላት ሁልጊዜ የቅሬታ አቀራረብ ዘዴው እንዳለ እንዲያስታውሱ መደረግ አለባቸው።

## ዓባሪ 4፡- የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘና (ESIA) እና የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ጠቋሚ ቢጋሮች

በፕሮጀክቱ የሕይወት ዑደት ላይ በጠቅላላ የፕሮጀክቱን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ለመመዘን ተበዳሪው አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናን ያከናውናል። 'አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘና' የሚለው አባባል የአንድ ፕሮጀክት አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ተለይተው መታወቃቸውን፣ ማስቅረት መቻላቸውን፣ መቀነሳቸውን፣ መገታታቸውን ወይም መፍትሔ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ በተበዳሪው ጥቅም ላይ የሚውለውን የትንታኔ አሰጣጥ እና ዕቅድ አወጣጥ ሂደት የሚያብራራ ለዚህ ተብሎ የተፈጠረ አባባል ነው።

አካባቢያዊ እን ማኅበራዊ ምዘና ፕሮጀክቶች በአካባቢያዊ እና በማኅበራዊ ጎናቸው ሲታዩ ተቀባይነት ያላቸው እና ዘላቂታማነት ያላቸው መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዋንኛ ዘዴዎች ሲሆኑ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ መረጃ ለማግኘት ጥቅም ላይ ይውላሉ። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናው የተለያዩ መሣሪያዎችን እና ዘዴዎችን እንደ ፕሮጀክቱ ዝርዝሮች እና እንደ ተበዳሪው ሁኔታዎች የሚጠቀም እንደ አስፈላጊነቱ ሊለዋወጥ የሚችል ሂደት ነው።

አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናው በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1) መሠረት ይከናወናል እና በተለይ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1)–10 ላይ ተለይተው የተቀመጡትን ጨምሮ ሁሉንም ተዛማጅነት ያላቸው ቀጥተኛ፣ ተዘዋዋሪ እና ድምር የፕሮጀክቱን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎችን በተቀናጀ መልኩ ከግምት ያስገባል። እንደ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘና አንድ አካል የሚደረገው ትንታኔ ስፋት፣ ጥልቀት እና ዓይነት በፕሮጀክቱ ተፈጥሮ እና ደረጃ እንዲሁም ሊያስከትል የሚችላቸው አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ላይ የሚመረኮዝ ይሆናል። ተበዳሪው ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች አንጻር መሳ ለመሳ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ምዘናውን ደረጃ በማስተካከል ምዘናውን የሚያከናውን ይሆናል።

አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናው የሚከናወንበት መንገድ እና መፍትሔ የሚሰጣቸው ችግሮች ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት የተለያዩ ይሆናሉ። የአፈጻጸም ወሰንን፣ የባለድርሻ አካል ተሳትፎችን፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ችግሮች እና ማናቸውም በባንኩ እና በተበዳሪው መካከል የተነሡ ማናቸውም ተለይተው የታወቁ ችግሮችን ጨምሮ ያሉትን እንቅስቃሴዎች ከግምት በማስገባት ጥቅም ላይ የሚውለውን ሂደት ለመመካከር ተበዳሪው ከባንኩ ጋር ይመካከራል። ሁሉም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ጉልህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ተለይተው መታወቃቸውን እና መፍትሔ ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናው ተፅዕኖ ካረፈባቸው ሰዎች እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ጋር ቅንጅት መፍጠር እና ምክክር ማድረግን ያካትታል እንዲሁም ከግምት ውስጥ ያስገባል።

አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘና ለማከናወን እና ምዘናውን በሰነድ ለመያዝ በተበዳሪው ጥቅም ላይ የሚውሉት የተለያዩ ዘዴዎች እና መሣሪያዎች እንዲሁም ተፈጻሚ የሚሆኑት የማስታረቂያ እርምጃዎች ጨምሮ የፕሮጀክቱን ተፈጥሮ እና ደረጃ የሚያንፀባርቁ ይሆናሉ። በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1) ላይ እንደተጠቀሰው እንደተገቢነቱ እነዚህ የሚከተሉትን ውህድ ወይም አባለ ነገራት የሚያካትቱ ይሆናሉ፡-

### a. የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘና (ESIA)

የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘና (ESIA) የአንድን እንደ ሐሳብ የቀረበ ፕሮጀክት ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎች፣ ለይቶ ለማወቅ እና ለመመዘን፣ አማራጮችን ለመመርመር፣ እና ተገቢነት ያላቸውን ማስታረቂያ፣ አስተዳደራዊ እና የክትትል እርምጃዎች ዲዛይን ለማድረግ የሚያስችል መሣሪያ ነው።

### b. አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ኦዲት

አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ኦዲት በአንድ በክንውን ላይ ያለ ፕሮጀክት ወይም እንቅስቃሴዎች ሁሉንም አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋት አካባቢዎች ተፈጥሮ እና መጠነ ስፋት ለማወቅ የሚያገለግል መሣሪያ ነው። ኦዲቱ አሳሳቢ አካባቢዎችን ለማስታረቅ አስፈላጊ የሆኑ ተገቢነት ያላቸው እርምጃዎችን እና ሥራዎችን ለይቶ ያወጣል እንዲሁም ምክንያታቸውን ያቀርባል እንዲሁም የእነዚህን እርምጃዎች እና ማስተካከያ ሥራዎች ወጪ ግምት ይሰጣል፣ እና የሚፈጸሙበትን የጊዜ መርሐግብር በምክረሐሳብ ደረጃ ያቀርባል። ለአንዳንድ የተወሰኑ ፕሮጀክቶች አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናው የአካባቢ ወይም ማኅበራዊ ኦዲትን ለብቻው ሊይዝ ይችላል፤ በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ፣ ኦዲቱ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናው አንድ አካል ይሆናል።

## c. የአደጋ ወይም የአደጋ ስጋት ምዘና

የአደጋ ወይም የአደጋ ስጋት ምዘና በፕሮጀክቱ የሥራ ቦታ ላይ ባሉ አደገኛ ማቴሪያሎች እና ሁኔታዎች ምክንያት የሚፈጠሩ የአደጋ ስጋቶችን ለይቶ ለማወቅ፣ ትንታኔ ለመስጠት እና ለመቆጣጠር የሚያስችል መሣሪያ ነው። ተቀጣጣይ፣ ፈንጂ፣ ጨረር እና መርዛማ ማቴሪያሎች ከተጠቀሰው መባቻ ደረጃ በላይ በብዛት የሚገኙባቸው ፕሮጀክቶች ላይ የአደጋ ወይም የአደጋ ስጋት ምዘና እንዲደረግ ባንኩ ያስገድዳል። ለአንዳንድ የተወሰኑ ፕሮጀክቶች የአካባቢ እና ማኅበራዊ ምዘናው የአደጋ ወይም የአደጋ ስጋት ምዘና ለብቻው በውስጡ ሊይዝ ይችላል፤ በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ የአደጋ ወይም የአደጋ ስጋት ምዘናው የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናው አንድ አካል ይሆናል።

## d. ድምር የተፅዕኖ ምዘና

ድምር የተፅዕኖ ምዘና የፕሮጀክቱን ድምር ተፅዕኖዎች ከሌሎች ተዛማጅነት ያላቸው ያለፍ፣ አሁን ያሉ እና በበቂ ምክንያት ሊገመቱ ከሚችሉ ወደፊት የሚኖሩ ዕድገቶች አንጻር የሚፈጠሩ ተፅዕኖዎች ጋር በጥምረት እንዲሁም ያልታቀዱ ሆኖም ግን በፕሮጀክቱ ምክንያት ሊፈጠሩ ኣንደሚችሉ የሚገመቱ በኋላ ላይ ወይም በተለየ ሌላ ቦታ ላይ የሚያጋጥሙ ተፅዕኖዎችን ከግምት ለማስገባት ጥቅም ላይ የሚውል መሣሪያ ነው።

## e. የማኅበራዊ እና የግጭት ትንታኔ

የማኅበራዊ እና የግጭት ትንታኔ ፕሮጀክቱ (ሀ) (በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ባረፈባቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ እና በእነዚህ ማኅበረሰቦች እና በሌሎች መካከል)በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ውጥረቶችን እና የእኩልነት አለመኖር ችግሮችን የሚያባብስ መሆን ስለመቻሉ፤ (ለ) በሰው ልጅ ደኅንነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያለው ስለመሆኑ፤ (ሐ) አሁን ባሉ ውጥረቶች፣ ግጭት እና አለመረጋጋት፣ በተለይ ጦርነት፣ ሕዝባዊ ዐመፅ ወይም ሁከት ባለባቸው ሁኔታዎች አሉታዊ ተፅዕኖ ይደርስበት እንደሆነ እስከምን ደረጃ ሁኔታው ሊደርስ እንደሚችል ለመመዘን የሚያስችል መሣሪያ ነው።

## f. የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅድ (ESMP)

የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅድ (ESMP)) (ሀ) አሉታዊ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎችን ለማስቀረት ወይም ለመቋቋም ወይም ተቀባይነት እስካለው ደረጃ ድረስ ለመቀነስ በፕሮጀክት ትግበራ እና ክወና ወቅት መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች፤ እና (b) እነዚህን እርምጃዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎች በዝርዝር የሚያብራራ መሣሪያ ነው።

## g. የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ማዕቀፍ (ESMF)

የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ማዕቀፍ (ESMF) አንድ ፕሮጀክት ፕሮግራም እና/ወይም ተከታታይነት ያላቸው ንኡስ ፕሮጀክቶችን የያዘ በሚሆንበት ጊዜ እና ስጋቶቹ እና ተፅዕኖዎቹ ፕሮግራሙ ወይም ንኡስ ፕሮጀክቱ ዝርዝሮች ተለይተው እስከሚታወቁ ድረስ ሊታወቁ ሳይችሉ ሲቀሩ ያሉትን ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ለመመርመር የሚያስችል መሣሪያ ነው።

የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ማዕቀፍ (ESMF) አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎችን ለመመዘን የሚያስችሉ መርሆዎችን፣ ደንቦችን እና የአሠራር ሥርዓቶችን ያቀርባል። አሉታዊ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ፣ ለማስታረቅ እና/ወይም ለመቋቋም የሚያስችሉ እርምጃዎችን፣ እንዲህ ያሉት እርምጃዎችን ወጪዎችን ለመገመት እና በጀት ለመመደብ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን፣ እንዲሁም የአንድ ፕሮጀክት አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎችን ለመቆጣጠር ያለውን አቅም ጨምሮ የፕሮጀክትን ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች መፍትሔ መስጠት ኃላፊነት ያለበትን ወይም ያለባቸውን ኤጀንሲ ወይም ኤጀንሲዎች በተመለከተ መረጃ በውስጡ የያዘ ነው። የአካባቢውን ማናቸውም ሊያጋጥም የሚችል አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ የአደጋ ተገላጭነት እና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተፅዕኖዎች እንዲሁም ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ ተብለው የሚታመኑ የማስታረቂያ እርምጃዎችን ጨምሮ ንኡስ ፕሮጀክቶች የት ቦታ ላይ መሆን እንዳለባቸው በቂ መረጃ በውስጡ የያዘ ነው።

እንደ የዳግም ማቋቋም ዕቅድ፣ ኑሮን ወደ ነበረበት የመመለስ ዕቅድ፣ የአገር ተወላጆች ዕቅድ፣ የብዝኃ ሕይወት የድርጊት መርሐ ግብር፣ የባህላዊ ቅርሶች አስተዳደር ዕቅድ እና ሌሎች ከባንኩ ጋር ስምምነት የሚደረስባቸውን ዕቅዶች የመሳሰሉ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ ዘዴዎችን እና መሣሪያዎችን የአንድ ፕሮጀክት የተወሰኑ ባሕሪያት ተበዳሪው እንዲጠቀም ሊያስገድዱት ይችላሉ።

ተበዳሪዎች በፕሮጀክት ክንውን ሂደት ወቅት በተቻለ ፍጥነት ቶሎ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናውን መጀመር አለባቸው። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናው ገና ከመጀመሪያው በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት እንዲችል ተደርጎ እንዲዘጋጅ ተበዳሪዎች በተቻለ ፍጥነት በቶሎ ከባንኩ ጋር መመካከር ይኖርባቸዋል።

**የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘና (ESIA) ጠቋሚ ቢጋር**

እንደ የአካባቢ እና ማኅበራዊ ምዘና አንድ አካል የአካባቢ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘና ሲዘጋጅ

የሚከተሉትን ያካትታል፡-

a. ልዩ አጭር ማጠቃለያ
   - በጉልህ የሚታዩ ግኝቶችን እና የሚመከሩ እርምጃዎችን በአጭሩ ያብራራል።

b. ሕጋዊ እና ተቋማዊ ማዕቀፍ
   - አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1) ጨምሮ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናው የሚካሄድበትን የፕሮጀክቱን ሕጋዊ እና ተቋማዊ ማዕቀፍ ትንታኔ ይሰጣል።
   - የተበዳሪውን አሁን ያለውን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ እንዲሁም አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ያነጻጽራል እንዲሁም በመካከላቸው ያለውን ክፍተት ለይቶ ያወጣል።
   - ለማናቸውም ተባባሪ ገንዘብ አቅራቢዎች አካባቢያዊ ኣን ማኅበራዊ መስፈርቶችን ለይቶ ያስቀምጣል እንዲሁም ይመዝናል።

c. የፕሮጀክት ዝርዝር መግለጫ
   - ከሥራ ቦታው ውጭ ሊያስፈልጉ የሚችሉ ኢንቨስትመንቶችን (ለምሳሌ ለፕሮጀክቱ ተብሎ የሚዘረጉ የውሃ ቧንቧ መሥመሮች፣ መዳረሻ መንገዶች፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት፣ የውሃ አቅርቦት፣ መጠለያ ቤቶች እና ጥሬ ዕቃና የምርት ማከማቻ ተቋማት) እንዲሁም የፕሮጀክቱን ተቀዳሚ አቅራቢዎች ጨምሮ እንደ ሐሳብ የቀረበውን ፕሮጀክት እና ጂኦግራፊያዊ፣ አካባቢያዊ፣ ማኅበራዊ እና ጊዜያዊ ዓውዱን እጥር ምጥን ባለ መንገድ ያብራራል።

- የፕሮጀክቱን ሁሉንም ዝርዝሮች ከግምት በማስገባት የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1) እስከ 10 ያሉትን መስፈርቶች ለማሟላት ማናቸውም ዕቅድ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ይጠቁማል።
- የፕሮጀክቱን የሥራ ቦታ እና በፕሮጀክቱ በቀጥታ፣ በተዘዋዋሪ እና በድምር ተፅዕኖዎች ተፅዕኖ ሊያርፍበት የሚችለውን አካባቢ ከበቂ ዝርዝር ጋር የሚያሳይ ካርታን ያካትታል።

d. መሠረታዊ መነሻ መረጃ

- ስለ ፕሮጀክቱ ቦታ፣ ዲዛይን፣ ክዋኔ ወይም የማስታረቂያ እርምጃዎች በተመለከተ ከሚሰጡ ውሳኔዎች ጋር ተዛማጅነት ያለው የመሠረታዊ መረጃ ዝርዝሮችን ያስቀምጣል። ይህ የመረጃውን ትክክለኛነት፣ አስተማማኝነት እና ምንጮች በተመለከተ የሚደረግ ውይይት እና እንዲሁም በፕሮጀክት ልየታ፣ ዕቅድ አወጣጥ እና ትግበራ ዙሪያ ያሉ ቀናትን በተመለከተ ያለ መረጃን ማካተት አለበት።
- ሊገኝ የሚችል መረጃ መጠነ ስፋት እና ጥራት፣ ዋንኛ የመረጃ ክፍተቶች እና ከግምቶቹ ጋር የተቆራኙ ጥርጣሬዎችን ለይቶ ያስቀምጣል እንዲሁም ግምቱን ይሰጣል።
- አሁን ባለው መረጃ ላይ በመመርኮዝ፣ የሚጠናውን አካባቢ መጠነ ስፋት ይመዝናል እንዲሁም ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብለው የሚጠበቁ ማናቸውንም ለውጦች ጨምሮ ተዛማጅነት ያላቸው አካላዊ፣ ባዮሎጂካዊ እን ሶሺዮኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ያብራራል።
- በፕሮጀክቱ አካባቢ ውስጥ ሆነው ሆኖም ግን ከፕሮጀክቱ ጋር በቀጥታ ያልተገናኙ አሁን ያሉ እና እንደ ሐሳብ የቀረቡ የልማት እንቅስቃሴዎችን ከግምት ያስገባል።

e. አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች

- ሁሉንም ተዛማጅነት ያላቸው የፕሮጀክቱን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ከግምት ያስገባል። ይህ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት ከ2 እስከ 8 (ESS2–8) ተለይተው የተቀመጡትን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች እና በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1) ውስጥ ተለይተው የተቀመጡ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎችን ጨምሮ ሌሎች ማናቸውም በፕሮጀክቱ ለየት ያለ ባሕሪ እና ዓውድ ምክንያት የሚፈጠሩ አካባቢያዊእና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች የሚያካትት ይሆናል።

f. የማስታረቅ እርምጃዎች

- ማስታረቂያ እርምጃዎችን እና በጉልህ የሚታዩ ማስታረቂያ እርምጃ ሊወሰድባቸው የማይችሉ የተረፈ ምርትና ግንባታ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለይቶ ያወጣል እንዲሁም በተቻለ መጠን የእነዚህን ተረፈ ምርቶች አሉታዊ ተፅዕኖዎች ተቀባይነት ደረጃን ይመዝናል።
- መጥፎ ተፅዕኖዎች እኩል ዕድል በማያገኙ ወይም ለጥቃት ተጋላጭ በሆኑ ወገኖች ላይ ከመጠን በላይ ጫና እንዳያሳርፉባቸው የተለያዩ እርምጃዎችን ለይቶ ያስቀምጣል።
- የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎችን ማስታረቂያ እርምጃ መውሰድን አዋጭነት፣ እንደ ሐሳብ የቀረቡት ማስታረቂያ እርጃዎች የሚያስፈልጋቸው ካፒታል እና በተከታታይ የሚወጡ ወጪዎች፣ እና በአካባቢ ሁኔታዎች አንፃር ሲታዩ ያላቸው ዘላቂነት፣ እና እንደ ሐሳብ ለቀረቡት እርምጃዎች ተቋማዊ፣ የሥልጠና እና የክትትል መስፈርቶችን ይመዝናል።
- ለዚህ ውሳኔ ምክንያት የሆኑትን መሠረቶች በማስቀመጥ ተጨማሪ ትኩረት የማያስፈልጋቸውን ችግሮች ያስቀምጣል።

g. የአማራጮች ትንታኔ

- እንደ ሐሳብ ለቀረበው የፕሮጀክት ቦታ፣ ቴክኖሎጂ፣ ዲዛይን እና ክዋኔ ያሉትን አዋጭ አማራጮች በዘዴ ያነጻጽራል—ይህም “ከፕሮጀክት ውጭ” ያሉ ሁኔታዎችን ያካትታል—ባላቸው አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎች አንፃር እየታየ።
- የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎችን ማስታረቂያ እርምጃ መውሰድን አዋጭነት፣ አማራጭ ማስታረቂያ እርጃዎች የሚያስፈልጋቸው ካፒታል እና በተከታታይ የሚወጡ ወጪዎች፣ እና በአካባቢ ሁኔታዎች አንፃር ሲታዩ ያላቸው ዘላቂነት፣ እና አማራጭ እርምጃዎች ተቋማዊ፣ የሥልጠና እና የክትትል መስፈርቶችን ይመዝናል።
- ለእያንዳንዳቸው አማራጮች፣ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎችን እስከተቻለው ርቀት ድረስ በመጠን ለይቶ ያስቀምጣል እንዲሁም አዋጭ ሆኖ በሚገኝበት ቦታ ላይ ኢኮኖሚያዊ እሴቶችን ያያይዛል።

h. የዲዛይን እርምጃዎች

- አንድን የተወሰነ እንደ ሐሳብ የቀረበ ፕሮጀክት ዲዛይን የሚመረጥበትን ምክንያት ያስቀምጣል እንዲሁም ተገቢነት ያላቸውን አካባቢያዊ፣ ጤና ነክ እና የደኅንነት መመሪያ ደንቦች (EHSGs) ይጠቅሳል ወይም የአካባቢ፣ ማኅበራዊ እና ደኅንነት መመሪያዎች (ESHGs) ተገቢነት እንደሌላቸው ከተቆጠሩ፣ ለብክለት ቁጥጥር እና ትግል የሚመከሩ የልቀት ደረጃዎችን እና ዘዴዎችን ምክንያቶች ከ የዓለምአቀፍ ኢንዱስትሪ አሠራር (GIIP) ጋር በሚጣጣም መልኩ ያቀርባል።

i. የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ቁልፍ እርምጃዎች

- የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) መስፈርቶችን ፕሮጀክቱ እንዲያሟላ የሚያስችሉ ቁልፍ እርምጃዎችን እና የጊዜ ማዕቀፍን በአጭሩ ያቀርባል። ይህ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) በማዘጋጀት ላይ ጥቅም ላይ ይውላል።

j. ዓባሪዎች

- በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናውን ያዘጋጁ ወይም ተሳትፎ ያደረጉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ዝርዝር።
- ዋቢዎች—ጥቅም ላይ የዋሉ ሁለቱንም የታተሙ እና ያልታተሙ በጽሑፍ የተዘጋጁ ማቴሪያሎችን ዝርዝር ማስቀመጥ።
- የስብሰባዎች፣ የምክክሮች እና ተፅዕኖ ባረፈባቸው ሰዎች እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ላይ የሚደረገውን ጨምሮ በባለድርሻ አካላት ላይ የሚደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች ሪኮርድ። ሪኮርዱ ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ሰዎች እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች አስተያየቶችን ለማግኘት ጥቅም ላይ የዋሉትን እንዲህ ያሉ የባለድርሻ አካል ተሳትፎን ማረጋገጫ ዘዴዎችን ይጠቅሳል።
- ዋቢ የሚጠቀሰውን አግባብነት ያለው መረጃ ወይም በዋናው ጽሑፍ በአጭሩ የቀረበውን የሚወክሉ ሠንጠረዦች።
- ተዛማጅነት ያላቸው ሪፖርቶች ወይም ዕቅዶች ዝርዝር።

**የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘና (ESMP) ጠቋሚ ቢጋር**

አስከፊ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶችን እና ተፅዕኖዎችን ለማስወገድ፣ ለመቋቋም ወይም ተቀባይነት እስካለው ደረጃ ድረስ እንዲቀንሱ ለማድረግ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) በትግበራ እና በፕሮጀክቱ ክዋኔ ወቅት የሚወሰዱ የማረቂያ፣ የክትትል፣ እና ተቋማዊ እርምጃዎች ስብስብን ይይዛል። የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) በተጨማሪ እነዚህን እርምጃዎች ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን ያካትታሉ። ተበዳሪው (ሀ) አስከፊ ሊሆኑ ለሚችሉ ተፅዕኖዎች ሊሰጡ የሚችሉ ምላሾችን ለይቶ ያውቃል፤ (ለ) እነዚህ ምላሾች በውጤታማ መንገድ እና ጊዜያቸውን

ጠብቀው መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ይወስናል፤ እንዲሁም (ሐ) እነዚያን መስፈርቶች ለማሟላት የሚያስችሉ ዘዴዎችን ያብራራል።

በፕሮጀክቱ ላይ በመመርኮዝ፣ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) እንደ ራሱን የቻለ ሰነድ ብቻውን ሊዘጋጅ ይችላል ወይም ይዘቱ በቀጥታ ወደ የአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) እንዲካተት ሊደረግ ይችላል። የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ይዘት የሚከተሉትን የሚያካትት ይሆናል፡-

a. ማስታረቅ
   - የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅድ (ESMP) ሊያጋጥም የሚችል አስከፊ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎች ተቀባይነት እስካለው ደረጃ ድረስ ለመቀነስ በሚያስችለው የማስታረቂያ ተዋረድ መሠረት ሊወሰዱ የሚችሉ እርምጃዎችን ለይቶ ያስቀምጣል። ዕቅዱ የሚቻል ከሆነ አስገዳጅ እርምጃዎችንም የሚያካትት ይሆናል። በተለይ፣ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP)፡- (i) ሁሉንም ይደርሳሉ ተብለው የሚገመቱ አስከፊ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎች (የአካባቢ ተወላጆችን ወይም በፈቃደኝነት ላይ ያልተመረኮዙ ሰፈራዎችን ጨምሮ) ለይቶ በማውጣት በአጭሩ ማጠቃለያ ይሰጣል፤ (ii) ከቴክኒክዊ ዝርዝሮች ጋር—ተዛማጅነት ካለው ተፅዕኖ ዓይነት እና እርምጃው ያስፈለገበት ሁኔታዎች ጨምሮ (ለምሳሌ በቀጣይነት ወይም ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉ ሊገመቱ የማይችሉ ነገሮች ሲያጋጥሙ)፣ እንደተገቢነቱ ከዲዛይን፣ የመሣሪያና ማሽን ማብራሪያዎች እና የሥራ ከንውን መመሪያዎች ጋር እያንዳንዱን ማስታረቂያ እርምጃ—ያብራራል፤ (iii) የእነዚህን የሚወሰዱ እርምጃዎች ማናቸውንም አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎች ይገምታል፤ እና (iv) ለፕሮጀክቱ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች የማስታረቂያ እርምጃዎችን ከግምት ያስገባል እንዲሁም ከእነርሱም ጋር በሚጣጣም መልኩ ይቀርባል (ለምሳሌ፡- በፈቃደኝነት ላይ ያልተመረኮዘ ሰፈራ፣ የአካባቢው ተወላጆች ወይም የባህል ቅርሶች)።

b. ክትትል
   - የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዱ (ESMP) በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘና ውስጥ የተፈተሹ ተፅዕኖዎች እና በየአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅድ (ESMP) ውስጥ ከተብራሩት የማስታረቂያ እርምጃዎች ጋር የክትትል ዓላማዎችን ለይቶ ያቀርባል እንዲሁም የክትትሉን ዓይነት በግልጽ ያስቀምጣል። በተለይ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዱ (ESMP) የክትትል ክፍል የሚከተሉትን ያቀርባል፡- (ሀ) የሚለኩ መስፈሪያ ልኬቶች፣ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዘዴዎች፣ ናሙና የሚወሰድባቸው ቦታዎች፣ ልኬቶቹ የሚከናወኑባቸው ድግምግሞሾች፣ የፈልን ማግኘት ውስንነቶች (ተገቢነት ሲኖረው)፣ እና ማስተካከያ ኣርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ የሚያመላክቱ መባቻዎች ትርጓሜ ጨምሮ የክትትል እርምጃዎች የተወሰነ ዝርዝር መግለጫን እና ቴክኒካዊ ዝርዝሮች፤ እና (ለ) የሚከተሉትን ለማድረግ የሚያስፈልጉ የክትትል እና የሪፖርት አደራረግ አሠራር ሥርዓቶች፡- (i) አንድን የተወሰነ የማስታረቂያ እርምጃ አስፈላጊነት የሚያጠናክሩ ሁኔታዎችን በጊዜ ለይቶ ለማወቅ መቻሉን ለማረጋገጥ፣ እና (ii) በማስታረቂያው እርምጃ ግሥጋሤ እና ውጤቶች ላይ መረጃን ለማቅረብ።

c. የአቅም ግንባታ እና ሥልጠና
   - ወቅቱን በጠበቀ መልኩ እና የአካባቢ እና ማኅበራዊ ክፍለ አካላት እና ማስታረቂያ እርምጃዎች ውጤታማ ትግበራን ለማከናወን ድጋፍ መስጠት እንዲቻል የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዱ (ESMP) በሥራ ቦታው ላይ ያሉ ኃላፊነት ያለባቸው ወገኖችን ወይም በኤጀንሲ እና በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ደረጃ ያሉ ኃላፊዎችን መኖር፣ ሚና እና አቅም ይጠቀማል።

   - በተለይ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዱ (ESMP) የማስታረቂያ እና የክትትል እርምጃዎቹን (ለምሳሌ ከወናው፣ ክትትሉ፣ ሕግ ማስፈጸሙ፣ የአፈጻጸም ክትትሉ፣ የእርምት እርምጃዎቹ፣ ፋይናንስ አቅርቦቱ፣ ሪፖርት

አደራረጉ እና የሠራተኞች ሥልጠናው) የትኛው ወገን የማከናወን ኃላፊነት እንዳለበት ለይቶ በማስቀመጥ የተቋማዊ አደረጃጀትን የተወሰነ ዝርዝር መረጃ ይሰጣል።

- የትግበራ ኃላፊነት ያለባቸውን ኤጀንሲዎች አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ የአስተዳደር አቅም ለማጠናከር፣ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዱ (ESMP) ኃላፊነት ያለባቸውን ወገኖች መቋቋም ወይም መስፋፋት፣ የሠራተኞችን ሥልጠና እና የማስታረቂያ እርምጃዎችን እንዲሁም ሌሎች ማናቸውም የአካባቢ እና ማኅበራዊ ምዘና ጠቃሚ ምክሮች ትግበራ ለመደገፍ አስፈላጊ ሊሆኑ የሚችሉ ማናቸውንም ተጨማሪ እርምጃዎችን እንደ ምክረ ሐሳብ ያቀርባል።

d. የትግበራ መርሐ ግብር እና የወጪ ግምቶች

- ለሦስቱም ገጽታዎች (ማስታረቂያ እርምጃ፣ ክትትል እና የአቅም ግንባታ)፣ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዱ (ESMP) የሚከተሉትን ያቀርባል፦ (ሀ) ከአጠቃላዩ የፕሮጀክት ትግበራ ዕቅዶች ጋር ያለውን ፈርጃዊ ክፍፍል እና ቅንጅት በማሳየት እንደ ፕሮጀክቱ አንድ አካል ሆኖ ለሚወሰዱ እርምጃዎች መከናወን ያለበትን የትግበራ መርሐግብር፤ እና የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዱን (ESMP) ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልግ ካፒታል እና በተከታታይ የሚወጡ ወጪዎች ግምት እና የገንዘብ ምንጮች። እነዚህ አኃዞች በተጨማሪ በድምር የፕሮጀክት ሠንጠረዦች ላይ ይካተታሉ።

e. የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP) ከፕሮጀክቶች ጋር ማቀናጀት

- ተበዳሪው ከፕሮጀክቱ ጋር ወደፊት ለመቀጠል የሚወስነው ውሳኔ እና የባንኩ ይህን ለመደገፍ የሚሰጠው ውሳኔ በአንድ በኩል የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዱ (ESMP) (እንደ ብቻውን የተነጠለ ራሱን የቻለ ወይም በአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) እንደተካተተ ሆኖ) በውጤታማ መንገድ ይከናወናል ከሚል እሳቤ የሚወሰኑ ውሳኔዎች ናቸው። ይህ በመሆኑም፣ ነፍስ ወከፍ ማስታረቂያ እና የክትትል እርምጃዎችን እና የድርጊት ውሳኔዎችን እና ከእያንዳንዱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ተቋማዊ ኃላፊነቶችን እና ይህን ለማድረግ የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ጨምሮ እያንዳንዱ ተፈጻሚ የሚሆን እርምጃ እና የድርጊት ውሳኔ በግልጽ የሚቀመጥ ይሆናል፤ ይህም ሁሉ በአጠቃላዩ የዕቅድ አወጣጥ፣ ዲዛይን ዝግጅት፣ በጀት ቀረጻ እና ትግበራ ላይ እንዲካተት የሚደረግ ይሆናል።

## ዓባሪ 5፡- የዳግም ሰፈራ ፖሊሲ ማዕቀፍ ጠቋሚ

አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS5) ከፕሮጀክት ጋር በተገናኘ የሚኖር የመሬት ማግኘት እና በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦች በማኅበረሰቦች እና በግለሰቦች ላይ መጥፎ ተፅዕኖ ሊያሳርፉ እንደሚችሉ ዕውቅና ይሰጣል። ከፕሮጀክት ጋር በተገናኘ የሚኖር የመሬት ማግኘት እና በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦች አካላዊ መፈናቀል (ወደ ሌላ ቦታ መዛወር፣ መኖሪያ ቦታን ማጣት ወይም መጠለያን ማጣት)፣ ኢኮኖሚያዊ መፈናቀል (የመሬት፣ የእሴት ወይም ወደ እሴቶች መዳረሻ መነጠቅ፣ በዚህም የገቢ ምንጮችን ወይም ሌሎች ኑሮን ማሸነፊያ ዘዴዎችን ማጣት)፣ ወይም ሁለቱንም ሊያስከትሉ ይችላሉ። "በፈቃደኝነት ላይ ያልተመሠረተ ሰፈራ" የሚለው ቃል እነዚህን ተፅዕኖዎች ይመለከታል። አንድ ሰፈራ በፈቃደኝነት ላይ ያልተመሠረተ እንደሆነ ተደርጎ የሚቆጠረው በመፈናቀል ምክንያት ተፅዕኖ ያረፈባቸው ግለሰቦች ወይም ማኅበረሰቦች የመሬት መወሰዱን ወይም በመሬት አጠቃቀም ላይ የተጣሉትን ገደቦች ለመቃወም ሳይችሉ የሚቀሩበት ሁኔታ ሲኖር ነው።

### 1. ዓላማዎች

ዓላማዎቹ እነዚህ ናቸው፡-

a. በፈቃደኝነት ላይ ያልተመረኮዘ ሰፈራን ማስቅረት ወይም ይህን ለማድረግ የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የፕሮጀክት ዲዛይን አማራጮችን በሚገባ በመመርመር በፈቃደኝነት ላይ ያልተመረኮዘ ሰፈራን መቀነስ።

b. ተገዶ የቦታ ይዞታን መልቀቅን ለማስቀረት።

c. ከመሬት መነጠቅ ወይም በመሬት አጠቃቀም ላይ በሚጣል ገደብ ምክንያት መፈጠራቸውን ማስቀረት የማይችሉ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖዎችን የሚከተሉትን በማድረግ ማስታረቅ፡- (ሀ) በኪሳራ መተኪያ ተመጣጣኝ ዋጋ ለጠፉት እሴቶች ካሳን በወቅቱ ማቅረብ እና (ለ)የተፈናቀሉ ግለሰቦች ሕይወታቸውን እና የአኗኗር ዘይቤያቸውን በዕውናዊ ሁኔታዎች ለማሻሻል የሚያደርጉትን ጥረት ወይም ከቅድመ መፈናቀል ደረጃ ላይ ወይም ከፕሮጀክቱ ትግበራ በፊት ወደነበሩት ደረጃዎች ከሁለቱ ከፍተኛ ወደ ሆነው ደረጃ ቢያንስ ወደነበረበት ለመመለስ እንዲቻሉ ድጋፍ መስጠት።

d. በቂ የሆነ መኖሪያ ቤት፣ አገልግሎቶችን እና ተቋማትን እንዲደርሱባቸው በማድረግ እና የመሬት ይዞታን ዋስትና በመስጠት በአካላዊ ደረጃ የተፈናቀሉ ድሃ ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ግለሰቦችን የአኗኗር ሁኔታዎችን ማሻሻል።

e. የፕሮጀክቱ ሁኔታ በሚፈቅደው ደረጃ ልክ በቂ የሆኑ የኢንቨስትመንት ምንጮችን በማቅረብ የተፈናቀሉ ግለሰቦች በቀጥታ ከፕሮጀክቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ እንደ ዘላቂ የልማት ፕሮግራሞች የዳግም ማቋቋም እንቅስቃሴዎችን ማዘጋጀት እና ተፈጻሚ ማድረግ።

f. የዳግም ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ከአግባብነት ያላቸው የመረጃን ይፋ ማድረጊያ ዘዴዎች፣ ትርጉም ያለው ምክክር እና ተፅዕኖ ካረፈባቸው ጋር በሙሉ ግንዛቤ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ከማድረግ ጋር እንደ ታቀዱ እና ተግባራዊ እንደሆኑ ማረጋገጥ።

### 2. የትግበራው ወሰን

የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS5) ተፈጻሚነት በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1) ላይ በተብራራው አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘና ወቅት ይቋቋማል። ይህ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS)

ከፕሮጀክት ትግበራ ጋር በተገናኘ ላጋጠሙ ወይም በተጣሉ ከሚከተሉት ዓይነት የመሬት መነጠቅ ወይም የመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦች የተነሣ የሚፈጠሩ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ አካላዊ እና ኢኮኖሚያዊ መፈናቀሎች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡-

a. በመንግሥት ትዕዛዝ ወይም በብሔራዊ ሕግ ላይ በተመረኮዙ በሌሎች አስገዳጅ አፈጻጸም ሥርዓቶች በኩል የመሬት መብትን ወይም የመሬትን መጠቀም መብትን ማጣት ወይም ገደብ ውስጥ መግባት፤

b. ከመሬት ባለቤቶች ወይም መሬቱ ላይ ሕጋዊ መብቶች ካላቸው ጋር በሚደረግ የካሳ ድርድር ምክንያት የመሬት መብትን ወይም የመሬትን መጠቀም መብትን ማጣት ወይም ገደብ ውስጥ መግባት፤ እና የካሳ ድርድሩ ሳይሳካ ቢቀር የመንግሥትን ትዕዛዝ ወይም ሌሎች አስገዳጅ የአፈጻጸም ሥርዓቶችን የሚያስከትሉ ከሆነ፤

c. ማኅበረሰብን ወይም በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለን ቡድን በባህላዊ ወይም በልማዳዊ የባለቤትነት ሥርዓት ወይም ተለይቶ ሊታወቅ በሚችል የመጠቀም መብቶች ምክንያት ለተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ያላቸውን መብቶች የሚያሳጡ የመሬት አጠቃቀም እና የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ገደቦች። ከፕሮጀክቱ ጋር በተገናኘ ይህ በሕጋዊ መንገድ የተከለሉ ጥበቃ የሚደረግላቸው ቦታዎች፣ ደኖች፣ የብዝኃ ሕይወት አካባቢዎች ወይም ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ማድረግ የማይፈቀድባቸው የተከለሉ ቀጠናዎችን ሊያካትት ይችል ይሆናል፤

d. ለፕሮጀክት ጅማሬ ከተቆረጠው ቀን በፊት መሬትን የያዙ ወይም እየተጠቀሙ ያሉ መደበኛ፣ ባህላዊ ወይም ተለይቶ ሊታወቅ የሚችል የመጠቀም መብቶች የሌላቸውን ሰዎች ወደ ሌላ ቦታ በማዛወር ማስፈር፤

e. የእነርሱን መሬት እንዳይጠቀሙ ወይም እንዳይደርሱበት በሚያደርግ የፕሮጀክቱ ተፅዕኖዎች ምክንያት የሰዎች መፈናቀል፤

f. እንደ የባሕር እና የውሃ ሀብቶች፣ ከደን የሚገኙ የእንጨት ምርቶች እና እንጨት ነክ ያልሆኑ ምርቶች፣ ንጹሕ ውሃ፣ መድኃኒትነት ያላቸው ዕፅዋት፣ አደን እና የፍራፍሬ መልቀሚያ መሬቶች እና የግጦሽ እና የእርሻ ማሳዎች የመሳሰሉ በጋራ ባለቤትነት የመሬት እና የተፈጥሮ ሀብቶች ይዞታን ጨምሮ በመሬት እና በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦች፤

g. ያለ ሙሉ የካሳ ክፍያ በግለሰቦች ወይም ማኅበረሰቦች የተተዉ የመሬት መብቶች ወይም የመሬት ወይም የተፈጥሮ ሀብቶች ይገባኛል ጥያቄዎች፤ እና

h. በፕሮጀክቱ ምክንያት ወይም የፕሮጀክቱን መምጣት ከግምት በማስገባት ወይም እንደ ዝግጅት ከፕሮጀክቱ በፊት የተጣሉ የመሬት ባለቤትነት ወይም የመሬት አጠቃቀም ገደቦች።

ይህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) በፕሮጀክቱ ምክንያት በመሬት መነጠቅ ወይም የመሬት አጠቃቀም ላይ በተጣሉ ገደቦች ጋር በቀጥታ በተገናኘ በገቢ ወይም በኑሮ ላይ የሚደርሱ ተፅዕኖዎች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም። እንዲህ የመሳሰሉት ተፅዕኖዎች በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 (ESS1) መሠረት መፍትሔ ያገኛሉ።

## 3. መስፈርቶች

### 3.1 አጠቃላይ

#### የብቁነት ምደባ

ተፅዕኖ ያረፈባቸው ሰዎች እንደ የሚከተሉት ግለሰቦች ሆነው ተለያይተው ሊመደቡ ይችላሉ፡- (ሀ) የመሬት ወይም የእሴቶች መደበኛ ሕጋዊ የባለቤትነት መብቶች ያሏቸው፤ (ለ) የመሬት ወይም የእሴቶች መደበኛ ሕጋዊ የባለቤትነት መብቶች የሌላቸው ሆኖም ግን በብሔራዊ ሕግ መሠረት በመሬቱ ወይም በእሴቶቹ ላይ ይገባኛል ጥያቄ ለማቅረብ መብት እንዳላቸው ሆነው የታወቁ

ወይም ሊታወቁ የሚችሉ፤ ወይም (ሐ) ምንም ተለይቶ የታወቀ ሕጋዊ መብት  የሌላቸው ወይም የያዙትን ወይም የሚጠቀሙበትን መሬት ወይም እሴቶች ይገባኛል ለማለት የማይችሉ።

**የፕሮጀክትቀረጻ**

ተበዳሪው በፈቃደኝነት ላይ ያልተመረኮዘ የመሬት ይዞታ ወይም በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦች በአንድ በግልጽ የተቀመጠ ክፍለ ጊዜ ውስጥ በግልጽ በተቀመጡ የፕሮጀክት ዓላማዎች ለፕሮጀክቱ መሳካት አስፈላጊነት ባላቸው ሁኔታዎች ላይ የተወሰኑ መሆናቸውን በተግባር ማሳየት ይኖርበታል። በተለይ አካላዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ መፈናቀልን የሚያስከትል በሚሆንበት ጊዜ የመሬት መነጠቅን ወይም የመሬት አጠቃቀም ላይ ገደቦችን መጣልን ለማስቀረት አካባቢያዊ፣ ማኅበራዊ እና የገንዘብ ወጪዎችን እና ጥቅማ ጥቅሞችን ሚዛን እየጠበቀ እና በሥርዓተ ጾታ ላይ ለሚፈጠሩ ተፅዕኖዎች እና በድሆች እና ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ወገኖች ላይ የሚደርሱ ተፅዕኖዎች የተለየ ትኩረት እየሰጠ ተበዳሪው አዋጭ የሆኑ አማራጭ የፕሮጀክት ዲዛይኖችን ከግምት ያስገባል።

**ተፅዕኖ ላረፈባቸው ግለሰቦች የሚሰጡ ካሳ እና ጥቅማ ጥቅሞች**

(ቋሚ ሆነ ጊዜያዊ) የመሬት መነጠቅ ወይም በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦች ሊቀሩ የማይችሉ ሆነው ሲገኙ፣ ሕይወታቸውን ለማሻሻል ወይም ቢያንስ በፊት ወደ የነበራቸው የአኗኗር ዘይቤ መመለስ እንዲችሉ ለማገዝ እንደ አስፈላጊነቱ ተበዳሪው ተፅዕኖ ላረፈባቸው ግለሰቦች የወጪ ምትክ ካሳ እና ሌሎች ድጋፎችን ይሰጣል።

የመሬት እና ቋሚ እሴቶች ምድቦች ካሳ አከፋፈል መመዘኛ መስፈርቶች ለሕዝብ ይፋ ይሆናሉ እንዲሁም በወጥነት ተፈጻሚ ይሆናሉ። የካሳ ክፍያ ተመኖች የድርድር ስትራቴጂዎች ተፈጻሚ በሚሆኑበት ጊዜ ወደ ላይ እያደገ የሚሄድ ማስተካከያን መጠቀም ሊያስገድዱ ይችሉ ይሆናል። በሁሉም ሁኔታዎች ላይ፣ ግልጽ የሆነ የካሳ ስሌት መሠረት በሰነድ ተይዞ ይቀመጣል እና ካሳ ግልጽነት ባላቸው የአሠራር ሥርዓቶች አማካይነት እንዲከፋፈል ይደረጋል።

የተፈናቀሉ ሰዎች ሕይወት የተመረኮዘው ከመሬት በሚያገኙት ጥቅም ላይ ከሆነ ወይም መሬት በጋራ ባለቤትነት የተያዘ ከሆነ፣ ተመጣጣኝ የሆነ የመሬት ምትክን መስጠት የማይቻል ስለ መሆኑ ባንኩ ሊያምንበት በሚችል መልኩ በማስረጃ ካልተደገፈ በቀር በአንቀጽ 35 (ሀ) መሠረት ተበዳሪው ለተፈናቀሉ ሰዎች ተመጣጣኝ የሆነ የመሬት ምትክ ማቅረብን አማራጭ ያቀርብላቸዋል። የፕሮጀክቱ ባሕሪ እና ዓላማዎች በሚፈቅዱት ልክ፣ ተበዳሪው በተጨማሪ ለተፈናቀሉ ማኅበረሰቦች እና ግለሰቦች ከፕሮጀክቱ ተገቢነት ያለውን የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዕድሎችን ይሰጣል።

በዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) መሠረት ካሳ ከተሰጠ በኋላ፣ እና ተገቢነት ሲኖረው ተፈናቃይ ሰዎች ዳግም ከተቋቋሙ እና ለተፈናቀሉት ግለሰቦች ከካሳው በተጨማሪ ተዘዋዋሪ ድጎማዎች ከቀረቡላቸው በኋላ ብቻ ተበዳሪው የተወሰደባቸውን መሬት እና ተዛማጅነት ያላቸውን እሴቶች በቁጥጥሩ ሥር ማዋል ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ተፅዕኖ ያረፈባቸው ግለሰቦች የቀረበላቸውን አማራጭ የኑሮ ዘይቤ ተቀብለው ተጠቃሚ ለመሆን በበቂ ሁኔታ የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይህን የማድረጉ አስፈላጊነት ሲመጣ የኑሮ ወደነበረበት መመለስ እና ማሻሻያ ፕሮግራሞች ጊዜውን በጠበቀ መልኩ በሥራ ላይ መዋል ይጀምራሉ።

ለምሳሌ በቦታው ላይ የሌሉ የመሬት ባለቤቶችን ለማግኘት የተደረገው ሙከራ ሳይሰካ ቢቀር፣ በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ያረፈባቸው ሰዎች በጸደቀው ዕቅድ መሠረት የቀረበላቸውን ካሳ ክፍያ አንቀበልም ብለው አሻፈረኝ ካሉ ወይም በመሬት ወይም በእሴቶች ባለቤትነት ጥያቄ ላይ የሚነሡ የይገባኛል ጥያቄዎች ክርክር ረዥም ጊዜ የሚወስድ የፍርድ ቤት ክርክርን የሚያስከትል ከሆነ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ለተወሰኑ ተፅዕኖ ያረፈባቸው ግለሰቦች ካሳ መክፈል ጋር በተገናኘ በጉልህ የሚታዩ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። በአንዳንድ የተለዩ ሁኔታዎች፣ ከባንኩ በቅድሚያ ከሚሰጥ ፈቃድ ጋር እና ተበዳሪው እንዲህ ላሉት ጉዳዮች መፍትሔ ለመስጠት ተቀባይነት ያላቸውን ጥረቶች ስለ ማድረጉ  በተጨባጭ ማሳየት ሲችል፣ ተበዳሪው በዕቅዱ በተቀመጠው መሠረት

የካሳ ገንዘቡን (ብሎም ተቀባይነት ያለው ተጨማሪ የመጠባበቂያ ገንዘብን ጨምሮ) ወለድ በሚታሰብበት መልኩ ወይም ሌላ አማራጭ የባንክ ገንዘብ ማስቀመጫ ሒሳብ በባንክ ተቀማጭ በማድረግ ተዛማጅነት ያላቸውን የፕሮጀክት ኣንቅስቃሴዎች ማድረጉን መቀጠል ይችላል። በጊዜ ገደብ የተቀመጠ ወለድ ያለው የካሳ ገንዘብ ችግሮቹ ልክ መፍትሔ እንዳገኙ ካሳውን ለማግኘት ብቁ ለሆኑ ግለሰቦች በወቅቱ እንዲያገኙት ይደረጋል።

**የማኅበረሰብ ተሳትፎ**

በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS10) ላይ እንደተብራራው በባለድርሻ አካል ተሳትፎ ሂደት አማካኝነት ተበዳሪው ተቀባይ ማኅበረሰብን ጨምሮ ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ማኅበረሰቦች ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል። ከዳግም መቋቋም እና ኑሮን ወደነበረበት መመለስ ጋር የተገናኙ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ተፅዕኖ ያረፈባቸው ግለሰቦች ምርጫ ማድረግ የሚችሉባቸውን አማራጮች የሚያካትቱ ይሆናሉ። ተዛማጅነት ያለው መረጃ እና ትርጉም ያለው ተፅዕኖ ያረፈባቸው ማኅበረሰቦች እና ግለሰቦች ተሳትፎ አማራጭ የፕሮጀክት ዲዛይኖች ከግምት በሚገቡበት ወቅት እና ከዚህ በኋላ በካሳ አከፋፈል ሂደት እና ወደ ቀድሞ ኑሮ የመመለስ እንቅስቃሴዎች እና ወደ ሌላ ቦታ የማዛወር ሂደት ዕቅድ አወጣጥ፣ በትግበራ፣ በክትትል፣ እና ምዘና ወቅት ተፈጻሚ ይሆናሉ። በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7) መሠረት ከተፈናቀሉ የአካባቢው ተወላጆች ጋር ለሚደረጉ ምክክሮች ተጨማሪ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

የምክክር ሂደቱ የሴቶች አመለካከቶች መንፀባረቃቸውን እና በዳግም ማቋቋም እና ትግበራው ሁሉም ገጽታዎች ላይ የእነርሱ ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ እንዲገቡ መደረጋቸውን ማረጋገጥ መቻል አለበት። በኑሮ ላይ የሚደርሱ ተፅዕኖዎችን መፍትሔ መስጠት ሴቶች እና ወንዶች በኑሯቸው ላይ በተለያየ መልኩ ተፅዕኖ የሚያርፍባቸው ከሆነ ቤት ለቤት የተያያዘ ትንታኔ መስጠትን ሊጠይቅ ይችላል። ከጥሬ ገንዘብ ይልቅ እንደ ምትክ መሬት ወይም ምትክ የተፈጥሮ ሀብቶችን ማግኘት የመሳሰሉ የካሳ አሰጣጦች ላይ ሴቶች እና ወንዶች ያሏቸው ምርጫዎች ምን እንደሆኑ በሚገባ መታየት ይኖርባቸዋል።

**የቅሬታአቀራረብዘዴ**

በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS10) መሠረት በፕሮጀክቱ ዝግጅት ወቅት በተቻለ ፍጥነት ሳይዘገይ ስለ ካሳ፣ ስለ ወደ ሌላ ቦታ መዛወር ወይም ወደ ቀድሞ ኑሮ ተመልሶ መቋቋም እርምጃዎች በተመለከተ በተፈናቀሉ ሰዎች ሊነሡ የሚችሉ የተወሰኑ ለየት ያሉ ጥያቄዎችን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ ለፕሮጀክቱ እንዳለው ተበዳሪው ማረጋገጫ ይሰጣል። የሚቻል ሲሆን፣ እንዲህ ያሉት የቅሬታ አቀራረብ ዘዴዎች ለፕሮጀክት ዓላማዎች ተስማሚ የሆኑ በሥራ ላይ ያሉ መደበኛ ወይም ኢመደበኛ የቅሬታ አቀራረብ ዘዴዎችን ይጠቀማል፥ ይህም ሲሆን በገለልተኝነት አለመግባባቶችን ለመፍታት ተጨማሪ ፕሮጀክቱን ያማከሉ ማስተካከያዎች ሊደረጉበት ይችላሉ።

**ዕቅድ አወጣጥ እና ትግበራ**

መሬትን መውሰድ ወይም በመሬት አጠቃቀም ላይ ገደቦችን መጣል ሊቀር የማይችል ሆኖ ሲገኝ፣ እንደ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘና አንድ አካል በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ የሚያርፍባቸውን ሰዎች ለመለየት፣ ተፅዕኖ የሚያርፍባቸውን መሬቶች እና እሴቶች ለመቁጠር፣ ማን ካሳ እና ድጋፍ ለማግኘት ብቁ እንደሆነ ለመወሰን፣ እንዲሁም እንደ አጋጣሚውን ለመጠቀም የሚፈልጉ ሕገወጥ ሰፋሪዎች የመሳሰሉ ብቁ ያልሆኑ ሰዎች የጥቅማ ጥቅሞች የይገባኛል ጥያቄ እንዳያቀርቡ ለማገድ ተበዳሪው የሕዝብ ቆጠራ ያካሂዳል። ማኅበራዊ ምዘናው በተጨማሪ  በበቂ ምክንያት የሕዝብ ቆጠራው በሚደረግበት ወቅት በፕሮጀክቱ አካባቢ ላይ ላይኖሩ የሚችሉ ማኅበረሰቦችን ወይም ቡድኖችን ለምሳሌ ወቅትን ተከትለው የተፈጥሮ ሀብቱን እንደሚጠቀሙ ያሉ ተጠቃሚዎችን የይገባኛል ጥያቄዎች መፍትሔ የሚሰጥ ይሆናል። ከሕዝብ ቆጠራው ጎን ለጎን፣ ተበዳሪው ብቁነት የሚወሰንበትን ቁርጥ ያለ ቀን ያስቀምጣል። የተቀረጠውን ቀን የተመለከተው መረጃ በሰነድ ይያዛል እና በጽሑፍ እና (እንደተገቢነቱ) በጽሑፍ ባልሆኑ መንገዶች በመደበኛ የጊዜ ልዩነቶች እና ተገቢነት ባላቸው የአካባቢው ቋንቋዎች በፕሮጀክቱ

አካባቢ ላይ የሚሰራጭ ይሆናል። ይህ ከተቆረጠው ቀን በኋላ በፕሮጀክቱ አካባቢ የሚሰፍሩ ሰዎች ከቦታው እንዲነሡ እንደሚደረጉ የሚለጠፍ ማስጠንቀቂያን ያካትታል።

በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ምዘናው ተለይተው የታወቁትን ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት፣ ተበዳሪው ከፕሮጀክቱ ጋር በተገናኘ ለተፈጠሩት ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ተመጣጣኝ የሆነ ዕቅድን ያዘጋጃል፦

a. ቀላል ለሆኑ የመሬት መውሰዶች ወይም በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦች ላሏቸው እና በዚህም ምክንያት በገቢ ወይም በኑሮ ዘይቤ ላይ ይህ ነው የሚባል ተፅዕኖ የማይፈጥሩ ፕሮጀክቶች ዕቅዱ ተፅዕኖ ላረፈባቸው ሰዎች ብቁነትን መለያ መስፈርቶች ያስቀምጣል፣ የካሳ አከፋፈል ሥርዓቶችን እና መመዘኛዎችን ይደነግጋል እንዲሁም ለምክክር፣ ለክትትል እና ቅሬታዎችን መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ያካትታል፤

b. አካላዊ መፈናቀልን ለሚያስከትሉ ፕሮጀክቶች ዕቅዱ ጉዳት የደረሰባቸውን ግለሰቦች ወደ ሌላ ቦታ ከማዛወር ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ተጨማሪ እርምጃዎች ያስቀምጣል፤

c. በኑሮ ዘይቤ ላይ ወይም በገቢ ምንጮች ላይ ጉልህ ተፅዕኖ የሚፈጥሩ ኢኮኖሚያዊ መፈናቀሎች ላሏቸው ፕሮጀክቶች፣ ዕቅዱ የኑሮ ዘይቤን ለማሻሻል ወይም ወደነበረበት ለመመለስ ከሚሠራ ሥራ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተጨማሪ እርምጃዎች የሚያስቀምጥ ይሆናል፤ እና

d. በሕግ በተለዩ ፓርኮች ወይም ጥበቃ የሚደረግላቸው ቦታዎች ወይም የአካባቢ ነዋሪዎች ኑሯቸውን ለመግፋት ዓላማ ጥገኛ ሊሆኑባቸው የሚችሉ ሌሎች በጋራ ባለቤትነት የተያዙ የተፈጥሮ ሀብቶች መዳረሻን የሚከለክል የመሬት አጠቃቀም ደንብን የሚያስቀምጡ ለውጦች ላሏቸው ፕሮጀክቶች፣ ዕቅዱ በአጠቃቀም ላይ ተገቢነት ያላቸውን ገደቦች ለማስቀመጥ አሳታፊ የሆነ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደትን በሥራ ላይ ያውላል እንዲሁም እንዲህ ባሉት ገደቦች ምክንያት በኑሮ ዘይቤ ላይ ለሚፈጠሩ አስከፊ ተፅዕኖዎች መፍትሔ ለመስጠት የማስታረቂያ እርምጃዎችን ይቀርባል።

የተበዳሪው ዕቅድ የፋይናንስ አቅርቦትን እና ትግበራ በተመለከተ ሚናዎችን እና ኃላፊነቶችን ለይቶ ያስቀምጣል እንዲሁም ያልተጠበቁ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችል የመጠባበቂያ ገንዘብ አቅርቦትን አዘገጃጀት እንዲሁም የፕሮጀክቱን ግሥጋሤ ሊገቱ የሚችሉ ይደርሳሉ ተብለው ያልታሰቡ ሁኔታዎችን በጊዜ እና በተቀናጀ መልኩ ምላሽ ለመስጠትና ወደተፈለገው ውጤት ለመድረስ የሚያስችሉ መፍትሔዎችን የሚያካትት ይሆናል። የፕሮጀክቱን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ ለሰፈራ ወይም ዳግም ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ሙሉ ወጪዎች በፕሮጀክቱ አጠቃላይ ወጪዎች ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋሉ። ልክ እንደ ሌሎች የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ወጪዎች ሁሉ፣ የዳግም ማቋቋም ወይም የሰፈራ ወጪዎች፣ እንደ በፕሮጀክቱ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎች ላይ የሚታሰቡ አስፈላጊ ወጪዎች እንደሆኑ ተደርገው ይቆጠራሉ፤ እንዲሁም ለሰፋሪዎቹ የሚደርሷቸው የተጣሩ ክፍያዎች («ፕሮጀክት ውጭ» ከሆኑ አንፃር ሲታዩ) በፕሮጀክቱ ዋንኛ የጥቅማ ጥቅም ክፍያዎች ላይ እንዲጨምሩ ይደረጋሉ።

የዕቅዱን ትግበራ ለመከታተል እና ለመመዘን የሚያስፈልጉትን የአሠራር ሥርዓቶች ተበዳሪው ያዘጋጃል እንዲሁም የዚህን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ዓላማዎች ለማሳካት በትግበራ ወቅት አስፈላጊ ሆነው የሚገኙትን የዕርምት እርምጃዎች ይወስዳል። የክትትል እንቅስቃሴዎቹ ሊሄዱበት የሚችሉት ርቀት ከፕሮጀክቱ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል። ጉልህ የሆነ በፈቃደኝነት ላይ ያልተመረኮዘ የሰፈራ ተፅዕኖዎች ላሉባቸው ሁሉም ፕሮጀክቶች፣ የዳግም ማቋቋሙን ወይም የሰፈራውን ዕቅዶች ትግበራ እንዲከታተሉ፣ እንደ አስፈላጊነቱ የዕርምት እርምጃዎችን እንዲያዘጋጁ፣ በዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) መሠረት ምክር እንዲለግሡ እና በክፍለ ጊዜ ገደብ የተለያዩ የክትትል ሪፖርቶችን እንዲያቀርቡ ተበዳሪው ብቃት ያላቸውን የዳግም ማቋቋም ወይም የሰፈራ ፕሮፌሽናሎችን ይቀጥራል። በክትትል ሂደቱ ላይ ተፅዕኖ ካረፈባቸው ሰዎች ጋር ምክክር ይደረጋል። በክፍለ ጊዜ ገደብ የተለያዩ የክትትል ሪፖርቶች ይዘጋጃሉ እና ተፅዕኖ ያረፈባቸው ሰዎች ስለ ክትትሉ ውጤቶች ጊዜውን በጠበቀ መልኩ መረጃ እንዲያገኙ ይደረጋሉ።

የተበዳሪው የትግበራ ዕቅድ እንደተጠናቀቀ የሚቆጠረው የዳግም ሰፈራው አስከፊ ተፅዕኖዎች ተገቢነት ካለው ዕቅድ እና እንዲሁም ከዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ዓላማዎች ጋር በሚጣጣም መልኩ መፍትሔ ሲያገኝ ነው። ጉልህ የሆነ በፈቃደኝነት ላይ ያልተመረኮዘ የሰፈራ ተፅዕኖዎች ላሉባቸው ሁሉም ፕሮጀክቶች ተበዳሪው ሁሉም የማስታረቂያ እርምጃዎች በበቂ ሁኔታ ከተጠናቀቁ በኋላ የዕቅዱን አፈጻጸም በውጭ ኦዲተር አማካይነት እንዲጣራ ያስደርጋል። የተጠናቀቀው ኦዲት ብቃት ባላቸው የሰፈራ ጉዳይ ባለሙያዎች (ፕሮፌሽናሎች) የሚከናወን ይሆናል፣ ኦዲት ሪፖርቱም የኑሮ ዘይቤዎች እና የኑሮ መመዘኛዎች እንደተሻሻሉ ወይም ቢያንስ ወደነበሩበት ደረጃ እንደተመለሱ ይመዝናል እንዲሁም አስፈላጊ ሲሆን እስካሁን ግባቸውን ያልሙቱ ዓላማዎችን ለማሳካት የዕርምት እርምጃዎችንእንደ ሐሳብ ያቀርባል።

በፕሮጀክት ዝግጅቱ ወቅት ከፕሮጀክቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላዊ እና/ወይም ኢኮኖሚያዊ መፈናቀልን ሊያስከትሉ የሚችሉ የመሬት መያዙ ወይም የመሬት አጠቃቀም ገደቦቹ ባሕሪ ወይም መጠነ ስፋት የማይታወቅ በሚሆንበት ጊዜ፣ ከዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ጋር የሚጣጣሙ አጠቃላይ መርሆዎችን እና የአሠራር ሥርዓቶችን ለማቋቋም የሚያስችል ማዕቀፍን ተበዳሪው ያዘጋጃል። ነፍስ ወከፍ የፕሮጀክቱ ክፍለ አካላት አንድ ጊዜ ከተበየኑ በኋላ እና አስፈላጊ የሆነው መረጃ ከተገኘ በኋላ እንዲህ ያለው ማዕቀፍ ሊከሰቱ ከሚችሉ ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ጋር ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ወደ አንድ ወይም ከዚያ በላይ በልዩ ሁኔታ የተዘጋጁ ዕቅዶች እንዲስፋፉ ይደረጋል። በዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) የተቀመጡ ዕቅዶች እስከሚከናወኑ እና በባንኩ እስከሚፈቀድ ድረስ ምንም ዓይነት አካላዊ እና/ወይም ኢኮኖሚያዊ መፈናቀል አይኖርም።

### 3.2 መፈናቀል

#### አካላዊ መፈናቀል

አካላዊ መፈናቀልን በተመለከተ፣ ተፅዕኖ ያረፈባቸው ሰዎች ብዛት ከግምት ሳይገባ የዚህን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ተገቢነት ያላቸውን ግዴታዎች ቢያንስ የሚሸፍን ዕቅድን ተበዳሪው ያዘጋጃል። ዕቅዱ የመፈናቀሉን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለማስታረቅ እና ቃል በተገባው መሠረት ያሉትን የልማት ዕድሎች ለይቶ ለማስቀመጥ በሚያስችል መልኩ የሚዘጋጅ ይሆናል። የዳግም ማቋቋም ወይም የሰፈራ በጀት እና የትግበራ መርሐግብር የሚያካትት ይሆናል ኣንዲሁም ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ግለሰቦች ሁሉንም ምድቦች ብቁነት ሁኔታ የሚያመላክት ይሆናል (ፕሮጀክቱ የሚከናወንበት ቦታ ማኅበረሰቦችን ጨምሮ)። ለሥርዓተ ጾታ ገጽታዎች እና ለድሃ እና ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች ፍላጎቶች የተለየ ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል። ተበዳሪው የመሬት ባለቤትነት መብቶችን ለማግኘት፣ የካሳ አሰጣጥ ድንጋጌዎችን ዝግጅት እና ሌሎች ከዳግም ሰፈራ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ድጋፎች በተመለከተ ሁሉንም የገንዘብ ዝውውሮች በሰነድ ይይዛል።

በፕሮጀክቱ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወሩ ማድረግ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ተበዳሪው የሚከተሉትን ያደርጋል፦

a. በቂ ተተኪ መኖሪያ ቤት ወይም የጥሬ ገንዘብ የካሳ ክፍያን ጨምሮ ለተፈናቀሉ ሰዎች አዋጭ ከሆኑ የሰፈራ አማራጮች መካከል እንዲመርጡ ዕድል ይሰጣል፤ እና

b. የተፈናቀሉ ሰዎችን የተለያዩ ቡድኖች የእያንዳንዳቸውን ፍላጎቶች የሚያሟላ የዳግም ሰፈራ ድጋፍን ይሰጣል።

አዳዲስ የሰፈራ ቦታዎች ቢያንስ ከዚህ ቀደም ከነበሩት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ለኑሮ አስፈላጊ ሁኔታዎች ያሟላል ወይም የበላይነት ባላቸው ዝቅተኛ ደረጃን የሚወስኑ ደንቦች ወይም መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ባለው ልክ የሚያሟላ ሲሆን፣ እዚህ ላይ የተሻለ ከፍተኛ ዕድል የሚሰጠው መመዘኛ ተመራጭ ይሆናል። አዳዲስ የሰፈራ ቦታዎች ገና የሚዘጋጁ ከሆነ፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቀባይ ማኅበረሰቦች ጋር ስላሉት የዕቅድ አወጣጥ አማራጮች ምክክር ይደረጋል እንዲሁም የዳግም ሰፈራ ዕቅዶቹ ተቀባይ ማኅበርሰቦቹ ለተቋማት እና አገልግሎቶች ያላቸው ተደራሽነት ቢያንስ አሁን ባሉት ደረጃዎች ወይም መመዘኛ መስፈርቶች ልክ እንዲቀጥሉ መደረግ መቻሉን ያረጋግጣሉ። በተቻለ መጠን የሚፈናቀሉ ግለሰቦች ቀደም ሲል በነበሩ ማኅበረሰቦች ወይም

ቡድኖች ውስጥ ዳግም ለመቋቋም ወይም ለመስፈር የሚኖራቸው ምርጫ የሚከበር ይሆናል። በወቅቱ ያሉ የተፈናቃይ ግለሰቦቹ እና የማናቸውም ተቀባይ ማኅበረሰቦች ማኅበራዊ እና ባህላዊ ተቋማት የሚከበሩ ይሆናሉ።

በአንቀጽ 10 (ሀ) እና (ለ) መሠረት አካላዊ መፈናቀል ለሚያጋጥማቸው ግለሰቦች፣ በምትክ ዋጋ መጠን እኩል ወይም የበለጠ ዋጋ ያለው ተተኪ ንብረት ከይዞታ ዋስትና እንዲሁም እኩል ወይም የተሻሉ ጠባዮች እና የአካባቢ ጥቅማ ጥቅሞች ወይም የገንዘብ ካሳ መካከል እንዲመርጡ ተበዳሪው ምርጫ ይሰጣቸዋል። ከጥሬ ገንዘብ ይልቅ በዓይነት የሚሰጥ ካሳ ከግምት የሚገባ ይሆናል።

በአንቀጽ 10 (ሐ) መሠረት አካላዊ መፈናቀል ለደረሰባቸው ግለሰቦች በቂ የሆነ መኖሪያ ቤት ከይዞታ ዋስትና ጋር እንዲያገኙ ለማስቻል ተበዳሪው የተመቹ ሁኔታዎችን ይፈጥርላቸዋል። እነዚህ የተፈናቀሉ ሰዎች የገነቧቸው ሕንጻዎች ካሏቸው፣ እንደ መኖሪያ ቤት እና ሌሎች በመሬቱ ላይ የተደረጉ ግንባታዎች በወቅቱ ባለው የምትክ ዋጋ መጠን ልክ ተበዳሪው ከመሬቱ በተጨማሪ ለሚደርስባቸው ኪሣራ ካሳ ይከፍላቸዋል። ከተፈናቀሉ ሰዎች ጋር በሚደረግ ምክክር ላይ በመመርኮዝ በቂ በሆነ አማራጭ ቦታ ላይ ኑሯቸውን መልሰው እንዲመሠርቱና እንዲቋቋሙ ከሚያስችላቸው በቂ ከሆነ ምትክ መሬት ጋር የመልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍን ተበዳሪው ይሰጣቸዋል።

የተቆረጠው ቀን በግልጽ የተቀመጠ ከሆነ እና ለሕዝብ ይፋ የተደረገ እስከሆነ ድረስ ከተቆረጠው ቀን በኋላ ይገባኛል ጥያቄ ለሚያቀርቡ የፕሮጄክት አካባቢውን ወረው በሕገወጥ መንገድ ለያዙ ሰዎች ካሳ እንዲከፍል ወይም ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ተበዳሪው አይገደድም።

ተበዳሪው ተፅዕኖ የሚያርፍባቸውን ሰዎች አስገድዶ የቦታ ይዞታን የማስለቀቅ አማራጭን አይጠቀምም። “ተገዶ የቦታ ይዞታን መልቀቅ” የሚለው አባባል ግለሰቦችን፣ ቤተሰቦችን እና/ወይም ማኅበረሰቦችን አግባብነት ያላቸው የሕግ እና ሌላ ጥበቃዎች ባልተሟሉበት እና ሁሉም የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) አፈጻጸም ሥርዓቶችን እና መርሆዎችን እንዲከበሩላቸው ለማስደረግ በማይችሉበት ሁኔታ ያለ ፍላጎታቸው በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ከመኖሪያ ቤታቸው እና/ወይም መሬታቸው ላይ በግዳጅ እንዲነሡ የማድረግ ድርጊት እንደሆነ ተደርጎ ይተረጎማል። ድርጊቱ የሚፈጸመው ሁሉንም የብሔራዊ ሕግ ድንጋጌዎች እና የዚህን አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ግዴታዎች እስካሟላ ድረስ እና (አስቀድሞ በቂ የሆነ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣ ቅሬታዎችን እና ይግባኞችን ለማቅረብ የሚያስችሉ ትርጉም ያላቸው ዕድሎች መኖር፣ እና አስፈላጊነት የሌለው፣ ተመጣጣኝ ያልሆነ ወይም ከልክ በላይ የሆነ ጉልበትን መጠቀም እስከሌለበት ድረስ ጨምሮ) አፈጻጸሙም አግባነት ያለውን የአፈጻጸም ሂደት መሠረታዊ መርሆዎች ያልጣሰ እስከሆነ ድረስ ተበዳሪው የሚያከናውነው አግባብነት ያለውን ይዞታን ማስከበር፣ አስገዳጅ መሬትን አያያዝ ወይም ተመሳሳይ ሥልጣኖችን ማስከበር ድርጊት እንደ ተገዶ የቦታ ይዞታን መልቀቅ ተደርጎ አይቆጠርም።

እንደ የመፈናቀል አንድ አማራጭ፣ ተፅዕኖ የሚያርፍባቸው ወገኖች ያላቸውን ንብረት ከልማት ሥራው በኋላ ያለውን እሴት በሚጨምር ማሻሻያ በመስማማት ከመሬታቸው የተወሰነውን ክፍል ለማጣት ወይም በአካባቢው ሳይርቁ ዳግም ለመስፈር መምረጥ እንዲችሉ ልማት በሚከናወንበት ቦታ ላይ ድርድር ማድረግን ተበዳሪው እንደ አማራጭ መውሰድ ይችላል። በዚህ የማይስማማ ማናቸውም ግለሰብ በዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) በተቀመጠው መሠረት ሙሉ ካሳን እና ሌሎች ድጋፎችን ማግኘትን በምትኩ እንዲመርጥ ይፈቀድለታል።

**ኢኮኖሚያዊ መፈናቀል**

ፕሮጀክቶች አኗኗር ዘይቤ ወይም የገቢ ምንጮች ላይ ተፅዕኖ በሚያሳርፉባቸው ሁኔታዎች ላይ የተበዳሪው ዕቅድ ተፅዕኖ የሚያርፍባቸውን ሰዎች ገቢያቸውን ወይም የአኗኗር ዘይቤያቸውን እንዲያሻሽሉ ወይም ቢያንስ ወደነበረበት ደረጃ መመለስ እንዲችሉ የሚያደርጉ እርምጃዎችን የሚያካትት ይሆናል። ለሥርዓተ ጾታ ጉዳዮች እና ለማኅበረሰቡ ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ክፍሎች ፍላጎቶች የተለየ ትኩረት በማድረግ፣ ዕቅዱ ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ግለሰቦች እና/ወይም ማኅበረሰቦች ያሏቸውን

መብቶች በግልጽ የሚያስቀምጥ ይሆናል እንዲሁም እነዚህ መብቶችም ግልጽነት፣ ወጥነት እና ርትዓዊነት ባለው መልኩ የሚከበሩ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ዕቅዱ በትግበራ ወቅት የአኗኗር ዘይቤዎችን ወደነበሩበት ወይም ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ውጤታማነት ለመከታተል እንዲሁም አንድ ጊዜ ትግበራው እንደተጠናቀቀ ፍተሻና ምዘና መደረጉን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማስተካከያዎችን በውስጡ የያዘ ይሆናል። ለኢኮኖሚያዊ መፈናቀል የሚወሰደው የማስታረቂያ እርምጃ የፍጻሜ ኦዲት ሪፖርቱ ተፅዕኖ ያረፈባቸው ግለሰቦች ወይም ማኅበረሰቦች ማግኘት ያለባቸውን ድጋፍ በሙሉ ማግኘታቸውን እና ኑሯቸውን ዳግመኛ ለማቋቋም የሚያስችላቸውን በቂ ዕድል እንደተሰጣቸው በማረጋገጥ ከድምዳሜ ላይ ሲደርስ እርምጃው ተከውኖ እንደተጠናቀቀ ይቆጠራል።

ያሏቸውን እሴቶች ወይም የእሴቶቻቸውን መዳረሻዎች ያጡ ኢኮኖሚያዊ መፈናቀል የደረሰባቸው ግለሰቦች እንዲህ ላለው ኪሣራ በምትክ አከፋፈል ወጪ ልክ ተመጣጣኝ ካሳ የሚያገኙ ይሆናሉ፡-

a. የመሬት መያዝ ወይም በመሬት አጠቃቀም ላይ የተጣሉ ገደቦች በንግድ ድርጅቶች ላይ ተፅዕኖ በሚያሳድሩበት ጊዜ እነዚህ ተፅዕኖ ያረፈባቸው የንግድ ድርጅቶች ባለቤቶች አዋጭ የሆነ አማራጭ ቦታን ለይቶ ለማግኘት ለሚያወጡት ወጪ፣ ወደ አዲሱ ቦታ በሚያደርጉት ሽግግር ወቅት ለሚደርስባቸው የተጣራ ገቢ ኪሣራ፣ ወደ ሌላ ቦታ ለመዛወር እና ፋብሪካቸውን፣ ማሽኖቻቸውን ወይም ሌላ መሣሪያዎችን ዳግመኛ ለመትከል እና እንዲሁም የንግድ እንቅስቃሴያቸውን እንደገና ለማስጀመር ለሚያወጡት ወጪ በሙሉ ካሳ የሚያገኙ ይሆናሉ። ተፅዕኖ ያረፈባቸው ተቀጣሪ ሠራተኞች ለሚያጋጥማቸው ጊዜያዊ ደመወዝን የማጣት ኪሣራ ድጋፍ ያገኛሉ እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ አማራጭ የሥራ ቅጥር ዕድሎችን ለማግኘት እንዲችሉ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፤

b. ሕጋዊ የመሬት የባለቤትነት መብቶች ያላቸው ወይም በብሔራዊ ሕጉ (አንቀጽ 10 (ሀ) እና (ለ) ን ይመልከቱ) ሥር ዕውቅና ያላቸው ወይም ሊኖራቸው የሚችሉ የይገባኛል ጥያቄ የሚያቀርቡ ተፅዕኖ ያረፈባቸው ግለሰቦችን በሚመለከት፣ ዋጋው እኩል ወይም የበለጠ የሆነ ምትክ የቦታ ይዞታ (ለምሳሌ የእርሻ ወይም የንግድ ሥራ መሥሪያ ቦታ) እንዲያገኙ ይደረጋሉ ወይም ተገቢነት ሲኖረው በጥሬ ገንዘብ የሚከፈል ካሳ እንደ ምትክ ኪሣራ ዋጋ እንዲከፈላቸው ይደረጋሉ፤ እና

c. በሕጋዊ መንገድ የሚታወቅ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ የሌላቸው ኢኮኖሚያ መፈናቀል የደረሰባቸው ግለሰቦች (አንቀጽ 10 (ሐ) ን ይመልከቱ) ከመሬት ውጭ ለሚደርስባቸው ኪሣራ (እንደ ሰብል፣ የመስኖ መሠረተ ልማት እና ሌሎች በመሬቱ ላይ የተሠሩ ሥራዎች የመሳሰሉ) በምትክ ኪሣራ ዋጋ መጠን ካሣ እንዲያገኙ ይደረጋሉ። በተጨማሪ፣ ተበዳሪው እንዲህ ያሉ ግለሰቦችን ሌላ ቦታ ኑሯቸውን ዳግመኛ ለመመሥረት የሚያስችላቸውን ዕድል ለመስጠት ከመሬት ካሣ ፈንታ ሌላ በቂ የሆነ ድጋፍን ይሰጣቸዋል። ከተቆረጠው ቀን በኋላ ይገባኛል ጥያቄ ለሚያቀርቡ የፕሮጀክት አካባቢውን ወረው በሕገወጥ መንገድ ለያዙ ሰዎች ካሳ እንዲከፍል ወይም ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ተበዳሪው አይገደድም።

ኢኮኖሚያዊ መፈናቀል የደረሰባቸው ግለሰቦች የገቢ ማግኘት አቅማቸውን፣ የማምረት ደረጃቸውን እና የኑሮ ደረጃቸውን ማሻሻል እንዲችሉ ወይም ወደነበረበት ቢያንስ መመለስ እንዲችሉ የሚያደርጓቸውን ዕድሎች ይሰጧቸዋል፤

a. ኑሯቸው ከመሬት ጋር ለተቆራኘ ግለሰቦች፣ የምርታማነት አቅም፣ የቦታ የተሻለ ዕድል እና ካጡት ቦታ ጋር ቢያንስ እኩል የሆኑ ሌሎች ሁኔታዎችን የሚያሟላ ምትክ መሬት አዋጭ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ የሚሰጣቸው ይሆናሉ፤

b. ኑሯቸው በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ለተመረኮዘ ግለሰቦች እና ወደ እነዚህ ሀብቶች ያላቸውን መዳረሻ ከፕሮጀክቱ ጋር በተገናኙ ክልከላዎች ምክንያት የሚያጡ ከሆነ፣ ተፅዕኖ ወዳረፈባቸው ሀብቶች መድረስ እንዲችሉ የሚያደርግ ወይም አማራጭ ሀብቶችን ከተመጣጣኝ ገቢ ጋር እና ተደራሽነት ጋር እንዲያገኙ መዳረሻ የሚሰጥ እርምጃ ተፈጻሚ ይሆናል። በጋራ ባለቤትነት የተያዙ ንብረቶች ላይ ተፅዕኖ በሚያርፍበት ጊዜ በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ጋር የተገናኙ የሚሰጡ ጥቅማ ጥቅሞች እና ካሳዎች በተፈጥሯቸው በጋራ የሚሰጡ ይሆናሉ፤ እና

c. ምትክ መሬት ወይም የተፈጥሮ ሀብቶችን መስጠት የማይቻል መሆኑ ከታወቀ፣ እንደ የብድር አገልግሎቶች፣ የክኅሎት ሥልጠና፣ የንግድ ማስጀመሪያ የገንዘብ ድጋፍ፣ የሥራ ቅጥር ዕድሎች፣ ወይም ለእሴቶች ከሚሰጠው ካሳ በተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ የመሳሰሉ አማራጭ የገቢ ማግኛ ዕድሎችን ኢኮኖሚያዊ መፈናቀል ለደረሰባቸው ግለሰቦች ተበዳሪው የሚሰጣቸው ይሆናል። ሆኖም ግን የገንዘብ ድጋፍ ብቻውን ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ግለሰቦች አምራች የሚያደርጋቸውን መንገድ ወይም ኑሯቸውን ወደነበረበት ለመመለስ የሚያስችሉ ክኅሎቶችን በተደጋጋሚ ለመስጠት ሳይችል ሲቀር ተስተውሏል።

በሽግግር ወቅት የሚሰጥ ድጋፍ እንደ አስፈላጊነቱ ለሁሉም ኢኮኖሚያዊ መፈናቀል ለደረሰባቸው ግለሰቦች ተቀባይነት ባለው ወደ ቀድሞ የገቢ ማግኘት አቅማቸው፣ የማምረት ደረጃቸው እና የኑሮ ሁኔታቸው እንዲመለሱ በሚያስችል የጊዜ ገደብ ግምት ላይ በመመርኮዝ የሚሰጣቸው ይሆናል።

## ዓባሪ 6፡- ለዳግም ማቋቋሚያ ዕቅድ የድርጊት መርሐ ግብር ጠቋሚ ቢጋር

ይህ ዓባሪ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS5) ላይ ያሉትን አካላዊ እና/ወይም ኢኮኖሚያዊ መፈናቀል መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችሉትን ዕቅዶች አባለ ነገራት ያብራራል። ለዚህ ዓባሪ ዓላማ፣ እነዚህ ዕቅዶች ከዚህ በኋላ "የዳግም ማቋቋሚያ ዕቅዶች" በመባል የሚጠቀሱ ይሆናል። የዳግም ማቋቋሚያ ዕቅዶች በፕሮጀክት ይፈጠራሉ ተብለው የሚጠበቁ ተፅዕኖዎች ባሕሪ ላይ በመመርኮዝ ለአካላዊ እና/ወይም ኢኮኖሚያዊ መፈናቀሎች የሚወሰዱ እርምጃዎችን ይወስዳሉ። ፕሮጀክቶች በዳግም ማቋቋሚያ ዕቅዱ ወሰን ላይ በመመርኮዝ አማራጭ እንደ ቦታው ተስማሚ የሆነ ስያሜን ሊጠቀሙ ይችሉ ይሆናል - ለምሳሌ፣ ፕሮጀክቱ ኢኮኖሚያዊ መፈናቀል ብቻ የሚመለከተው ከሆነ፣ የዳግም ማቋቋሚያ ዕቅዱ "የኑሮ ዕቅድ" በመባል ሊጠራ ይችል ይሆናል ወይም በሕጋዊ መንገድ በተከለሉ ፓርኮች እና ጥበቃ የሚደረግላቸው አካባቢዎች ላይ መዳረሻ በሚታገድበት ጊዜ ዕቅዱ "የሂደት ማዕቀፍ" ቅርጽን ሊያዝ ይችል ይሆናል።

የዳግም ማቋቋሚያ ዕቅዱ መስፈርቶች እና የዝርዝር ደረጃዎች ወሰን ከዳግም ማቋቋሚያው መጠነ ስፋት እና ውስብስብነት ደረጃ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ዕቅዱ ስለሚከተሉት በሚሰበሰብ ወቅታዊ እና አስተማማኝ መረጃ ላይ የተመረኮዘ ይሆናል፡- (ሀ) እንደ ሐሳብ የቀረበው ፕሮጀክት እና በተፈናቀሉ ግለሰቦች እና ሌሎች ከፉኛ ተፅዕኖ ባረፈባቸው ቡድኖች ላይ ሊኖረው የሚችሉት ተፅዕኖዎች፣ (ለ) ተገቢነት ያላቸው እና አዋጭ አስታራቂ እርምጃዎች፣ እና (ሐ) ለዳግም ማቋቋሚያ እርምጃዎች ውጤታማ ለሆነ ትግበራ የሚያስፈልጉ ሕጋዊ እና ተቋማዊ ማስተካከያዎች።

**የዳግም ማቋቋሚያ ዕቅድ ዝቅተኛ የሚፈቀዱ አባለ ነገሮች፡-**

**የፕሮጀክቱ ዝርዝር መግለጫ።** የፕሮጀክቱ ዝርዝር መግለጫ እና የፕሮጀክት ሥራ ቦታ አካባቢ ልየታ።

**ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተፅዕኖዎች።** የሚከተሉት ልየታ፡-

a. የተመረጠው መሬት ለምን በፕሮጀክቱ የጊዜ መርሐግብር ውስጥ ጥቅም ላይ ለመዋል መያዝ እንዳለበት የሚያብራሩ መፈናቀልን የሚያስከትሉ የፕሮጀክቱ ክፍለ አካላት ወይም እንቅስቃሴዎች፤
b. እንዲህ ያሉት ክፍላተ አካላት ወይም እንቅስቃሴዎች የተፅዕኖ ቀጠና፡-
c. የመሬት መያዝ እና በመሬት ላይ ባሉ ግንባታዎች እና ሌሎች ቋሚ እሴቶች ወሰን እና ደረጃ፤
d. በመሬት ወይም የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም፣ ወይም መዳረሻ ላይ በፕሮጀክቱ የሚጣሉ ማናቸውም ገደቦች፤
e. መፈናቀልን ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ ከግምት የገቡ አማራጮች እና ውድቅ የተደረጉት ደግሞ ለምን ውድቅ እንደተደረጉ፤ እና
f. በተቻለ መጠን በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት መፈናቀልን ለመቀነስ የተቋቋሙ ዘዴዎች።

**ዓላማዎች።** የዳግም ሰፈራው ፕሮግራም ዋንኛ ዓላማዎች።

**የሕዝብ ቆጠራ ዳሰሳ ጥናት እና የመሠረታዊ መነሻ ሶሺዮኢኮኖሚያዊ ጥናቶች።** ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ግለሰቦችን ለይቶ ለማወቅ እና ለመቁጠር ቤት ለቤት የሚደረገው የሕዝብ ቆጠራ ግኝቶች እና ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ግለሰቦች በማሳተፍ መሬት፣ በመሬት ላይ ያሉ ግንባታዎች እና ሌሎች ቋሚ እሴቶች ላይ የሚደረግ ዳሰሳ ጥናት በፕሮጀክቱ የሚከናወኑ ይሆናሉ። የሕዝብ ቆጠራው ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወንም ጭምር ያገለግላል፡-

a. የተፈናቀለው ሕዝብ የአመራረት ሥርዓቶች፣ ሠራተኝ፣ እና የቤተሰብ ድርጅት ዝርዝር መግለጫ፤ እና በኑሮ ዘይቤዎች ላይ መሠረታዊ መረጃ (እንደ ተገቢነቱ የምርት ደረጃዎች እና ከመደበኛ እና ኢመደበኛ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የተገኘ

ገቢ ጨምሮ) እና (የጤና ሁኔታን ጨምሮ) የኑሮ ደረጃ ጨምሮ የተፈናቀሉ ቤተሰቦችን መገለጫ ባሕሪያትን ለይቶ ማወቅ፤

b. ልዩ ድንጋጌ ሊደረግላቸው የሚገባ ለጥቃት ተጋላጭ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ላይ የሚሰበሰብ መረጃ፤

c. ተፅዕኖ ሊያርፍባቸው የሚችሉ የሕዝብ ወይም የማኅበረሰብ መሠረተ ልማቶችን፣ ንብረቶችን ወይም አገልግሎቶችን ለይቶ ማወቅ፤

d. ለዳግም ማቋቋሚያ ፕሮግራሙ ዲዛይን እና በጀት ምደባ የሚሆን መሠረትን ማስቀመጥ፤

e. ከቀን ቆረጣ ጋር ጎን ለጎን፣ ብቁነት የሌላቸው ሰዎች የካሳ እና የዳግም ማቋቋሚያ ድጋፍ እንዳያገኙ ነጥሎ ማውጣት የሚያስችል መሠረትን መጣል፤ እና ለክትትል እና ለምዘና ዓላማዎች ጠቃሚ የሆኑ መሠረታዊ ሁኔታዎችን ማቋቋም፤

f. ባንኩ አስፈላጊ ነው ብሎ ሊያምንበት በሚችልበት መልኩ፣ የሕዝብ ቆጠራውን ለመደገፍ ወይም መረጃ ለመስጠት በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ጥናቶችን ማድረግ ያስፈልግ ይሆናል፤

g. ሰዎች ኑሯቸውን የሚገፉባቸው እና ዕለት ጉርሳቸውን የሚያገኙባቸው የተለምዱ የንብረትና የተፈጥሮ ሀብት ግብዓቶች፣ (ዓሣ ማስገሪያ ቦታዎች፣ የግጦሽ መሬት፣ ወይም ከደን አካባቢ የሚገኙ ጥቅማ ጥቅሞች ጨምሮ) በአካባቢ በታወቁ የመሬት ምደባ ዘዴዎች የሚተዳደሩ የባለቤትነት መብት የሌላቸው መሬትን በጋራ ባለቤትነት መያዣ ሥርዓቶች፣ እና ፕሮጀክቱ በሚገኝበት ቦታ ላይ ባሉ የተለያዩ የመሬት ይዞታ ሥርዓቶች ምክንያት የሚፈጠሩ ምክንያቶች ቆጠራ ጨምሮ የመሬት ይዞታ እና የሽግግር ሥርዓቶች፤

h. ማኅበራዊ አውታረ መረቦችን እና ማኅበራዊ የመደጋገፍ ሥርዓቶችን እንዲሁም እንዴት እነዚህ በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ሊያርፍባቸው እንደሚችል ጨምሮ ተፅዕኖ በሚያርፍባቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ ያለው ማኅበራዊ ትስስር ጠባዮች፤ እና

i. ለምክክር ስትራቴጂ እና የዳግም ማቋቋሚያ እንቅስቃሴዎች ዝግጅት እና አፈጻጸም ጋር ተዛማጅነት ሊኖራቸው የሚችሉ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ ተቋማት (ለምሳሌ የማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ የእምነት ቡድኖች፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያዶች)) ጨምሮ የተፈናቀሉ ማኅበረሰቦች ማኅበራዊ እና ባህላዊ መገለጫ ባሕሪያት።

***ሕጋዊ ማዕቀፍ።*** የሚከተሉትን የሚሸፍን የሕጋዊ ማዕቀፍ ትንታኔ ግኝቶች፡-

a. የአስገዳጅ መሬት ይዞታ ሥልጣን እና የመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣል ገደብ ወሰን እንዲሁም የዋጋ አሰጣጥ ዘዴን እና የክፍያ አፈጻጸም የጊዜ መርሐ ግብርን ሁሉቱንም ከግምት በማስገባት ከዚህ ጋር ግንኙነት ያለው ተከፋይ ካሳ ዓይነት፣

b. በፍትሕ አሰጣጥ ሥርዓቱ ሂደት የተፈናቀሉ ሰዎች ማግኘት የሚችሏቸው መፍትሔዎች ዝርዝር መግለጫ እና እንዲህ ላሉት የፍትሕ ሥርዓት አሠራሮች አስፈላጊ የሆነው የጊዜ መርሐግብር ማዕቀፍ እንዲሁም ማናቸውም ከፕሮጀክቱ ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችሉ በቦታው ላይ ያሉ የቅሬታ አቀራረብ ዘዴዎች ጨምሮ አግባብነት ያላቸው ሕጋዊ እና አስተዳደራዊ የአሠራር ሥርዓቶች፤

c. የዳግም ማቋቋም እንቅስቃሴዎችን ለመተግበር ኃላፊነት ከሚወስዱ ኤጀንሲዎች ጋር የተገናኙ ሕጎች እና ደንቦች፤ እና

d. አስገዳጅ የመሬት ይዞታ፣ በመሬት አጠቃቀም ላይ የሚጣሉ ገደቦችን እና የዳግም ማቋቋሚያ እርምጃዎች አቅርቦት እና አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 5 (ESS5) እንዲሁም እንዲህ ያሉ ክፍተቶችን ለመሙላት የተዘጋጁ ዘዴዎችን የሚሸፍኑ በአካባቢ ሕጎች እና ልማዶች መካከል ክፍተቶች፣ ካሉ።

***ተቋማዊ ማዕቀፍ።*** የሚከተሉትን የሚሸፍን የተቋማዊ ማዕቀፍ ትንታኔ ግኝቶች፡-

a. ለዳግም ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ኃላፊነትን ሊወስዱ የሚችሉ ኤጀንሲዎችን እና ለተፈናቀሉ ግለሰቦች ድጋፍ መስጠትን ጨምሮ በፕሮጀክት ትግበራ ላይ ሚና ሊኖራቸው የሚችሉ መያዶችን/የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች (CSOs) ለይቶ ማወቅ፤

b. እንደዚህ ያሉ ኤጀንሲዎች፣ መያዶች/የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች (CSOs) ምዘና፤ እና

c. ለዳግም ማቋቋም ሥራ ትግበራ ኃላፊነትን የሚወስዱ ኤጀንሲዎች እና መያዶች/የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች (CSOs) ተቋማዊ አቅምን ለማበልፀግ እንደ ሐሳብ የቀረቡ ማናቸውም እርምጃዎች።

**ብቁነት።** ተዛማጅነት ያላቸው የተቆረጡ ቀናቶች ጨምሮ፣ ለተፈናቀሉ ሰዎች ማንነት የሚሰጠው ፍቺ እና ካሳ እንዲሁም ሌሎች የዳግም ማቋቋሚያ እገዛዎችን ለማግኘት ያላቸውን ብቁነት ለመወሰን ጥቅም ላይ የሚውሉ መስፈርቶች።

**ለሚደርሱ ኪሣራዎች ዋጋ ማውጣት እና ካሳ መስጠት።** ለሚደርሱ ኪሣራዎች መተኪያ ዋጋቸውን ለመወሰን ጥቅም ላይ የሚውለው ዘዴ፤ እና ለመሬት፣ ለተፈጥሮ ሀብቶች እና ሌሎች እሴቶች በአካባቢ ሕጎች ሊሰጥ የታሰበው ካሳ ዓይነቶች እና ደረጃዎች ዝርዝር መግለጫ እና እንዲህ ያሉት መተኪያ ዋጋ ለማግኘት አስፈላጊ የሆኑ ደጋፊ እርምጃዎች።

**የማኅበረሰብ ተሳትፎ።** የተፈናቃይ ግለሰቦች ተሳትፎ (አግባብነት ሲኖረው ተቀባይ ማኅበረሰቦችን ጨምሮ)፦

a. ምክክር የሚደረግበት ስትራቴጂ ዝርዝር መግለጫ፣ እና በዲዛይን እና በማቋቋሚያ አንቅስቃሴዎች ትግበራ ላይ የተፈናቀሉ ሰዎች ተሳትፎ፤

b. የተሰጡ አስተያየቶች እና እነዚህ አስተያየቶች እንዴት የዳግም ማቋቋሚያ ዕቅዱን በማዘጋጀት ላይ እንዴት ከግምት እንደገባ የሚያሳይ አጭር ማጠቃለያ፤

c. የቀረቡ የዳግም ማቋቋም አማራጮች ግምገማ እና ለእነርሱ የቀረቡ አማራጮችን በተመለከተ ተፈናቃይ ግለሰቦች የመረጧቸው ምርጫዎች፤ እና

d. ተፈናቃይ ግለሰቦች ያሏቸውን ጥያቄዎች ለፕሮጀክቱ ባለሥልጣናት በዕቅድ አወጣጥ እና ትግበራው ሂደት ላይ ማቅረብ የሚችሉባቸው ተቋማዊ ምቹ ሁኔታዎች፣ እና እንደ የአካባቢው ተወላጆች፣ ሕዳጣኖች፣ መሬት አልቦዎች እና ሴቶች የመሳሰሉ ለጥቃት ተጋላጭ ቡድኖች በበቂ ሁኔታ መወከላቸውን ለማረጋገጥ የሚወሰዱ እርምጃዎች።

**የትግበራ መርሐግብር** መፈናቀሉ ይከናወናል ተብሎ የሚጠበቅባቸው ቀናት እና ለሁሉም የዳግም ማቋቋሚያ ዕቅድ እንቅስቃሴዎች ማስጀመሪያና ማጠናቀቂያ ቀናትን የያዘ የትግበራ መርሐግብር። መርሐግብሩ የዳግም ማቋቋሚያ እንቅስቃሴዎቹ እንዴት ከአጠቃላዩ ፕሮጀክት ትግበራ ጋር እንደሚገናኝ ማሳየት አለበት።

**ወጪዎች እና በጀት።** ለዋጋ ግሽበት የሚሰጡ ድጎማዎች፣ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት፣ እና ሌሎች መጠባበቂያ ገንዘቦች፤ የገንዘብ አወጣጥ የጊዜ ሰሌዳዎች፣ የገንዘብ ምንጮች፣ እና ገንዘቦች ጊዜውን የጠበቀ ፍሰት እንዲኖራቸው ዘዴዎች፣ ከፈጻሚው ኤጀንሲ የሥራ ክልል ውጭ ባሉ ቦታዎች ላይ ማግኘት የሚቻል ከሆነ የማቋቋሚያ ገንዘብ አቅርቦት ጨምሮ ለሁሉም የዳግም ማቋቋሚያ እንቅስቃሴዎች በምድብ የተከፋፈሉ የወጪ ግምቶችን የሚያሳዩ ሠንጠረዦች።

**የቅሬታ አፈታት ዘዴ።** ዕቅዱ ለሦስተኛ ወገን ከመፈናቀል ወይም ዳግም መቋቋም ጋር በተገናኘት የሚነሡ አለመግባባቶችን ለመፍታት ዋጋቸው ተመጣጣኝ እና ተደራሽ የሆኑ አሠራር ሥርዓቶችን ያብራራል፤ እንዲህ ያለው የቅሬታ አቀራረብ ዘዴዎች የፍትሕ ሥርዓት፣ የማኅበረሰብ እና ባህላዊ የአለመግባባትን መፍቻ መንገዶች ተገኝነት ከግምት ማስገባት መቻል አለባቸው።

**ክትትል እና ግምገማ።** የተሟላ እና ሚዛናዊ መረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ፣ ለዳግም ማቋቋሚያ እንቅስቃሴዎች ግቤቶችን፣ ውጽአቶችን ን ውጤቶችን ለመለካት የሚያስችሉ የአፈጻጸም ክትትል ማድረጊያ ጠቋሚዎች፣ በክትትል ሂደቱ የተፈናቀሉ ግለሰቦች ተሳትፎ፣ ሁሉም የዳግም ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ተከናውነው ካለቁ በኋላ ተቀባይነት ላለው ክፍለ ጊዜ ያክል የሚቆይ የውጤቶች ምዘና፤ ተከትሎ የሚመጣ ትግበራን ለመምራት የዳግም ማቋቋሚያ ሥራውን ክትትል ውጤቶች መጠቀም ጋር በፈጻሚው ኤጀንሲ በመፈናቀል እና ዳግም ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ላይ የሚደረጉ ክትትሎች አደረጃጀት፣ በባንኩ ተገቢነት እንዳለው በሚረጋገጥ በሦስተኛ ወገን ተቆጣጣሪዎች የሚደረግ ክትትል።

**የተስማሚ አስተዳደር ዝግጅቶች።** ዕቅዱ በፕሮጀክቱ ሁኔታዎች ላይ ለሚያጋጥሙ ያልተጠበቁ ለውጦች ወይም አጥጋቢ የዳግም ማቋቋም ውጤቶች ላይ ከመድረስ የሚያግዱ ያልተጠበቁ መሰናክሎች ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ የዳግም ማቋቋሚያ ትግብራን አጣጥሞ ለማዘጋጀት የሚረዱ ዕሳቤዎችን በውስጡ ማካተት አለበት።

## ዓባሪ 7፡- የአካባቢ ተወላጆች ዕቅድ አዘጋጀት ማዕቀፍ ጠቋሚ

አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7) በአንድ ተለይቶ የታወቀ የተወሰነ ልዩ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ቡድን ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። እንዲህ ላሉት ቡድኖች ጥቅም ላይ የሚውለው ቃል ከአገር ወደ አገር ይለያያል፣ እና ብዙውን ጊዜ ብሔራዊ ከግምት የሚገቡ ነገሮችን ያንፀባርቃል። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7) ተለይተው የታወቁ ቡድኖች በተለያዩ አገሮች በተለያዩ ስያሜዎች ሊታወቁ እንደሚችሉ ከግምት በማስገባት "ወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች" የሚለውን መጠሪያ ስም ይጠቀማል። እንዲህ ያሉት መጠሪያ ስሞች "ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች"፣ "ተወላጅ ኅዳጣኖች"፣ "ጥንታዊ ሰዎች/ አቦርጂኖች"፣ "በኮረብታ ላይ የሚኖሩ ነገዶች"፣ "ለጥቃት የተጋለጡ እና የተገለሉ ቡድኖች"፣ "ኅዳጣን ዜጎች"፣ "ተለይተው የተያዙ ነገዶች"፣ "የመጀመሪያዎች የአገሬው ሰዎች" ወይም "የጎሣ ቡድኖች" የሚሉ ስያሜዎችን ያካትታሉ። በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 7 (ESS7) የተቀመጡትን መስፈርቶች እስካሟሉ ድረስ እንዲህ በመሳሰሉት በሁሉም ቡድኖች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል። ለዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ዓላማዎች፣ "ወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች" የሚለው አባባል እንዲህ ያሉትን ሁሉንም አማራጭ ቃላት ያካትታል።

### 1. ዓላማዎች

ዓላማዎቹ እነዚህ ናቸው፡-

a. የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦችን ሰብአዊ መብቶች፣ ክብር፣ ተስፋዎች፣ ማንነት፣ ባህል እና ተፈጥሮ ሀብት ላይ የተመረኮዘ ኑሮን ሙሉ አክብሮት ሰጥቶ የልማት ሂደቱ ማጎልበት መቻሉን ማረጋገጥ።

b. በየአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ላይ ፕሮጀክቶች የሚያደርሱን አስከፊ ተፅዕኖዎች ማስቀረት ወይም ይህን ማስቀረት ሳይቻል ሲቀር እንዲህ ያሉትን ተፅዕኖዎች መቀነስ፣ አራቂ እርምጃዎችን መውሰድ እና/ወይም ካሳ መስጠት።

c. ለየአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ተደራሽ፣ በባህል ተቀባይነት ባለው እና ሁሉን አካታች የሆነ ዘላቂነት ያለው የልማት ተጠቃሚነት እና ዕድሎችን ማበረታታት።

d. የፕሮጀክት ዲዛይንን ማሻሻል እና በፕሮጀክቱ ተፅዕኖ ያረፈባቸውን በፕሮጀክቱ የሕይወት ዑደት ወቅት በጠቅላላ ከየአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ጋር ትርጉም ያለው ምክክርን በማድረግ ቀጣይነት ያለው ግንኙነት መፍጠር እና ግንኙነቱን ጠብቆ ማቆየት።

e. በዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ውስጥ በሦስት ሁኔታዎች ውስጥ ተፅዕኖ ያረፈባቸውን የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የሚሰጡትን የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) ለማግኘት።

f. የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦችን ባህል፣ ዕውቀት እና ልማዶች ዕውቅና ለመስጠት፣ ለማክበር እና ጠብቆ ለማቆየት እንዲሁም ለእነርሱ ተቀባይነት ባለው አግባብ እና የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ እየተለወጡ ካሉ ሁኔታዎች ጋር ራሳቸውን ለማጣጣም የሚያስችላቸውን ዕድል ለእነርሱ መስጠት።

### 2. የትግበራው ወሰን

አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) በአንድ ተለይቶ የታወቀ የተወሰነ ልዩ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ቡድን ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። በአንዳንድ አገሮች ውስጥ፣ እንዲህ ያሉት ቡድኖች እንደ "የአካባቢ ተወላጆች" በመባል ይታወቃሉ። በሌሎች አገራት ውስጥ በሌላ ስሞች ሊታወቁ ይችሉ ይሆናል፣ ለአብነት "ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች"፣ "ተወላጅ ኅዳጣኖች"፣ "ጥንታዊ ሰዎች/ አቦርጂኖች"፣ "በኮረብታ ላይ የሚኖሩ ነገዶች"፣ "ለጥቃት የተጋለጡ እና የተገለሉ ቡድኖች"፣ "ኅዳጣን ዜጎች"፣ "ተለይተው የተያዙ ነገዶች"፣ "የመጀመሪያዎች የአገሬው ሰዎች" ወይም "የጎሣ ቡድኖች" የሚሉ ስያሜዎችን ያካትታሉ። "የአካባቢ ተወላጆች" የሚለው አባባል ከአገር ወደ አገር በሰፊው የሚለያይ እንደመሆኑ፣ ተበዳሪው ከሚገኝበት አገር ብሔራዊ ዓውድ አንፃር ተገቢነት ያለው አማራጭ መጠሪያ ስም ለአካባቢ ተወላጆች ባንኩ እንዲጠቀም ተበዳሪው ሊጠይቅ ይችላል። ምንም ዓይነት ስያሜ በጥቅም ላይ ቢውልም የዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) መስፈርቶች በሁሉም እንዲህ ያሉ ቡድኖች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። ይህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) በብሔራዊ ዓውድ ውስጥ የአካባቢ ተወላጆችን ለመጥቀስ የተለያዩ ስያሜዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ እንደሚችሉ ዕውቅና በመስጠት "የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች" የሚለውን ስያሜ ይጠቀማል።

የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች (በብሔራዊው ዓውድ ውስጥ ሊጠቀሱ በሚችሉበት ስም) በሚገኙበት ጊዜ ላይ ሁሉ ወይም በአካባቢያዊ እን ማኅበራዊ ምዘና ወቅት በሚወሰነው መሠረት በአንድ እንደ ሐሳብ የቀረበ ፕሮጀክት አካባቢ ላይ የጋራ የሆነ ትስስር በሚኖራቸው ጊዜ ይህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ተፈጻሚነት ይኖረዋል። የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ በሆኑ መልኩ ተፅዕኖ እንደ ደረሰባቸው ከግምት ሳይገባ እና የእነዚህ ማናቸውም ተፅዕኖዎች ጉልህነት ከግምት ሳይገባ ይህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ከዚህ በተጨማሪ ምንም እንኳ የተጋላጭነት ባሕሪ እና ደረጃ ርትዓዊ የሆነ የጥቅማ ጥቅሞች ተደራሽነት ለማበረታታት ወይም አስከፊ ተፅዕኖዎችን ለማረቅ እንደ ቁልፍ ከግምት የሚገባ ነጥብ ዕቅዶችን በማዘጋጀት ወቅት ጥቅም ላይ የሚውል ቢሆንም በጉልህ የሚታይ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ወይም ማኅበራዊ ተላጭነቶች መኖር ወይም አለመኖር ከግምት ሳይገባ ይህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

በዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ውስጥ፣ "የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች" የሚለው አባባል (ወይም በብሔራዊ ዓውድ ውስጥ አማራጭ አባባልን በመጠቀም ሊጠቀሱ በሚችሉበት ስያሜ) የሚከተሉትን መገለጫ ባሕሪያት በተለያዩ ደረጃዎች የሚያንጸባርቅ ለየት ያለ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ቡድንን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ አባባል ነው፡-

a. የአንድ ለየት ያለ አገር በቀል ማኅበራዊ እና ባህላዊ ቡድን ራሳቸውን እንደ አባላት ለይቶ መግለጽ እና ይህም ማንነት በሌሎች ዕውቅና የተሰጠው ሲሆን፤ እና

b. በወል የተያዘ በጂኦግራፊያዊ መንገድ የተለየ መኖሪያ ቦታ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየ የራስ ግዛት ወይም በወቅት የተከፋፈለ የቦታዎች አጠቃቀም ወይም ይዞታ እንዲሁም በእነዚህ ቦታዎች ላይ የሚኖር የተፈጥሮ ሀብቶች የወል አጠቃቀም፤ እና

c. ለየት ያሉ ወይም ከዋናው የታወቀ ማኅበረሰብ ወይም ባህል የተነጠሉ ልማዳዊ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ ወይም ፖለቲካዊ ተቋማት፤ እና

d. ከኦፊሴላዊው ቋንቋ ወይም ከአገሪቱ ወይም ከሚኖሩበት ክልል ቋንቋዎች ብዙውን ጊዜ የተለየ ራሱን የቻለ ቋንቋ ወይም የአነጋገር ዘይቤ።

በአስገዳጅ የሆነ ከባድ ችግር፣ ግጭት፣ በመንግሥት የሰፈራ ፕሮግራሞች፣ መሬታቸው ስለተነጠቀ፣ በተፈጥሮ አደጋ፣ ወይም እንዲህ ያሉ ቦታዎች ወደ ከተማ እንዲካለሉ በመደረጉ ምክንያት በማኅበረሰቡ ወይም ቡድን የሕይወት ዘመን ወቅት ለየት ካሉ

በፕሮጀክቱ አካባቢ የሚገኙ መኖሪያ ቦታዎች ወይም ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ የነበሩ ቦታዎች የነበራቸውን ቁርኝት ያጡ የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦችን በያዙ ማኅበረሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ይህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) በተጨማሪ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ይህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) በተጨማሪ በጫካ ውስጥ በሚኖሩ፣ አዳኝ-ፍራፍሬ በመልቀም የሚኖሩ፣ አርብቶ አደሮች ወይም ሌላ ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስ የሚኖሩ ቡድኖች ላይ መስፈርቶቹን እስካሟሉ ድረስ ተፈጻሚ ይሆናል።

የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች በቦታው እንዳሉ ወይም በፕሮጀክት አካባቢው ላይ የወል ቁርኝት እንዳላቸው በዓለም ባንክ ከተወሰነ በኋላ፣ ተበዳሪው የምክክር፣ የዕቅድ አወጣጥ ወይም የዚህን የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ሌሎች መስፈርቶች ለማሟላት እንዲችል ተገቢነት ካላቸው ስፔሺያሊስቶች ግብዓቶችን ለማግኘት እንዲሞክር ሊገደድ ይችላል። የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች (በብሔራዊ ዓውድ ሊጠሩ በሚችሉበት ሌላ ስም) ማንነት ለይቶ ለማወቅ በፕሮጀክት ምርመራ ወቅት እነዚህ ሂደቶች በዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 8 (ESS8) የተቀመጡትን መስፈሮች እስካሟላ ድረስ ያሉትን ብሔራዊ የአፈጻጸም ሂደቶች የዓለም ባንክ የሚከተል ይሆናል።

**አጠቃላይ**

የዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ቁልፍ ዓላማ በፕሮጀክቱ አካባቢ ውስጥ የሚገኙ ወይም የወል ቁርኝት ያላቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ሙሉ በሙሉ ስለ ፕሮጀክቱ ምክክር እንዲያደርጉ መደረጉን እና በፕሮጀክት ዲዛይን፣ እና በፕሮጀክት ትግበራ ዕቅዶች አወሳሰን ላይ በንቃት ለመሳተፍ ዕድሎች እንዳላቸው ለማረጋገጥ ነው። የምክክሩ ወሰን እና ደረጃ እንዲሁም ተከትሎ የሚመጣው የፕሮጀክት ዕቅድ አወጣጥ እና ሰነድ አያያዝ ሂደቶች የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ላይ ሊያደርሱ በሚችሉት የፕሮጀክት ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ወሰን እና ደረጃ ልክ የሚመጣጠኑ ይሆናሉ።

ተበዳሪው በፕሮጀክቱ አካባቢ የሚገኙ ወይም ከቦታው ጋር በወል ቁርኝት ያላቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ላይ ይደርሳል ተብሎ የሚጠበቀውን ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ (ባህላዊ ቅርሶችን ጨምሮ) እና አካባቢያዊ ተፅዕኖዎችን ይገመግማል። ተበዳሪው የምክክር ስትራቴጂ ያዘጋጃል እንዲሁም ተፅዕኖ ያረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች እና በፕሮጀክት ዲዛይን እና ትግበራ ላይ ተሳታፊ የሚሆኑበትን መንገድ ለይቶ ያስቀምጣል። በመሆኑም፣ ውጤታማ የሆነ የፕሮጀክት ዲዛይን እና የሰነድ አያያዝ ከዚህ በታች እንደተገለጸው ይዘጋጃል።

ተበዳሪው እንደ ሐሳብ የሚያቀርባቸው እርምጃዎች እና ውሳኔ ሐሳቦች ተፅዕኖ ካረፈባቸው ከየአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ምክክር በማድረግ ያዘጋጃል እና እንደ የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ዕቅድ በመሳሰሉ በጊዜ ገደብ በተቀየደ ዕቅድ ውስጥ እንዲካተት ያደርጋል። የዕቅዱ ወሰን እና ደረጃ ከፕሮጀክት ሊያከትል የሚችላቸው ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ጋር ተመጣጣኝ ይሆናል። የዕቅዱ ቅርጸት እና አርዕስት ከፕሮጀክቱ ወይም ከአገሩ ዓውድ አንፃር እንዳለው ተገቢነት እየታየ ይስተካከላል እንዲሁም ለአካባቢ ተወላጆች የቀረበ ማናቸውንም አማራጭ ስያሜ የሚያንፀባርቅ ይሆናል።

**አስከፊ ተፅዕኖዎችን ማስቀረት**

በአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ላይ የሚደርሱ አስከፊ ተፅዕኖዎች በተቻለ መጠን ለማስቀረት ጥረት ይደረጋል። አማራጮች በሚገባ ከታሰሱ በኋላ አስከፊ ተፅዕኖዎችን ማስቀረት ሳይቻል ሲቀር፣ እንዲህ ያሉት ተፅዕኖዎች ካላቸው ባሕሪ እና ደረጃ ጋር በሚመጣጠን መልኩና በባህል አንፃር አገባብነት ባለው መንገድ እንዲሁም ተፅዕኖ ባረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ተጋላጭነት ዓይነት እና ደረጃ ልክ ተፅዕኖዎቹን ተበዳሪው ይቀንሳል እና/ወይም ካሳ ያቀርባል።

ከውጭው ዓለም ጋር ውስን ግንኙነት ያላቸውን፣ በተጨማሪ “በፈቃደኝነት ራሳቸውን ያገለሉ”፣ “ከሰው የተነጠሉ ሰዎች” ወይም “ለመጀመሪያ ጊዜ ሰውን የሚያገኙ ሰዎች” በመባል የሚታወቁት ሰዎች በሚኖሩበት በርቀት የሚኖሩ ቡድኖች ላይ ፕሮጀክቶች ተፅዕኖ ሊፈጥሩ የሚችሉባቸው ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ፣ ተበዳሪው የእነርሱን መሬት እና ግዛቶች፣ አካባቢ፣ ጤና እና ባህል ዕውቅና ለመስጠት፣ ለማክበር እና ጥበቃ ለማድረግ የሚያስችሉ ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል እንዲሁም በፕሮጀክቱ መዘዝ ከእነርሱ ጋር ያልተፈለገ ዓይነት ግንኙነትን በሙሉ ለማስቀረት የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል። እንዲህ ያለውን ግንኙነት የሚፈጥሩ የፕሮጀክቱ ጉዳዮች ከዚያ በላይ እንዲገፉ አይደረጉም።

**ማስታረቂያ እርምጃ እና የልማት ጥቅማ ጥቅሞች**

ተበዳሪው እና የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS)1 በተዘረዘረው የማስታረቂያ እርምጃ ተዋረዳዊ ሰንሰለት ጋር እና በባህል ተገቢነት ካላቸው እና ዘላቂነት ያላቸው የልማት ጥቅማ ጥቅሞች ከሚያስገኙ ዕድሎች ጋር ሊወሰዱ የሚችሉ የማስታረቂያ እርምጃዎችን ለይተው ያስቀምጣሉ። የምዘና እና ማስታረቂያ እርምጃው መጠነ ስፋት ባህላዊ ተፅዕኖዎችን እና አካላዊ ተፅዕኖዎችን የሚያካትት ይሆናል። ተፅዕኖ ላረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ከስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን እርምጃዎች በተቀመጠላቸው ጊዜ ገደብ እንደሚከናወኑ ተበዳሪው ያረጋግጣል።

ተፅዕኖ ላረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች የሚሰጠው ካሳ እና የሚጋሩ ጥቅማ ጥቅሞች ውሳኔ፣ አቀራረብ እና ስርጭት የእነዚህን የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ተቋማት፣ ደንቦች እና ልማዶች እንዲሁም ከዋናው ማኅበረሰብ ጋር ያላቸውን መስተጋብር መጠን ከግምት የሚያስገባ ይሆናል። ካሳ ለማግኘት ያለው ብቁነት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ የተመረኮዘ ወይም የሁለቱም ጥምረት ሊሆን ይችላል። ካሳ የሚሰጠው በቡድን ደረጃ በሚሆንበት ጊዜ፣ ካሳው ለሁሉም ብቁ የሆኑ አባላት በውጤታማ መንገድ እንዲከፋፈል ወይም የቡድኑን አባላት በሚጠቅም መልኩ ካሳው በጋራ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማበረታታት የሚያስችሉ ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ዘዴዎች ተበይነው በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋሉ።

የፕሮጀክቱ ባሕሪ፣ የፕሮጀክቱ ዓውድ እና ተፅዕኖ ያረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ተጋላጭነት ጨምሮ ሆኖም ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን የተለያዩ መመዘኛ መስፈርቶች ተፅዕኖ ያረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ከፕሮጀክቱ እንዴት ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ የሚወስኑ ይሆናሉ። የእነርሱን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፣ ለባህል ተቀባይነት ባለው መንገድ ኑሯቸውን ማሻሻል እንዲሁም እነርሱ ጥገኛ የሆኑባቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ዘላቂታማ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ጨምሮ ተለይተው የታወቁ ዕድሎች ተፅዕኖ ያረፈባቸውን የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ግቦች እና ምርጫዎችን የማሟላት ዓላማ ይኖራቸዋል።

**ለየአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀ ትርጉም ያለው ምክክር**

ውጤታማ የሆነ የፕሮጀክት ዲዛይንን ለማዘጋጀት፣ የአካባቢ ፕሮጀክት ድጋፍ ወይም ባለቤትነትን ለመገንባት፣ እና ከፕሮጀክት ጋር የተገናኙ መዘግየቶችን ወይም እሰጣ አገባዎችን ስጋት ለመቀነስ፣ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS 10) በተደነገገው መሠረት ተፅዕኖ ካረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ጋር የማሳተፍ ሂደትን ተበዳሪው የሚያከናውን ይሆናል። ይህ የማሳተፍ ሂደት የባለድርሻ አካል ትንታኔ እና የተሳትፎ ዕቅድ አወጣጥ፣ የመረጃ ይፋ ማውጣት እና በባህል ተቀባይነት ባለውም መንገድ እና ሥርዓተ ጾታን እና የተለያየ ዕድሜ ላይ ያሉ ሰዎችን አሳታፊ በሆነ መልኩ ትርጉም ያለው ውይይት ማድረግን የሚያካትት ይሆናል። ለየአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች፣ ትርጉም ያለው ምክክር በተጨማሪ፡-

a. የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ተወካይ አካላት እና ድርጅቶችን ማሳተፍ (ለምሳሌ የሽማግሌዎች መማክርት ጉባኤ ወይም የመንደር ምክር ቤቶች ወይም የጎሣ አለቆች) እና ተገቢነት ሲኖረው ሌሎች የማኅበረሰቡን አባላት ማሳተፍ፤

b. ለየአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች በውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ እንዲሳተፉ በቂ የሆነ ጊዜ መስጠት፤ እና

c. እነርሱን በአዎንታዊ ወይም በአሉታዊ መንገድ ተፅዕኖ ሊያሳርፉባቸው በሚችሉ የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ወይም የማስታረቂያ እርምጃዎች ዝግጅት ወቅት የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ውጤታማ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማስቻል።

**3. በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) መስጠትን የሚጠይቁ ሁኔታዎች**

የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች መሬታቸው ሊያጡ፣ ከመሬታቸው ሊነጠሉ ወይም መሬታቸው ላይ ብዝበዛ ሊደረግባቸው እና ለተፈጥሮ እና የባህል ሀብቶች ያላቸውን መዳረሻ ሊያጡ ይችሉ ይሆናል። ይህን የጥቃት ተጋላጭነት ዕውቅና በመስጠት፣ ከዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) (ክፍል ሀ) ላይ ከተቀመጡት አጠቃላይ መስፈርቶች እና በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 1 እና 10 (ESS1 እና 10) በተጨማሪ፣ ተበዳሪው ተፅዕኖ ያረፈባቸውን የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ፕሮጀክቱ የሚከተሉት እንደሚኖሩት በመጥቀስ በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫን (FPIC) ያገኛል፡-

a. በባህላዊ ባለቤትነት ወይም በልማዳዊ አጠቃቀም ወይም ይዞታ ሥር በመመርኮዝ በመሬት እና ተፈጥሮ ሀብቶች ላይ አስከፊ ተፅዕኖዎች ሊኖሩት ይችላሉ፤

b. የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ከባህላዊ ባለቤትነት ወይም በተለምዶ ከነበረ አጠቃቀም ወይም ይዞታ ከመሬት እና ተፈጥሮ ሀብቶች አንሥቶ ወደ ሌላ ቦታ ማስፈርን ሊያስከትል ይችላል፤ ወይም

c. ተፅዕኖ ባረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ሕይወት ላይ በማንነታቸው እና/ወይም ባህላዊ፣ ክብረ በዓላዊ ወይም መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ በተጨባጭ የሚታይ የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ባህላዊ ቅርሶች ላይ ጉልህ ተፅዕኖዎች ሊኖሩት ይችላል።

በእነዚህ ሁኔታዎች ወቅት፣ ተበዳሪው የፕሮጀክቱን ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ለይቶ በማወቅ ላይ እንዲያግዙ ገለልተኛ የሆኑ ስፔሺያሊስቶችን እንዲሳተፉ ያደርጋል።

በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኘ ትርጓሜ የለም። ለዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ሲባል በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) እንደሚከተለው ተቀምጧል፦

a. በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) ወሰን በፕሮጀክት ዲዛይን፣ ትግበራ አደረጃጀቶች እና ተፅዕኖ ባረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ላይ ባሉት ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ጋር በተገናኘ ከሚጠበቁ ውጤቶች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤

b. በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 10 (ESS10) ላይ የተብራራውን ትርጉም ያለው ውይይት ሂደት ላይ በመንላበት የሚስፋፋ ይሆናል እንዲሁም በተበዳሪው እና ተፅዕኖ ባረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች መካከል በጥሩ መተማመን በሚደረግ ድርድር መሠረት የሚቋቋም ይሆናል፤

c. ተበዳሪው የሚከተሉትን በሰነድ ይይዛል፦ (i) በተበዳሪው እና የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች መካከል ከስምምነት የተደረሰበትን የመተማመን ድርድር ውጤቶችን በሥራ ላይ ለማዋል ከስምምነት የተደረሰበትን ሂደት የሚያሳይ፤ እና (ii) ሁሉም ስምምነት ላይ የተደረሰባቸውን እና እንዲሁም ተቃራኒ ሐሳቦችን ጨምሮ በተበዳሪው እና የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች መካከል በቀና ልቦና የተደረጉ ድርድሮች ውጤት፤ እና

d. በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) ስምምነትን አይጠይቅም እና ተፅዕኖ ባረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ውስጥ ያሉ ወይም በመካከላቸው የሚገኙ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በግልጽ እንዳልተስማሙ ቢገልጹም ማረጋገጫው ሊገኝ ይችላል።

ለዚህ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት (ESS) ዓላማዎች፣ እነርሱ ላይ ተፅዕኖ ለሚያሳርፉባቸው የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ተፅዕኖ ካረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች በባህል አንፃር ተቀባይነት ባለው መንገድ የሚገኝን የወል ድጋፍ የሚመለከት ነው። አንዳንድ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እንዲህ ያሉትን የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ቢቃወሙም ማረጋገጫውን ማግኘት ይቻላል።

ተፅዕኖ ያረፈባቸውን የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) በባንኩ ሊረጋገጥ በማይችልበት ጊዜ፣ ተፅዕኖ ያረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ጋር ግንኙነት ባለው የፕሮጀክቱ ጉዳዮች የተሰጠው ሊረጋገጥ ያልቻለው በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) ከዚህ በላይ ሊስተናገድ አይችልም። ባንኩ ተፅዕኖ ባረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች የተሰጠውን በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) ማረጋገጥ ባልቻለበት ፕሮጀክት ላይ ያሉት ሌሎች ጉዳዮች ሥራ ላይ መዋላቸውን እንዲቀጥሉ ውሳኔ ሲሰጥ፣ ተበዳሪው እንዲህ ባሉት የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ላይ በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት ምንም ዓይነት አስከፊ ተፅዕኖዎች እንደማይፈጠሩባቸው ያረጋግጣል።

በተበዳሪው እና ተፅዕኖ ባረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች መካከል የሚደርሱ ስምምነቶች ይብራራሉ እንዲሁም ስምምነቶቹን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ኣርምጃዎች በየአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅዱ (ESCP) ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋሉ። በትግበራ ወቅት፣ የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ለፕሮጀክቱ የሚሰጡትን ድጋፍ ይዞ ማቆየት እንዲቻል ተበዳሪው አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች መወሰዳቸውን እና ስምምነት የተደረሰባቸው ጥቅማ ጥቅሞች ወይም የአገልግሎቶች ማሻሻያዎች እንደተሰጡ ወይም እንደተደረጉ ያረጋግጣል።

### በባህላዊ ባለቤትነት ወይም በልማዳዊ አጠቃቀም ወይም ይዞታ ሥር በመመርኮዝ በመሬት እና ተፈጥሮ ሀብቶች ላይ አስከፊ ተፅዕኖዎች

የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ብዙውን ጊዜ ከመሬታቸው እና ተዛማጅ የተፈጥሮ ሀብቶች ጋር በቅርበት የተቆራኙ ናቸው። ብዙውን ጊዜ፣ መሬት በባህላዊ መንገድ የተያዘ ወይም በባህላዊ መንገድ ጥቅም ላይ የሚውል ወይም የሚተዳደር ነው። የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች በብሔራዊ ሕጉ በተደነገገው መሠረት የመሬት ባለቤትነት ሕጋዊ ማስረጃ ላይኖራቸው መቻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንነታቸው እና ማኅበረሰባቸውን የሚገልጹ ለኑሯቸው፣ ወይም ለባህላቸው፣ ለክብረ በዓላቶቻቸው እና መንፈሳዊ ዓላማዎቻቸው ወቅትን ጠብቀው የሚደረጉ ወይም ዑደታዊ የመሬት አጠቃቀሞች ብዙውን ጊዜ በማስረጃ ሊደገፉ እና በሰነድ ሊያዙ ይችላሉ። ፕሮጀክቶች (ሀ) የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች በባህላዊ መንገድ በባለቤትነት በያዟቸው ወይም በልምዳዊ መንገድ ጥቅም ላይ የዋሉ ወይም የተያዙ መሬቶች እና ግዛቶች ሕጋዊነት የተለበሱ የመሬት ባለቤትነት መብቶችን በማቋቋም ላይ የሚመረኮዙ እንቅስቃሴዎች፣ ወይም (ለ) እንዲህ ያሉትን መሬት መያዝን የሚመለከቱ ሲሆኑ፣ እንዲህ ያለውን የባለቤትነት መብት፣ ይዞታ ወይም አጠቃቀም ጉዳይ የሚመለከታቸውን የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ላኗቸው ባህሎች፣ ወጎች እና የመሬት ይዞታ ሥርዓቶች አስፈላጊውን አክብሮት በመስጠት ሕጋዊ ዕውቅና ሊገኝ የሚችልበትን ዕቅድ ተበዳሪው ያዘጋጃል። እንዲህ ያሉት ዕቅዶች ዓላማዎች እንደሚከተለው ይሆናሉ፦ (ሀ) አሁን ያሉትን የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ልማዳዊ የመሬት ይዞታ ሥርዓቶች ሙሉ ሕጋዊ ዕውቅና መስጠት፤ ወይም (ለ) ልማዳዊ የአጠቃቀም መብቶችን ወደ ወል እና/ወይም ግለሰባዊ ባለቤትነት መብቶች መቀየር። ከሁለቱም አማራጮች በብሔራዊ ሕግ ሥር አንዳቸውም ሊከናወኑ የማይችሉ ከሆነ፣ ዕቅዱ የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ቀጣይ ወይም ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ሊታደስ የሚችል የሞግዚትነት ወይም የመጠቀም መብቶችን ሕጋዊ ዕውቅና መስጠት የሚያስችሉ እርምጃዎችን ያካትታል።

### የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ከባህላዊ ባለቤትነት ወይም በተለምዶ ከነበረ አጠቃቀም ወይም ይዞታ ከመሬት እና ተፈጥሮ ሀብቶች አንሥቶ ወደ ሌላ ቦታ ማስፈር

በወል ከተያዙ ወይም በባህላዊ ባለቤትነት ወይም ልማዳዊ አጠቃቀም ወይም ይዞታ ጋር ግንኙነት ያላቸው መሬቶች እና ተፈጥሮ ሀብቶች የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ወደ ሌላ ቦታ እንዳይዛወሩ ለመከላከል አዋጭ አማራጭ የፕሮጀክት ዲዛይኖችን ተበዳሪው ከግምት ያስገባል። እንዲህ ያለው ወደ ሌላ ቦታ አዛውሮ ማስፈር ሊቀር የማይችል ከሆነ፣ በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫው (FPIC) ከላይ በተብራራው መንገድ የተገኘ ካልሆነ በቀር ተበዳሪው ከፕሮጀክቱ ጋር አይቀጥልም፤ እና ተበዳሪው ተገዶ የቦታ ይዞታን ማስለቀቅ አማራጭን አይመርጥም እንዲሁም ማናቸውም የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ውደ ሌላ ቦታ ማዛወሮች የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት

5 (ESS5) የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ ይሆናል። የሚቻል ሲሆን ወደ ሌላ ቦታ ተወስደው እንዲሰፍሩ የተደረጉበት ምክንያት መፍትሔ ሲያገኝ የአካባቢው ተወላጆች/ከሳህራ በታች ያሉ በታሪክ የአፍሪካ በቂ አገልግሎት ያላገኙ ባህላዊ የአካባቢ ማኅበረሰቦች ወደ ባህላዊ ወይም የተለምዶ መሬታቸው መመለስ እንዲችሉ ይደረጋል።

## ዓባሪ 8፡- የአካባቢ ተወላጆች ዕቅድ ጠቋሚ ቢጋር

የአካባቢ ተወላጆች ዕቅድ ጠቋሚ ቢጋር እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

*የሚከተለው የግል የኃይል አምራቾች (IPP) ቁልፍ አባለ ነገራትን ያቀርባል፡- የአገር ተወላጆች ከፕሮጀክት እና/ንኡስ ፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ተጠቃሚዎች በሚሆኑባቸው ሁኔታዎች እና/ወይም ቀላል ተፅዕኖዎች እንደሚደርሱ ሲገመቱ የግል የኃይል አምራቾች (IPP) አባለ ነገሮች እንደ የመሬት መያዝ እና ሕዝብን ወደ ሌላ ቦታ ማስፈር ዕቅዶች ወይም የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMPs) የመሳሰሉ ሌሎች ሕጋዊ ሰነዶች ላይ ሊካተቱ ይችላሉ። እነዚህ አባለ ነገሮችን የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-*

a. ***የግል የኃይል አምራቾች (IPP) አጭር ማጠቃለያ።*** *ይህ ክፍል (ለብቻቸው ለሚቆሙ የግል የኃይል አምራቾች (IPP) የሚያስፈልጉ) ወሳኝ እውነታዎችን፣ በጉልህ የሚታዩ ግኝቶችን እና ጠቃሚ ምክሮችን በአጭሩ ያብራራል፤*

b. ***በአካባቢ ተወላጆች ላይ ተፅዕኖ ያላቸው የፕሮጀክት እና/ወይም ንኡስ ፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ምዘናዎች።*** *ይህ ክፍል እንዲህ ያሉት ተፅዕኖዎች ያላቸው ተፈጥሮ እና ደረጃ ትንታኔ ያቀርባል፤ እንዲህ ማድረግም ይኖርበታል፡-*

   i. *በፕሮጀክት ዓውድ ውስጥ ለአካባቢ ተወላጆች ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጋዊ እና ተቋማዊ ማዕቀፍ መገምገም።*

   ii. *ተፅዕኖ ያረፈባቸውን ማኅበረሰቦች ሥነ ሕዝባዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካ ባሕሪያት፣ በባህላዊ መንገድ በባለቤትነት የያዙት መሬት እና ግዛቶች ወይም በልማዳዊ መንገድ ጥቅም ላይ የዋሉ ወይም የተያዙ መሬቶች እና እነርሱ ጥገኛ የሚሆኑባቸው የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ መሠረታዊ መረጃን ማቅረብ።*

   iii. *ቁልፍ የፕሮጀክት ባለድርሻ አካላትን ለይቶ ማወቅ እና በፕሮጀክቱ ዝግጅት እና ትግበራ እያንዳንዱ ደረጃ ላይ ከአካባቢ ተወላጆች ጋር ትርጉም ያለው ምክክር ለማድረግ በባህል ተቀባይነት ያለው እና የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ ግድ የሚለው ሂደትን ማዳበር፣ ግምገማውን እናም መሠረታዊ መረጃ ከግምት ማስገባት።*

   iv. *ተፅዕኖ ካረፈባቸው ማኅበረሰቦች ጋር በተደረገ ትርጉም ያለው ምክክር ላይ በመመርኮዝ የፕሮጀክቱን እና ንእሱ ፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ሊያስከትሉ የሚችሏቸውን አስከፊ እና አዎንታዊ ውጤቶችን መመዘን። ሊያጋጥሙ የሚችሉ አስከፊ ተፅዕኖዎች ስለመኖራቸው ከድምዳሜ ላይ ለመድረስ ወሳኙ ተፅዕኖ ባረፈባቸው የአካባቢ ተወላጆች ላይ ከመሬት እና ተፈጥሮ ሀብቶች ጋር ካላቸው ቅርብ ትስስር እና ያሉበት ሁኔታን ከግምት በማስገባት እንዲሁም ለሌሎች በማኅበረሰቦች፣ ክልሎች ወይም እነርሱ በሚኖሩባቸው ብሔራዊ ማኅበረሰቦች ውስጥ ላሉ የማኅበረሰብ ቡድኖች በአንፃራዊንት የሚገኙ ዕድሎችን ለማግኘት ካላቸው የመዳረሻ ዕጥረት ከግምት በማስገባት ያላቸውን አንፃራዊ ተጋላጭነት እና ስጋቶች ሥርዓተ ጾታ ግድ የሚለው ትንታኔ ነው።*

   v. *ተፅዕኖ ያረፈባቸው የአካባቢ ተወላጆች ስለ ፕሮጀክት ያላቸው አመለካከት እና በእነርሱ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ሁኔታ ላይ ያለው ተፅዕኖ ላይ ሥርዓተ ጾታ ግድ የሚለው ምዘናን ማካተት።*

   vi. *ተፅዕኖ ካረፈባቸው ማኅበረሰቦች ጋር በተደረገ ትርጉም ያለው ምክክር ላይ በመመርኮዝ፣ አስከፊ ተፅዕኖዎችን ለማስቀረት የሚያስፈልጉ እርምጃዎች ለይቶ ማስቀመጥ እና ጠቃሚ ምክር መስጠት፤ ወይም እንዲህ ያሉት እርምጃዎች የማይቻሉ ከሆነ እንዲህ ያሉትን ተፅዕኖዎች ለመቀነስ፣ ለማስታረቅ እና/ወይም ካሳ ለማቅረብ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ለይቶ ማስቀመጥ፣ እና የአካባቢው ተወላጆች በፕሮጀክቱ ሥራ በባህል ተቀባይነት ያላቸውን ጥቅማ ጥቅሞች ማግኘት መቻላቸውን ለማረጋገጥ።*

c. ***በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫን (FPIC) የሚጠይቁ ሁኔታዎች ምዘናዎች እና አስከፊ ተፅዕኖዎችን ለማስቀረት አማራጭ የፕሮጀክት ዲዛይን/ቦታ ምርመራዎች (በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ ክፍልን ይመልከቱ)።***

**d.** ***የመረጃ ይፋ ማውጣት፣ ምክክር እና ተሳትፎ።*** *ይህ ክፍል፡-*

i. *በፕሮጀክት ዝግጅት ወቅት ሊከናወኑ የሚችሉ የመረጃ ይፋ ማውጣትን፣ ምክክርን እና ተፅዕኖ ካረፈባቸው ማኅበረሰቦች ጋር ተሳትፎ ማድረግ ሂደት ያብራራል፤*

ii. *በማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘና ውጤቶች ላይ የእነርሱን አስተያየት እና በምክክር ወቅት የተነሡ ጥያቄዎችን እና እንዴት እነዚህ በፕሮጀክት ዲዛይን እንዴት እንደተያዙ በአጭሩ ማስቀመጥ፤*

iii. *የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) የሚጠይቁ በሚሆኑበት ጊዜ ሂደቱን እና ተፅዕኖ ካረፈባቸው ማኅበረሰቦች ጋር እንደ የሚደረጉ ምክክሮች እና ለፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች እና እንዲህ ያሉት እንቅስቃሴዎች ተፅዕኖዎች ላይ የስጋት ቁጥጥር ማድረጊያ እርምጃዎች በእነዚህ ምክክሮች ምክንያት የሚገኝ ማናቸውም ስምምነትየሚገኝ ውጤትን በሰነድ መያዝ፤*

iv. *የአካባቢ ተወላጆች በትግበራ ወቅት መሳተፍ መቻላቸውን ለማረጋገጥ በትግበራ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ የምክክር እና የተሳትፎ ማድረጊያ ዘዴዎችን ማብራራት፤ እና*

v. *ተፅዕኖ ላረፈባቸው የአካባቢው ተወላጆች ረቂቁኣን የመጨረሻዎቹ ሰነዶች ይፋ እንደተደረጉላቸው ማረጋገጥ፤*

**e.** ***የጥቅማ ጥቅሞች ማጋሪያ ዘዴዎች።*** *ይህ ክፍል ተፅዕኖ ያረፈባቸው ማኅበረሰቦች በባህል ተቀባይነት ያላቸውን እና ሥርዓተ ጾታን ከግምት የሚያስገቡ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅማ ጥቅሞች መቀበላቸውን ለማረጋገጥ የሚወሰዱ እርምጃዎችን አንድ በአንድ ያስቀምጣል።*

**f.** ***የማስታረቂያ እርምጃዎች።*** *ይህ ክፍል በአካባቢ ተወላጆች ላይ አስከፊ ተፅዕኖዎችን እንዳይደርሱ ለመከላከል የሚወሰዱ እርምጃዎችን፣ እና ማስቀረት ሳይቻል ሲቀር፣ ለእያንዳንዱ ተፅዕኖ የሚያርፍበት ማኅበረሰብ ተለይተው የታወቁ አስከፊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ፣ ለማስታረቅ እና ካሳ ለመስጠት የሚያስችሉ እርምጃዎችን ያብራራል።*

**g.** ***የአቅም ግንባታ።*** *ይህ ክፍል የሚከተሉትን አካላት ማኅበራዊ፣ ሕጋዊ እና ቴክኒክ አቅሞች ለማጠናከር የሚያስችሉ እርምጃዎችን ያቀርባል፡- (ሀ) የመንግሥት ተቋማት በፕሮጀክት አካባቢ ውስጥ የአካባቢ ተወላጆችን ችግሮች መፍትሔ እንዲሰጡ፤ እና (ለ) በፕሮጀክቱ አካባቢ ውስጥ ያሉ ተፅዕኖ ያረፈባቸው የማኅበረሰብ ድርጅቶች የእነርሱን ማኅበረሰቦች ይበልጥ በወጤታማነት መወከል እንዲችሉ እና በስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ቁጥጥር ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ።*

**h.** ***ግብረ መልስ እና የቅሬታ አፈታት ዘዴ።*** *ይህ ክፍል ተፅዕኖ ባረፈባቸው የአካባቢው ተወላጅ ሕዝቦችና ማኅበረሰቦች ላይ የቀረቡ አቤቱታዎችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ጥቅም ላይ የሚውሉትን የአሠራር ሥርዓቶች ያብራራል። ǀበተጨማሪ አሠራር ሥርዓቶች እንዴት ለአካባቢ ተወላጆች ተደራሽ እንደሆነ እና በባህል ተገቢነት ያለው እና ሥርዓተ ጾታ ጉዳዮች ግድ የሚለው ስለ መሆኑ ያብራራል።*

**i.** ***ክትትል፣ ሪፖርት አደራረግ እና ምዘና።*** *ይህ ክፍል የግል የኃይል አምራቾችን (IPP) ትግበራ ለመከታተል እና ለመመዘን ጥቅም ላይ የሚውሉትን ዘዴዎችን እና ካስማዎችን ያብራራል። በክትትል፣ እና በምዘና ሪፖርቶች ዝግጅት እና ማጽደቅ ሥራ ላይ ተፅዕኖ ያረፈባቸው የአገር ተወላጆች ተሳትፎ ማድረግ የሚያስችላቸውን ዘዴዎች በተጨማሪ ይጠቅሳል።*

**j.** ***ተቋማዊ አደረጃጀቶች።*** *ይህ ክፍል በየግል የኃይል አምራቾች (IPP) ውስጥ ያሉትን የተለያዩ የማስታረቂያ እርምጃዎች ለማከናወን የሚያስፈልጉትን ተቋማዊ አደረጃጀት ኃላፊነቶች እና ዘዴዎችን ያብራራል። ተዛማጅነት ያላቸው የአካባቢ ድርጅቶች እና/ወይም መያዶችን የግል የኃይል አምራቾች (IPP) በማከናወን ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ የሚያስችል ሂደትን በተጨማሪ ያብራራል።*

k. ***በጀት እና ፋይናንስ።*** *ይህ ክፍል በየግል የኃይል አምራቾች (IPP) ውስጥ ለተዘረዘሩት ሁሉም እንቅስቃሴዎች አንድ በአንድ ተዘርዝሮ የቀረበ በጀትን ያቀርባል።*

*የሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC) መስፈርት የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘናዎች (ESIAs) አንድ አካል በሚሆንበት ጊዜ ገለልተኛ የሆኑ ስፔሺያሊስቶች በሙሉ ግንዛቤ፣ በነጻነት እና በቅድሚያ የተሰጠ የፈቃደኝነት ማረጋገጫ (FPIC)ን ለማሳላጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ይደረጋል። የባለድርሻ አካል ቅሬት አቀራረብ ዘዴ ይዘጋጃል፣ የአካባቢ ተወላጆች ማናቸውንም ግብረመልሶችን ወይም ቅሬታቸውን ማስገባት እንዲችሉ የሚያደርጉ መስፈርቶችን ያካትታል።*

## ዓባሪ 9፡- የሠራተኛ አስተዳደር አሠራር ሥርዓቶች ጠቋሚ

በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2) የሠራተኛ እና የሥራ ቦታ ሁኔታ ሥር ተበዳሪዎች የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) እንዲያዘጋጁ ይገደዳሉ። የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) ዓላማ የፕሮጀክቱን ዕቅድ አወጣጥ እና ትግበራን ለማሣለጥ ነው። የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያ (LMP) ከፕሮጀክቱ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ዋንኛ የሠራተኛ መስፈርቶችን እና ስጋቶችን ለይቶ ያስቀምጣል እና ተበዳሪው የፕሮጀክት የሠራተኛ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ተበዳሪው እንዲያውቅ ያግዛል። የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያ (LMP) በፕሮጀክት ዝግጅት ወቅት ገና ከመጀመሪያው የሚዘጋጅ እና በፕሮጀክት ዝግጅት እና ትግበራ ወቅት እየተሻሻለ የሚሄድ ህያው ሰነድ ነው።

ዝግጁ አብነቱ ተበዳሪዎች የሠራተኛ ዕቅድ አወጣጥ እና አስተዳደር ቁልፍ ገጽታዎችን ለይተው እንዲያውቁ ለማስቻል የተዘጋጀ ነው። ይዘቱ ጠቋሚ ነው፡- ተለይተው የታወቁት ችግሮች በፕሮጀክቱ ውስጥ ተዛማጅነት ያላቸው ናቸው፣ ተበዳሪዎች በ የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) ውስጥ ሊይዟቸው ይገባል። አንዳንድ ችግሮች ተዛማጅነት ላይኖራቸው ይችል ይሆናል፤ አንዳንድ ፕሮጀክቶች ከዕቅድ አወጣጥ ዕይታ አንፃር መያዝ ያለባቸው ሌሎች ችግሮች ሊኖሯቸው ይችላሉ። የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2) መስፈርቶችን ብሔራዊ ሕግን በሚጠይቁበት ሁኔታ ይህ በየሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) ውስጥ ሊስተዋል ይችላል እና እንዲህ ያሉትን ድንጋጌዎች የመደጋገም አስፈላጊነት የለም። የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) ራሳቸውን ችለው እንደ አንድ ሰነድ ሊዘጋጁ ወይም የሌላ አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ሰነዶች አንድ አካል ሊሆኑ ይችላሉ።

እጥር ምጥን ያለ እና ወቅቱን የጠበቀ የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያ (LMP) የተለያዩ ከፕሮጀክት ጋር የተገናኙ የተለያዩ አካላት ለምሳሌ አንድን አሃድ በመተግበር ላይ ያሉ የፕሮጀክቱ ሠራተኞች፣ ሥራ ተቋራጮች እና ንኡስ ሥራ ተቋራጮች እና የፕሮጀክት ሠራተኞች በአንድ የተወሰነ የሠራተኛ ጉዳይ ችግር ላይ ምን እንደሚያስፈልግ ግልጽ የሆነ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል። በየሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) ውስጥ የተካተተው ዝርዝር ጉዳይ ደረጃ በፕሮጀክቱ ዓይነት እና ሊገኝ በሚችለው መረጃ ላይ የሚመረኮዝ ይሆናል። ተዛማጅነት ያለው መረጃ ሊገኝ በማይችልበት ጊዜ ይህ በማስታወሻ ተይዞ የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) በተቻለ ፍጥነት ወቅታዊ እንዲሆኑ መደረግ አለባቸው።

የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያ (LMP) በማዘጋጀት እና በማሻሻል ወቅት፣ ተበዳሪዎች የብሔራዊ ሕግ እና አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2) እና ለአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2) የጠቃሚ ምክር ማስታወሻ (GN) የተሰጠ መመሪያ ማስታወሻን ይመለከታሉ። ዝግጁ አብነቱ ለሁለቱም አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2) እና አጠቃላይ ማስታወሻ (GN) የሚሆኑ ዋቢዎችን ያካትታል።

*ሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) ጠቋሚ ዝግጁ አብነት (ቴምፕሌት) ቢጋር፡-*

### 1. በፕሮጀክቱ ላይ የሠራተኛ አጠቃቀም አጠቃላይ ዕይታ

ይህ ክፍል ባለው መረጃ ላይ በመመርኮዝ የሚከተለውን ያብራራል፡-

a. የፕሮጀክት ሠራተኞችን ብዛት፡- በፕሮጀክቱ ላይ የሚቀጠሩ ሠራተኞችን አጠቃላይ ድምር፣ እና የተለያዩ ዓይነት ሠራተኞች፡- ቀጥታ ሠራተኞች፣ ጊዜያዊ ቅጥር ሠራተኞች እና የማኅበረሰብ ሠራተኞች። ቁጥሮች እርግጠኛ ሆነው መቅረብ ሳይችሉ ሲቀር ግምቱ መሰጠት አለበት።

b. የፕሮጀክት ሠራተኞች ጠባዮች፦ በተቻለ መጠን፣ ሰፋ ያለ ዝርዝር መግለጫ እና የፕሮጀክት ሠራተኞች ሊኖራቸው የሚችል ጠቋሚ ለምሳሌ የአካባቢ ሠራተኞች፣ ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ፍልሰተኞች፣ ሴት ሠራተኞች፣ ከዝቅተኛ ዕድሜ እና በ18 ዓመት መካከል ያሉ ሠራተኞች።

c. የሠራተኛ መስፈርቶች የጊዜ መርሐግብር አወጣጥ፦ ከሚያስፈልገው ብዛት፣ ቦታ፣ የሥራ ዓይነት እና ክኅሎት አንፃር የሠራተኛ መመዘኛ መስፈርቶች የጊዜ መርሐግብር እና ቅደም ተከተል አቀማመጥ።

d. ጊዜያዊ ቅጥር ሠራተኞች፦ ከሥራ ተቋራጮች/ንኡስ ሥራ ተቋራጮች ብዛት እና ዓይነቶች እንዲሁም ከሚቀጠሩ የፕሮጀክት ሠራተኞች ሊደርስ የሚችል ብዛት ጋር ወይም በሥራ ተቋራጮች/ንኡስ ሥራ ተቋራጮች የሚቀጠሩ ሠራተኞች ብችዛት ጋር ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው ወይም የታወቀ የፕሮጀክቱ የታወቀ ሥራ ተቋራጭ መዋቅር፣ የፕሮጀክት ሠራተኞች በደላሎች፣ በአገናኞች ወይም በኤጀንቶች አማካይነት የሚቀጠሩ ከመሰለ፣ ይህ ምን ያክል ሠራተኞች በዚህ መንገድ ይቀጠራሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ከሚያሳይ ግምት ጋር በማስታወሻ መያዝ አለበት።

e. ፍልሰተኛ ሠራተኞች፦ ፍልሰተኛ ሠራተኞች (የአገር ውስጥ ወይም ዓለምአቀፍ) በፕሮጀክቱ ላይ ይሠራሉ ተብሎ የሚጠበቅ ከሆነ ይህ በማስታወሻ ተይዞ ዝርዝሮቹ መሰጠት ይኖርበታል።

## 2. ቁልፍ ሊያጋጥሙ የሚችሉ የሠራተኛ ነክ ስጋቶች ምዘና

ይህ ክፍል ባለው መረጃ ላይ በመመርኮዝ የሚከተለውን ያብራራል፦

a. የፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች፦ የፕሮጀክቱ ዓይነት እና ቦታ፣ እና የፕሮጀክቱ ሠራተኞች የሚያከናውኗቸው የተለያዩ ሥራዎች።

b. ቁልፍ ሠራተኛ ነክ ስጋቶች፦ ከፕሮጀክቱ ጋር ግንኙነት ሊኖራቸው የሚችሉ ቁልፍ ሠራተኛ ነክ ስጋቶች (ለምሳሌ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2) እና አጠቃላይ ማስታወሻ (GN) ውስጥ ተለይተው የተሰጡትን ይመልከቱ)። ይህ ለምሳሌ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦

- እንደ በከፍታ ቦታዎች ላይ ሆኖ መሥራት ወይም በዝግ የሆኑ ቦታዎች ውስጥ መሥራት፣ ከባድ ማሽኖችን መጠቀም ወይም አደገኛ ማቴሪያሎች መጠቀም የመሳሰሉ አደገኛ ሥራዎችን መሥራት
- የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ወይም የግዳጅ ሥራ፣ ከዘርፉ ወይም ከአካባቢው አንፃር ሊያጋጥም የሚችል
- የፍልሰተኞች ወይም ወቅትን ጠብቀው ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞች አይቀሬ በቦታው መገኘት
- ከሠራተኛ ጋር የተገናኙ ፍልሰቶችና ሰፈራዎች ጋር ወይም ከጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃቃት ጋር የተገናኙ ስጋቶች
- ከዘርፉ ወይም አካባቢው አንፃር የሚታይ ሊያጋጥም የሚችል አደጋ ወይም ድንገተኛ ሁኔታ
- የሥራ ቦታ ላይ ጤና እና ደኅንነት መስፈርቶች አጠቃላይ ግንዛቤ እና ትግበራ

## 3. የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ አጭር አጠቃላይ ዕይታ፦ ውሎች እና ግዴታዎች

ይህ ክፍል ከሥራ ውል እና ግዴታዎች አንፃር እና እንዴት ብሔራዊ ሕጉ በተለያዩ በክፍል 1 ውስጥ ተለይተው የተቀመጡ የሠራተኛ ምድቦች ውስጥ ተፈጻሚ እንደሚሆን በተመለከተ የብሔራዊ የሠራተኛ ሕጉን ቁልፍ ገጽታዎች ያቀርባል። አጠቃላይ ዕይታው በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2)፣ አንቀጽ 11 ላይ የተቀመጡትን ንጥል ነገሮች ጋር የተገናኘ ሕግ ላይ ያተኩራል (ለምሳሌ ደመዎዝ፣ ተቀናሾች እና ጥቅማ ጥቅሞች)።

## 4. የአሠሪና ሠራተኛ ሕግ አጭር አጠቃላይ ዕይታ፦ የሥራ ቦታ ላይ ጤና እና ደኅንነት

ይህ ክፍል ከሥራ ቦታ ጤና እና ደኅንነት አንፃር እና እንዴት ብሔራዊ ሕጉ በተለያዩ በክፍል 1 ውስጥ ተለይተው የተቀመጡ የሠራተኛ ምድቦች ውስጥ ተፈጻሚ እንደሚሆን በተመለከተ የብሔራዊ የሠራተኛ ሕጉን ቁልፍ ገጽታዎች ያቀርባል። አጠቃላይ ዕይታው በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2)፣ አንቀጽ 24 እስከ 30 ላይ የተቀመጡትን ንጥል ነገሮች ጋር የተገናኘ ሕግ ላይ ያተኩራል።

## 5. ኃላፊነት ያለባቸው ሠራተኞች

ይህ ክፍል በፕሮጀክቱ ውስጥ ለሚከተሉት ኃላፊነት ያላቸው ተግባራትን እና/ወይም ግለሰቦችን ለይቶ ያስቀምጣል (እንደ ተዛማጅነቱ)፡-

a. የፕሮጀክት ሠራተኞችን ማሳተፍ እና ማስተዳደር
b. ሥራ ተቋራጮችን/ንኡስ ሥራ ተቋራጮችን ማሳተፍእና ማስተዳደር
c. የሥራ አካባቢ ደኅንነት እና ጤንነት (OHS) እርምጃዎች
d. የሠራተኞች ሥልጠና
e. ለሠራተኛ ቅሬታ መፍትሔ መስጠት

በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ይህ ክፍል በተለይ የፕሮጀክት ሠራተኞች በሦስተኛ ወገኖች በሚቀጠሩባቸው ፕሮጀክቶች ላይ በሥራ ተቋራጮች ወይም በንኡስ ሥራ ተቋራጮች ተግባራት እና/ወይም ግለሰቦችን ለይቶ ያስቀምጣል።

## 6. ፖሊሲዎች እና የአፈጻጸም ሥርዓቶች

ይህ ክፍል በየሥራ አካባቢ ደኅንነት እና ጤንነት (OHS) ሪፖርት አደራረግ እና ክትትል እንዲሁም ሌሎች አጠቃላይ የፕሮጀክት ፖሊሲዎች ላይ መረጃን ያቀርባል። ተዛማጅነት ሲኖረው፣ ተገቢነት ያለውን ብሔራዊ ሕግ ለይቶ ያስቀምጣል።

ጉልህ የሆኑ የደኅንነት ስጋቶች  እንደ ክፍል 2 አንድ አካል ተለይተው ሲታወቁ፣ ይህ ክፍል እነዚህ እንዴት መፍትሔ ሊሰጣቸው እንደሚችል አንኳር የሆኑ ነጥቦችን ያስቀምጣል። የግዳጅ ሥራ ስጋቱ ተለይቶ ሲታወቅ፣ ይህ ክፍል ይህ እንዴት መፍትሔ ሊያገኝ እንደሚችል አንኳር ነጥቦች ያስቀምጣል (አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2)) አንቀጽ 20 እና ተዛማጅነት ያላቸው አጠቃላይ ማስታወሻዎችን (GNs ይመልከቱ)። የሕፃን ጉልበት ብዝበዛ እንዳለ ተለይቶ ከታወቀ፣ እነዚህ ችግሮች በክፍል 7 ውስጥ ተብራርተዋል።

ተበዳሪው ራሳቸውን የቻሉ ፖሊሲዎች እና ሥራ አፈጻጸም ሥርዓቶች ካሉት እነዚህ በየሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) ውስጥ ከሌሎች ማናቸውም ደጋፊ ሰነዶች ጋር አብሮ ይጠቀሳል እንዲሁም ዓባሪ ይደረጋል።

## 7. የሥራ ቅጥር ዕድሜ

ይህ ክፍል የሚከተሉትን በተመለከተ ዝርዝሮችን ያስቀምጣል፡-

ሀ. በፕሮጀክቱ ላይ ዝቅተኛ ለሥራ ቅጥር የሚፈቀድ ዕድሜ

ለ. የፕሮጀክት ሠራተኞች ዕድሜያቸውን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ የሚውል ሂደት

ሐ. ዕድሜያቸው ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሠራተኞች በፕሮጀክቱ ውስጥ እየሠሩ ከተገኙ ተፈጻሚ የሚሆነው የአፈጻጸም ሥርዓት

መ. ዕድሜያቸው ከዝቅተኛ ዕድሜ እና በ18 ዓመት መካከል ላለ ሠራተኞች የስጋት ምዘናዎች የአፈጻጸም ሥርዓት

አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS 2)፣ አንቀጽ 17 እስከ 19 እንዲሁም ተዛማጅነት ያላቸውን የጠቃሚ ምክር ማስታወሻዎች (GNs) ይመልከቱ።

## 8. ውሎች እና ግዴታዎች

ይህ ክፍል የሚከተሉትን በተመለከተ ዝርዝሮችን ያስቀምጣል፦

- ሀ. በፕሮጀክቱ ላይ ተፈጻሚነት ያላቸው የተወሰኑ አበሎች፣ የሥራ ሰዓታት እና ሌሎች ድንጋጌዎች
- ለ. በፕሮጀክቱ ላይ በሥራ ላይ ሊቆይ የሚችልበት ከፍተኛው የሰዓታት ብዛት
- ሐ. በፕሮጀክቱ ላይ ተፈጻሚነት ያላቸው ማናቸውም የኅብረት ስምምነቶች። ተዛማጅነት ሲኖረው፣ የስምምነቶች ዝርዝርን ማቅረብ እና ቁልፍ ባሕሪያትን እና ድንጋጌዎችን ማብራራት
- መ. ሌሎች የተወሰኑ ውሎች እና ግዴታዎች

## 9. የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ

ይህ ክፍል ለቀጥታ እና ጊዜያዊ ሠራተኞች የሚሰጠውን የቅሬት አቀራረብ ዘዴ ዝርዞች ያስቀምጣል እና እነዚህ ሠራተኞች ስለ ዘዴው ሊያውቁ እንዲችሉ ስለሚደረግበት መንገድ ማብራሪያን ይሰጣል።

የማኅበረሰብ ሠራተኞች በፕሮጀክቱ ውስጥ እንዲሳተፉ ሲደረጉ፣ የእነዚህ ሠራተኞች የቅሬታ አቀራረብ ዘዴ ዝርዝሮች በክፍል 11 ላይ ተቀምጠዋል።

## 10. የሥራ ተቋራጭ አስተዳደር

ይህ ክፍል የሚከተሉትን በተመለከተ ዝርዝሮችን ያስቀምጣል፦

- ሀ. የሥራ ተቋራጮች መረጣ ሂደት በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2)፣ አንቀጽ31 እና አጠቃላይ ማስታወሻ (GN) 31.1 ላይ ተብራርቷል።
- ለ. የሠራተኛ ችግሮችን ለመቆጣጠር ከሥራ ተቋራጮች ጋር የተገናኙ የሥራ ውል ድንጋጌዎች በአካባቢ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2)፣ አንቀጽ 32 እና አጠቃላይ ማስታወሻ (GN) 32.1 ላይ በተጠቀሰው መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል።
- ሐ. የሥራ ተቋራጮችን ሥራ አፈጻጸም ለማስተዳደር እና ለመከታተል ሥራ ላይ የሚውሉ አፈጻጸም ሥርዓቶች በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2)፣ አንቀጽ 32 እና አጠቃላይ ማስታወሻ (GN) 32.1 ላይ በተብራራው መሠረት

## 11. የማኅበረሰብ ሠራተኞች

የማኅበረሰብ ሠራተኞች በፕሮጀክቱ ውስጥ ተሳትፎ ሲያደርጉ፣ ይህ ክፍል የሥራውን ውሎች እና ደንቦች ዝርዝሮች ያስቀምጣል እና የማኅበረሰብ ሠራተና በፈቃደኝነት ላይ በመመርኮዝ እንደቀረበ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ እርምጃዎችን ለይቶ ያስቀምጣል።

በተጨማሪ የሚያስፈልጉ ስምምነቶች ዓይነት እና እንዴት በሰነድ እንደሚያዙ ዝርዝሮችን ያቀርባል። የጠቃሚ ምክር ማስታወሻ (GN) 34.4ን ይመልከቱ።

ይህ ክፍል ለማኅበረሰብ ሠራተኞች ቅሬታ አቀራረብ ዘዴን እንዲሁም እንዲህ ያሉ ሠራተኞች በተመለከተ ክትትል ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ሚናዎች እና ኃላፊነቶች ዝርዝርን ያቀርባል። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርት 2 (ESS2)፣ አንቀጽ 36 እና 37ን ይመልከቱ።

## 12. ተቀዳሚ የአቅርቦት ሠራተኞች

ከተቀዳሚ አቅራቢዎች ጋር በተገናኘ በጉልህ የሚታይ የሕፃን ጉልበት ብዝበዛ ወይም የግዳጅ ሥራ ወይም ከባድ የደኅንነት ችግሮች እንዳሉ ተለይተው ከታወቁ በኋላ፣ ይህ ክፍል በተቀዳሚ አቅራቢ ሠራተኞች ላይ ክትትል ለማድረግ እና ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓትን ያስቀምጣል።

## ዓባሪ 10፡- ሥርዓተ ጾታ

የባንኩ አጠቃላይ የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ አያያዝ በዓለም ባንክ ቡድን የሥርዓተ ጾታ ስትራቴጂ (FY16-23) እና OP4.20 የሚመራ ነው፡- ሥርዓተ ጾታ እና ልማት። የሥርዓተ ጾታው ስትራቴጂ በበርካታ አገራት እና እንደ ክፍለ አህጉራዊ የሥርዓተ ጾታ ድርጊት መርሐ ግብር፣ የአገር መመርመሪያዎች (እና በአንዳንድ ክፍለ አህጉራት ውስጥ ከአገር የድርጊት መርሐ ግብሮች እና መድረኮች)፣ እና ዓለም አቀፍ የሥርዓተ ጾታ ስትራቴጂ ክትትል ማስታወሻዎች አማካይነት የሚደገፍ ነው።

በፕሮጀክት ደረጃ ላይ፣ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) ውስጥ ያሉት በሥርዓተ ጾታ ላይ የተቀመጡ ድንጋጌዎች በተለይ የተበደሉ ወይም ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖች፣ ሥርዓተ ጾታን ያማከል ጥቃትን ጨምሮ በሥርዓተ ጾታ እኩልነት እና አሳታፊነት ላይ የሚያተኩር ይሆናል። የ 2018 የሥርዓተ ጾታን ያማከለ ጥቃት (GBV) የመልካም አሠራር ማስታወሻ ከፍተኛ የሲቪል ኮንስትራክሽን ሥራዎችን በሚጠይቁ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፈንዶች /IPFs/ ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ወሲባዊ ጭቆና እና ጥቃት (SEA)/ወሲባዊ ጥቃት (SH) ከፍ ሊሉ እንደሚችሉ እና እነዚህን መቆጣጠር ስለሚቻልባቸው መንገዶችን ማብራሪያን ያቀርባል። አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) በተጨማሪ ቁልፍ የሥርዓተ ጾታ ክፍተቶችን ለመዝጋት በፕሮጀክት ደረጃ ያሉ ዕድሎችን ያበረታታል።

ተበዳሪው አካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች የማሟላት ኃላፊነቱን ይወስዳል፣ ባንኩዱ ደግሞ በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) በኩል ማድረግ ያለበትን ጥንቃቄ ያደርጋል። ባንኩ በኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ፋይናንስ አቀራረብ በኩል ለሚደገፉ ፕሮጀክቶች በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) መሠረት ተበዳሪዎች ለአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) ሲያመለከቱ እገዛ ያቀርብላቸዋል። የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) ትግበራ ስኬት በተበዳሪው ግንዛቤ እና በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) ሥር ያሉትን ችግሮችን፣ ሥርዓተ ጾታ ክፍተቶችን ጨምሮ በመረዳት ላይ በከፍተኛ ደረጃ የሚመረኮዝ ይሆናል። ለዚህ ሲባል እንደ አስፈላጊነቱ የባንክ ድጋፍ ለፕሮጀክት ትግበራ አሃድ ሠራተኞች በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ማዕቀፍ (ESF) በሥርዓተ ጾታ ረገድ የተቀመጡ ግዴታዎች እና በፕሮጀክቱ የሕይወት ዘመን ወቅት አፈጻምን በመከታተል ላይ የሚሰጡ የቴክኒክ ሥልጠናን የሚያካትት ይሆናል።

የፕሮጀክት ዑደቱ የተለያዩ ደረጃዎች - የፕሮጀክት ልየታ፣ የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ስጋቶች ምዘና፣ ውጤት አሰጣጥ፣ ትግበራ እና ክትትል - ሁሉም የሥርዓተ ጾታን እኩልነት እና በፕሮጀክት ደረጃ አሳታፊነትን በአምስት የተወሰኑ ዘዴዎች ዕድሎችን ይሰጣል፡-

ሀ. ከሥርዓተ ጾታ እኩልነት አለመኖር በተነሣ የሚፈጠሩትን ጨምሮ፣ የፕሮጀክት ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች የመጀመሪያ ደረጃ ***ምርመራ***፤

ለ. ለማስታረቂያ እርምጃ የተዘጋጀ የሥርዓተ ጾታ ክፍተቶችን የሚቀንስ የአካባቢ እና ማኅበራዊ ዋስትና ስጋቶች እና ተፅዕኖዎች ለይቶ ለማወቅ ጥቅም ላይ የሚውል ***ምዘና***(የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ ተፅዕኖ ምዘና (ESIA), የአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዶች (ESMP), RAP, የሠራተኛ አስተዳደር አፈጻጸም መመሪያዎች (LMP) and Stakeholder Engagement Plan (የባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) ጨምሮ) በአካባቢያዊ እና ማኅበራዊ መመዘኛ መስፈርቶች (ESSs) በተቀመጠው መሠረት። ሁሉን አቀፍ የሥርዓተ ጾታ ትንታኔ ቃል ሊገባ ይችላል፤

ሐ. ***ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ*** በጠቅላላ የፕሮጀክቱ ዕድሜ ወቅት ትርጉም ካለው ምክክር፣ መረጃ መስጠት እና ምላሽ ሰጪ ከሆነ የአቤቱታ አቀራረብ ዘዴ ጋር በየባለ ድርሻ አካላት ተሳትፎ ዕቅድ (SEP) መሠረት የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ማጣት የሚነሣ ልዩ ፍላጎት እና ስጋቶች።

መ.	በየአካባቢያዊ እና የማኅበራዊ ግዴታ ዕቅድ (ESCP) ውስጥ ባሉት የሥርዓተ ጾታ ጉዳይን ከግምት ማስገባት ጋር ግንኙነት ባላቸው ቁልፍ ***ግዴታዎች***ላይ መስማማት፤

ሠ.	ከሥርዓተ ጾታ ጋር የተገናኙ የፕሮጀክት ውጤቶች ***ተስማሚ የስጋት ቁጥጥር እና ክትትል***።